የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፹፪
አዲስ አበባ ህዳር ፴ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20[th] Year No. 82
ADDIS ABABA 9[th] December, 2014

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፳፻፯ ዓ.ም

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር አዋጅ..........................ገጽ ፯ሺ፯፻፶፭

**CONTENTS**

Proclamation No. 859/2014

Customs Proclamation ....................................Page 7755

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፳፻፯

## የጉምሩክ አዋጅ

ዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣምና በአገራችን እያደገ የመጣውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍ እንዲሁም ሕጋዊ ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ዘመናዊ የጉምሩክ ሕግ ማዕቀፍ ስራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

አገሪቱ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና አካባቢያዊ የንግድ ስምምነቶች ወቅታዊ የጉምሩክ ሕግና የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር የሚያስገድዱ በመሆናቸው፤

ኮንትሮባንድና ሌሎች የንግድ ማጭበርበር ወንጀሎች በሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴ፣ በሕዝብ ደህንነት፣ በመንግስት ገቢና በሌሎችም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቶች ላይ የሚያስከትሉትንና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል የተጠናከረ የሕግ ማስከበሪያ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 859/2014

## CUSTOMS PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to have an expedient and modern customs legal framework which encourages the development of manufacturing industries and investment compatible with the level of international trade practice;

WHEREAS, international, continental and regional trade agreements to which the country is a party require contemporary customs laws and procedures;

WHEREAS, strong system of law enforcement is required from time to time to prevent the increasing incidence of contraband and other commercial crimes which are resulting in negative impacts on legitimate trade, public security, government revenue and other social and economic development;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 89.15

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "ዕቃ" ማለት ማናቸውም ተንቀሳቃሽ ንብረት ሲሆን ግዙፍነት የሌላቸው በሕግ እንደተንቀሳቃሽ ንብረት የሚታወቁትን ንብረቶች፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን በአገልግሎት ላይ የዋሉ የተፈጥሮ ኃይልንና ሀብቶችን የሚያካትት ሲሆን ገንዘብን ይጨምራል፤

፪/ "ጭነት" ማለት በማናቸውም የማጓጓዣ ዓይነት ወደ አገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ዕቃ ሲሆን የንግድ ማጓጓዣ የጉዞ ዕቃ ክምችትንና የመንገደኞች ሻንጣዎችን አይጨምርም፤

፫/ "ቀረጥ" ማለት ይህን አዋጅና የዓለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓትን ተከትሎ በወጣው የጉምሩክ የታሪፍ ደንብ መሠረት በገቢና ወጪ እቃዎች ላይ የሚጣልና የሚሰበሰብ ክፍያ ነው፤

፬/ "ታክስ" ማለት ፀንተው በሥራ ላይ ባሉ የታክስ ሕጎች መሠረት በገቢና በወጪ ዕቃዎች ላይ እየተጣለ የሚሰበሰብ ክፍያ ነው፤

፭/ "ዕቃ ወደ አገር ማስገባት" ማለት ማናቸውንም ገቢ ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማምጣት ወይም እንዲገባ ማድረግ ነው፤

፮/ "ዕቃ ወደ ውጭ አገር መላክ" ማለት ማናቸውንም ዕቃ ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት ወይም እንዲወጣ ማድረግ ነው፤

፯/ "የጉምሩክ ክልል" ማለት የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ነው፤

፰/ "የጉምሩክ ጣቢያ" ማለት በመግቢያና በመውጫ ወደብ ወይም በመተላለፊያ መንገድ ወይም በጉምሩክ ክልል የሚገኝ በገቢና በወጪ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ቁጥጥርና ሥነ ሥርዓት የሚፈፀምበት እና ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ሥፍራ ነው፤

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Customs Proclamation No. 859/2014".

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "goods" means any kind of corporeal chattels and other incorporeal chattels deemed to be corporeal chattels by law including natural forces and resources of an economic value which are employed in use, and includes money;

2/ "cargo" means any goods imported or exported by any means of transport other than stores of means of transport for commercial use and baggage of travellers;

3/ "duty" means a charge levied and collected on any imported or exported goods in accordance with the Customs Tariff Regulations issued pursuant to this Proclamation and the International Convention on the Harmonized Commodity Description and Coding System;

4/ "tax" means payment collected in accordance with the existing tax laws on imported and exported goods;

5/ "importation" means bringing or causing to be brought goods into the customs territory;

6/ "exportation" means taking or causing to be taken out goods from the customs territory;

7/ "customs territory" means the territory of Ethiopia;

8/ "customs station" means any place designated as customs office at the port of entry or exit of goods, transit routes or customs area for the control of import and export goods or for accomplishment of customs formalities and collection of duties and taxes;

፱/ "የጉምሩክ መጋዘን" ማለት ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻን፣ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘንን እና የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘንን ይጨምራል፤

፲/ "ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ" ማለት፡-

ሀ) ገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ ስርዓት አፈጻጸም ተከናውኖባቸው እስከሚለቀቁ ወይም እንደሁኔታው ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ወይም ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እስኪዛወሩ፣ እና

ለ) ወጪ እና ተላላፊ እቃዎች አግባብነት ያለው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም እስከሚከናወንባቸው ወይም እንደሁኔታው ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ወይም ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እስከሚዛወሩ፣

በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆነው የሚቆዩበት ዝግ ወይም ክፍት የእቃ ማከማቻ ሥፍራ ሲሆን ደረቅ ወደብን ይጨምራል፤

፲፩/ "ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን" ማለት ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸውና የጉምሩክ ቁጥጥር እየተደረገባቸው የሚከማቹበት መጋዘን ሲሆን የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብሮችን እና ቦንድድ ፋብሪካዎችን ይጨምራል፤

፲፪/ "ቦንድድ ፋብሪካ" ማለት ጉምሩክ ቁጥጥር እየተደረገበት ለምርት አገልግሎት ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ጥሬ ዕቃዎችንና ግብዓቶችን በመጠቀም እቃዎችን የሚያመርት ፋብሪካ ነው፤

፲፫/ "የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን" ማለት የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ የተያዙ ወይም የተወረሱ እንዲሁም የተተው እቃዎች በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ እስከሚወገዱበት ጊዜ ድረስ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የሚከማቹበት መጋዘን ነው፤

፲፬/ "የመጋዘን ኃላፊ" ማለት የጉምሩክ መጋዘንን የሚያስተዳድር ሰው ነው፤

፲፭/ "ማጓጓዣ" ማለት በየብስ፣ በአየር ወይም በውሃ ላይ ሰውን ወይም ዕቃን የሚያጓጉዝ ማንኛውም የማጓጓዣ ዘዴ ሲሆን እንስሳትን፣ የኤሌክትሪክ መስመሮችንና የፈሳሽ ማስተላለፊያዎችን ይጨምራል፤

፲፮/ "አጓጓዥ" ማለት ዕቃን በማጓጓዝ ላይ ያለ ወይም የማጓጓዣውን እንቅስቃሴ የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው፤

9/ "customs warehouse" includes temporary customs storage, bonded customs warehouse and government customs warehouse;

10/ "temporary customs storage" means enclosed or open premises including dry ports, where:

a) import goods are stored under customs control until they are released upon completion of customs formalities or they are transferred to bonded customs warehouse or government customs warehouse, as the case may be; and

b) export and transit goods are stored under customs control until the completion of the applicable customs formalities or they are transferred to bonded customs warehouse or government customs warehouse, as the case may be;

11/ "bonded customs warehouse" means a warehouse under which goods are stored under customs control without payment of duties and taxes, and includes duty free shops and bonded factories;

12/ "bonded factory" means a factory which produces goods, under customs control, using raw materials and accessories acquired without payment of duty and taxes;

13/ "government customs warehouse" means a warehouse where goods seized or forfeited due to contravention of customs law as well as abandoned goods shall, be stored, while being under customs control, until they are sold or disposed otherwise;

14/ "warehouse operator" means a person who administers a customs warehouse;

15/ "means of transport" means any means of conveyance used for carriage of goods and travellers on land, air or water, and includes animals, electricity transmission lines and pipes used to transport liquids;

16/ "carrier" means the person actually transporting goods or responsible for the operation and control of the means of transport;

፲፯/ "የመተላለፊያ መሥመር" ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ገቢና ወጪ ዕቃዎች እንዲንጓዙበት በባለሥልጣኑ የተወሰነ ማናቸውም መንገድ ነው፤

፲፰/ "የጉምሩክ አስተላላፊ" ማለት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣ ደንብ መሠረት የጉምሩክ አስተላላፊነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲሆን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትን ለማስፈጸም የሚያስችል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በባለሥልጣኑ የተሰጠውን የዲክላራሲዮን አቅራቢ ሠራተኛ ይጨምራል፤

፲፱/ "ማጓጓዣ በመቀየር ዕቃን ማጓጓዝ" ማለት ዕቃን ጭኖ ወደ ጉምሩክ ወደብ ከገባ ማጓጓዣ ዕቃውን ከዚያው ወደብ ጭኖ ከአገር ወደሚወጣ ሌላ ማጓጓዣ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆኖ የሚተላለፍበት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ነው፤

፳/ "የዕቃ ዲክላራሲዮን" ማለት ወደ አገር የሚገቡ፣ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ወይም ተላላፊ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትና ለአፈጻጸሙ ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸውን ዝርዝሮች አስመልክቶ በዲክላራሲዮን አቅራቢ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚሰጥ መግለጫ ነው፤

፳፩/ "የዲክላራሲዮን አቅራቢ" ማለት የዕቃ ዲክላራሲዮን የሚያቀርብ ወይም የዕቃ ዲክላራሲዮን በስሙ የሚቀርብለት ማንኛውም ሰው ነው፤

፳፪/ "የጉምሩክ ሥነሥርዓት" ማለት የጉምሩክ ሕግን ለማክበር በሚመለከታቸው ሰዎችና በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የጉምሩክ ሂደቶችን ያጠቃልላል፤

፳፫/ "የኤሌክትሮኒክ ፊርማ" ማለት የኤሌክትሮኒክ መዝገቦች ወይም ሰነዶች ትክክለኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ በዚህ አዋጅ ወይም ተጠቃሚው በገባው ስምምነት ላይ በተቀመጡ መመዘኛዎች መሰረት ለተመዘገቡ ተጠቃሚዎች የሚፈቀድ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፤

፳፬/ "ለንግድ ዓላማ የማይውል ዕቃ" ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ በሚኒስቴሩ መመሪያ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ሆኖ ለአስመጪው ወይም ለባለይዞታው ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ ወይም ፍጆታ የሚውል ዕቃ ወይም የስጦታ ቁሳቁስ ነው፤

፳፭/ "ሰነድ" ማለት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀምን ለማከናወን በአካል ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የሚቀርብ ማናቸውም ሰነድ ነው፤

፳፮/ "የዋጋ ሰነድ" ማለት በአምራች ወይም በአቅራቢ የተሰጠ ስለዕቃ ዋጋ የሚገልፅ ሰነድ ነው፤

17/ "transit route" means any route designated by the Authority for the movement of imported or exported goods under customs control;

18/ "customs clearing agent" means a person issued with customs clearing agent license pursuant to regulation issued hereunder and includes an employee of a declarant issued, by the Authority, with a certificate of professional competence in respect of customs clearance;

19/ "transshipment" means the customs procedure under which goods are transferred under customs control from the importing means of transport to the exporting means of transport within the area of one customs port which is the port of both importation and exportation;

20/ "goods declaration" means a statement made in accordance with the provisions of this Proclamation, by which the declarant indicate the customs procedure to be applied to import, export or transit goods and furnish the particulars which the Authority requires for its application;

21/ "declarant" means any person who makes a goods declaration or in whose name such a declaration is made;

22/ "customs procedure" means all customs operations which shall be carried out by the persons concerned and by the Authority in order to comply with customs law;

23/ "electronic signature" means a digital signature allowed to a registered user for authentication of electronic records in conformity with the requirements prescribed in this Proclamation and user agreement;

24/ "non-commercial goods" means goods that are intended for the personal or family use of the consignee or persons carrying them, or which are clearly intended as gifts and the aggregate value or quantity of which does not exceed the amounts laid down in directive issued by the Ministry;

25/ "document" means any document presented physically or by electronic means to the Authority to complete customs formalities;

26/ "invoice" means a document issued by a manufacturer or supplier which shows the price of goods;

፳፯/ "አንድ ዓይነት ዕቃዎች" ማለት በአካላዊ ባህሪያቸው፣ በጥራታቸውና በተፈላጊነታቸው አንድ የሆኑና በአንድ አገር የተመረቱ ዕቃዎች ናቸው፤

፳፰/ "ተመሳሳይ ዕቃዎች" ማለት በሁሉም አንጻር ባይመሳሰሉም ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው፣ ከተመሳሳይ ማቴሪያል የተመረቱ፣ ተመሳሳይ ተግባር ማከናወን የሚችሉና ተመሳሳይ የገበያ ተፈላጊነት ያላቸው ዕቃዎች ሲሆኑ ጥራታቸው፣ በአንድ አገር የተመረቱ መሆናቸው፣ ተፈላጊነታቸውና የንግድ ምልክታቸው ስለተመሳሳይነታቸው ከግምት ውስጥ ይገባል፤

፳፱/ "ዕቃ ማስወገድ" ማለት ማናቸውንም ዕቃ በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ ወይም በማቃጠል ወይም በሌላ መንገድ እንዲወድም ማድረግ ነው፤

፴/ "የተከለከለ ዕቃ" ማለት በኢትዮጵያ ሕግ ወይም ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ወደ አገር እንዳይገባ፣ ከአገር እንዳይወጣ ወይም እንዳይተላለፍ የተከለከለ ማንኛውም ዕቃ ነው፤

፴፩/ "ገደብ የተደረገበት ዕቃ" ማለት በሕግ በተደነገገ ሥነ ሥርዓት መሠረት ሥልጣን ባለው አካል በተሰጠ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ወደ አገር እንዳይገባ ወይም ከአገር እንዳይወጣ ወይም እንዳይተላለፍ ገደብ የተደረገበት ዕቃ ነው፤

፴፪/ "የጭነት መግለጫ" ማለት የዕቃ ላኪን፣ ተቀባይን፣ ምልክትን፣ ዕሽግ ቁጥርን፣ ዓይነትን፣ ብዛትን፣ ክብደትን፣ የጭነት ዲክላራሲዮን ቁጥርንና የመሳሰሉትን ዝርዝሮች የሚያመለክት ሰነድ ነው፤

፴፫/ "ማካካሻ ምርት" ማለት ያምርት ሂደቱ በአገር ውስጥ ተጠናቆ እንዲወጣ ወይም የምርት ሂደቱ በውጭ አገር ተጠናቆ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባና ለነጻ ዝውውር እንዲለቀቅ በተፈቀዱ አሰራሮች መሰረት የተመረተ ወይም ጥገና የተደረገበት ምርት ነው፤

፴፬/ "የስሪት አገር የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ ዕቃ ስለተመረተበት አገር ትክክለኛነት በተመረተበት አገር ሥልጣን ባለው አካል የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰነድ ነው፤

፴፭/ "የስሪት አገር አወሳሰን ድንጋጌዎች" ማለት በዓለም አቀፍ፣ በአካባቢያዊ ወይም በሁለትዮሽ የንግድ ስምምነቶች መሠረት ዕቃዎች የተሠሩበትን አገር ለመወሰን የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓትና መመዘኛ ነው፤

፴፮/ "ኮንቴይነር" ማለት ዕቃን ለመያዝ የተሰራ፣ ለተደጋጋሚ አገልግሎት የሚውልና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ

27/ "identical goods" means goods which are the same in all respects including physical characteristics, quality, reputations and country of origin;

28/ "similar goods" means goods which, although not alike in all respects, have like characteristics, and component materials, perform the same functions and to be commercially interchangeable; and the quality, origin, reputation and the trade mark of which are among the factors to be considered in determining their similarity;

29/ "disposal of goods" means transferring of goods through sale, donation or by any other means or the act of destroying goods by way of burning or otherwise;

30/ "prohibited goods" means goods of which the importation, exportation or transit is prohibited by Ethiopia law or international agreement ratified by Ethiopia;

31/ "restricted goods" means goods which the importation, exportation or transit is restricted unless it is permitted by the competent authority in accordance with legal procedures;

32/ "cargo manifest" means a document which indicate the consignor, consignee, mark, package number, quality, quantity, weight, cargo declaration number and other particulars of goods;

33/ "compensating product" means product manufactured, processed or repaired abroad or at home, as the case may be, by inward or outward processing;

34/ "certificate of origin" means a document issued by a competent authority in the exporting country certifying the authenticity of the origin of goods;

35/ "rules of origin" means a procedure and criteria put in place to determine the origin of goods in accordance with international, regional or bilateral trade agreements;

36/ "container" means a receptacle which is either flat or open or fully or partially enclosed for containing goods and suitable for repeated use,

በሆነ የመጓጓዣ ዓይነት ዕቃን በቀላሉ ለማጓጓዝ እንዲቻል ተደርጎ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ ዝርግ፣ ክፍት ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ዝግ የሆነ የዕቃ መያዣ ነው፤

፴፯/ "የጉምሩክ ትራንዚት" ማለት ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆነው ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ የሚተላለፉበት የጉምሩክ ሥነሥርዓት ነው፤

፴፰/ "የጉምሩክ ቁጥጥር" ማለት የጉምሩክ ህግ መከበሩን ለማረጋገጥ በባለሥልጣኑ የሚወሰድ ማናቸውም እርምጃ ነው፤

፴፱/ "የጉምሩክ ሕግ" ማለት ይህንን አዋጅ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን እና ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች ህጎች ያጠቃልላል፤

፵/ "የጉምሩክ ወደብ" ማለት ለጉምሩክ ህግ አፈፃፀም ሲባል የገቢ፣ የወጪ ወይም ተላላፊ ወይም ማጓጓዣ ቀይረው የሚወጡ ዕቃዎች የሚራገፉበት፣ የሚቆዩበትና የሚጫኑበት በባለሥልጣኑ የሚወሰን ማናቸውም ስፍራ ሲሆን ደረቅ ወደብና በባለሥልጣኑ የሚወሰኑ ሌሎች ቦታዎችን ይጨምራል፤

፵፩/ "የዕቃ ምርመራ" ማለት የዕቃውን የስሪት አገር፣ የመጣበትን አገር፣ ባህሪ፣ ሁኔታ፣ አይነት፣ ብዛት፣ ዋጋና የታሪፍ አመዳደብ በዕቃ ዲክላራሲዮን ቅጽ ውስጥ በቀረበው ዝርዝር መሠረት የተሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ በጉምሩክ ሹም የሚፈፀም አካላዊ ምርመራ ሲሆን በመንገደኞች የሻንጣ ዲክላራሲዮን መሠረት የሚደረግ የዕቃ ምርመራን ይጨምራል፤

፵፪/ "የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር" ማለት ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ክፍያ ነፃ የሆነ ዕቃ ለዓለም አቀፍ መንገደኞችና ለሌሎች የቀረጥ ነፃ ባለመብቶች የሚሸጥበት በዓለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሌሎች ቦታዎች በባለሥልጣኑ ፈቃድ በተሰጣቸው ሰዎች የሚቋቋም መደብር ነው፤

፵፫/ "የጉምሩክ ማቋረጫ" ማለት ሰውንና ማጓጓዣን እንዲሁም የገቢ፣ የወጪና ተላላፊ ዕቃዎችን ለማስገባት፣ ለማስወጣትና ለማሸጋገር የተፈቀደ የድንበር መስመር ሲሆን ዓለም አቀፋዊ የድንበር ትራፊክ እንቅስቃሴ የሚፈፀምባቸውን ሥፍራዎች ይጨምራል፤

፵፬/ "የጉምሩክ የጠረፍ መስመር" ማለት ከኢትዮጵያ የጉምሩክ ድንበር መስመር ወደ ውስጥ እስከ ፲፭ ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ የሚገኝ ሥፍራ ነው፤

and specially designed to facilitate the carriage of goods by one or more mode of transport;

37/ "customs transit" means customs procedures under which goods are transported under customs control from one customs office to the other;

38/ "customs control" means any measure applied by the Authority to ensure compliance with customs law;

39/ "customs law" includes this Proclamation, regulations and directives issued hereunder and other laws enforced by the Authority;

40/ "customs port" means any place that is designated by the Authority for unloading, storage and loading of import, export and transit goods for the purpose of enforcing customs laws and includes dry port;

41/ "examination of goods" means the physical examination of goods by customs officer to satisfy that the origin, country of export, nature, condition, quality, quantity, tariff classification and value of the goods are in accordance with particulars furnished in the goods declaration and includes examination of goods on the basis of baggage declarations by travellers;

42/ "duty free shop" means a shop established, upon the authorization of the Authority, in international airports or, where necessary, in other places in which duty and tax free goods are sold to international travellers and other duty free privileged persons;

43/ "customs crossing" means a designated point of crossing of the customs boundary line for persons and means of transport as well as for import, export and transit goods, and includes international border traffic routes;

44/ "customs frontier strip" means a 15 kilometres wide part of the customs territory from the customs boundary line of Ethiopia;

፵፭/ "የሥጋት ሥራ አመራር" ማለት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ፣ በሚወጡና በሚተላለፉ እቃዎች ላይ አገልግሎት አሰጣጡንና የቁጥጥር ሥርዓቱን ሚዛናዊ ባደረገ ሁኔታ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሠረት የተለያየ የሥጋት ደረጃ በማውጣት የሚከናወን የአሠራር ሥርዓት ነው፤

፵፮/ "ዕቃን መልቀቅ" ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያለ ዕቃ ለተገለፀለት ዓላማ እንዲውል የሚለቀቅበት ሥርዓት ነው፤

፵፯/ "የጉምሩክ ሹም" ማለት የጉምሩክ ሥራን በሃላፊነት እንዲያከናውን የተመደበ ሃላፊ ወይም ሰራተኛ ሲሆን የምርመራ ሹምን ይጨምራል፤

፵፰/ "መያዝ" ማለት የጉምሩክ ሕግን ከማስከበር ጋር በተያያዘ ዕቃን ወይም ሰነድን በቁጥጥር ስር ማድረግ ነው፤

፵፱/ "በሕጋዊ ዕቃ ከለላነት መጠቀም" ማለት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ከቀረበበት ዕቃ ጋር በዓይነት፣ በመጠን፣ በብዛት፣ በዋጋ ወይም በሥሪት አገር ልዩነት ያለውን ዕቃ የመቀላቀል ድርጊት ነው፤

፶/ "መንገደኛ" ማለት፦

ሀ) መደበኛ መኖሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ ያልሆነና ወደ አገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ፤ ወይም

ለ) መደበኛ መኖሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ከአገር የሚወጣ ወይም ወደ አገር የሚመለስ፤

ሰው ነው፤

፶፩/ "የተተወ ዕቃ" ማለት የዕቃው ባለቤት በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ ሥነሥርዓትን አጠናቆ ያልተረከበው ዕቃ ነው፤

፶፪/ "የግል መገልገያ" ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ በሚኒስቴሩ መመሪያ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ሆኖ መንገደኛ የሚይዘው ዕቃ ነው፤

፶፫/ "የጉምሩክ ወንጀል" ማለት ከመደበኛ ስራው ጋር በተያያዘ የጉምሩክ ሹም ከሚፈፅመው ጥፋት ውጪ በማንኛውም ሰው የሚፈፀሙ በዚህ አዋጅ ክፍል ሰባት ምዕራፍ ሁለት የተዘረዘሩት ጥፋቶች ናቸው፤

፶፬/ "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ነው፤

፶፭/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፤

45/ "risk management" means a system of management by which different risk bands are categorized on the basis of their risk levels in light of fair customs service provision and control with respect to goods brought to or taken out of customs territory;

46/ "release of goods" means a procedure whereby goods under customs control are released for the purposes declared;

47/ "customs officer" means an official or employee assigned to discharge customs operations and includes an investigation officer;

48/ "seizure" means taking possession of goods or documents in relation with enforcement of customs law;

49/ "under the cover of legally declared goods" means the act of intermingling of goods that are different in type, size, quantity, value or country of origin with the declared goods;

50/ "traveller" means a person:

a) who is not a domiciliary of Ethiopia and who enters or leaves the territory of Ethiopia; or

b) who is a domiciliary of Ethiopia and who leaves or returns to Ethiopia;

51/ "abandoned goods" means goods that are not collected by their owner within the period prescribed by law completing customs procedures;

52/ "personal effects" means articles which a traveller may require for his personal use and the aggregate value or quantity of which does not exceed the amounts laid down in directive issued by the Ministry;

53/ "customs crime" means offences provided under Part Seven Chapter Two of this Proclamation but not include offences committed by customs officer in executing his duties;

54/ "Ministry" means the Ministry of Finance and Economic Development;

55/ "Authority" means the Ethiopian Revenues and Customs Authority;

፶፮/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፶፯/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ በመላው የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ፣ ከጉምሩክ ክልል በሚወጡ፣ በጉምሩክ ክልል በሚተላለፉና የጉምሩክ ቁጥጥር በሚደረግባቸው ዕቃዎች እንዲሁም ከጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ጋር በተያያዘ መብት በተሰጣቸውና ግዴታ በተጣለባቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ፬. ወደ አገር እንዳይገቡና ከአገር እንዳይወጡ ስለተከለከሉ ወይም ገደብ ስለተደረገባቸው ዕቃዎች

፩/ ማንኛውም ሰው የተከለከሉ ዕቃዎችን ወደ አገር ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት ወይም ማስተላለፍ አይችልም።

፪/ ማንኛውም ሰው ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች የተጣለው ገደብ የሚጠይቃቸውን መሥፈርቶች ካላሟላ በስተቀር ወደ አገር ማስገባት፣ ከአገር ማስወጣት ወይም ማስተላለፍ አይችልም።

## ክፍል ሁለት

## የጉምሩክ አሰራር መርሆዎች

## ፭. ጠቅላላ

የጉምሩክ አሰራር፦

፩/ አስመጪዎችና ላኪዎች በራሳቸው አነሳሽነት የዕቃዎችን ዋጋ እንዲሁም የቀረጥና ታክስ ስሌት መግለጫ በማቅረብ ራሳቸው ወስነው ቀረጥና ታክስ የሚከፍሉበትን ስርዓት ማጐልበት፤

፪/ የሥጋት ሥራ አመራር መርህን በተከተለ ሁኔታ ለተቀላጠፈ የንግድ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲሁም ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ ፍትሐዊ፣ ፈጣን፣ ተገማች እና አመኔታን ያተረፈ የጉምሩክ አገልግሎት በመስጠትና የጉምሩክ ቁጥጥር በማካሄድ ረገድ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራርን ማስፈን፤

፫/ የአምራች ኢንዱስትሪን እና የኢኮኖሚ ልማትን መደገፍ፤

፬/ ለተገልጋዮች ግልጽ መረጃን መስጠት እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስፈርትን የተከተለና ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር በመደጋገፍና በመመካከር የተደራጀ መረጃ መሰብሰብ፣

56/ "person" means any natural or juridical person;

57/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

1/ This Proclamation shall be applied in the entire territory of Ethiopia.

2/ Without prejudice to the provision of sub-article (1) of this Article, this Proclamation shall regulate import goods, export goods, goods in transit and any goods subject to customs control including rights and obligations of persons who takes part in customs formalities.

## 4. Prohibited or Restricted Imports and Exports

1/ No person may import, export or transit prohibited goods.

2/ No person may import, export or transit restricted goods unless in compliance with the requirements of the restriction.

## PART TWO

## PRINCIPLES OF CUSTOMS OPERATIONS

## 5. General

The customs operations shall:

1/ promote a self-assessment system whereby importers and exporters present the value of goods and pay duties and taxes by themselves;

2/ be based on the principles of risk management, transparency and accountability and create a conducive environment to provide equitable, expeditious, predictable and reliable services in the exercise of customs control;

3/ promote and support manufacturing industry and economic development;

4/ provide clear information to the customers and be based on the use of internationally accepted information technology systems through which information is gathered, analysed, used and stored in the course of cooperation and

መተንተን፣ መጠቀምና መጠበቅ፤ እና

፭/ ህግ አክባሪነትን በማበረታታት ህገ ወጥነትን መከላከል፤

የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

## ፮. የስጋት ስራ አመራር

፩/ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የጉምሩክ አገልግሎት እና የሚከናወን የቁጥጥር ስርዓት በመረጃ በተደገፈ መመዘኛ የገቢ፣ የወጪ እና የተላላፊ እቃዎችን የስጋት ደረጃ በመለየት የአገልግሎት አሰጣጥን እና የቁጥጥር ስርዓቱን ሚዛናዊነት ጠብቆ የሚከናወን ይሆናል፡፡

፪/ የዕቃ አወጣጥን፣ ቁጥጥርን፣ የሕግ ተገዥነትን እንዲሁም አገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ ተግባራት እና ባለሥልጣኑ የሚወስናቸው ውሳኔዎች የስጋት ስራ አመራርን መሰረት ያደረጉ ይሆናሉ፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የስጋት ስራ አመራርን መሰረት በማድረግ በተሰጠ አገልግሎት ላይ የታዩ የሕግ ጥሰቶችን በመለየት ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ኦዲትን እና ሌሎች የቁጥጥር ስልቶችን መሠረት ያደረገ ቁጥጥር ተግባራዊ እንዲደረግ ሊወስን ይችላል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ የገቢ፣ የወጪና ተላላፊ እቃዎችን በሚመለከት የሚኖር የስጋት ደረጃን የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

## ፯. በጉምሩክ አሰራር ተቀባይነት ያገኘ የዕቃ አያያዝ ወይም አጠቃቀም

፩/ በዕቃው ባህሪ፣ ብዛት፣ የሥሪት አገር፣ በመድረሻ ሥፍራው ወይም በአላላክ ሁኔታው ላይ ልዩነት ሳይደረግ በዚህ አዋጅ መሠረት በተቀመጡ መስፈርቶች በጉምሩክ አሰራር ተቀባይነት ያገኘ የዕቃ አያያዝ ወይም የአጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የዕቃ አያያዝ ወይም አጠቃቀም ከሕዝብ ሞራል አጠባበቅ፣ ከሰዎች፣ ከእንስሳት ወይም ከዕፅዋት ጤንነትና ሕይወት አጠባበቅ፣ ከታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች አጠባበቅ ወይም በሌላ ሕግ ከተፈቀደ የዕቃዎች አያያዝ ወይም አጠቃቀም ጋር የሚቃረን ከሆነ በሥራ ላይ አይውልም፡፡

consultation among concerned bodies;

5/ prevent illegal practices by promoting self-compliance.

## 6. Risk Management

1/ The customs facilitation service and control shall classify the risk level of import, export and transit goods and be carried out with striking balance between facilitation and control which shall be based on a criteria substantiated by information.

2/ Activities performed and decisions passed by the Authority with respect to release of goods, control, compliance management and facilitation shall take the principles of risk management into account.

3/ The Authority may employ audit based control and other methods of control to take appropriate measures on such irregularities identified after decision on facilitation is provided in accordance with principles of risk management.

4/ The Authority shall issue directive regarding the risk level of import, export and transit goods.

## 7. Customs Approved Treatment or Use of Goods

1/ Customs approved treatment or use of goods shall be applied in accordance with standards prescribed by this Proclamation without any discrimination as to the nature, quantity, origin, and destination or shipment conditions of the goods.

2/ Sub-article (1) of this Article may not be applicable if such application is contrary to any measure taken for the protection of public morality, the protection of health and life of humans, animals or plants, the protection of historical and cultural heritages, or other specific treatment or use of goods provided by law.

## ክፍል ሦስት
## የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

### ምዕራፍ አንድ
### የዕቃ ዲክላራሲዮን

**፰. ዲክላራሲዮን አቅራቢ**

፩/ በዕቃው ላይ የማዘዝ መብት ያለው ማንኛውም ሰው ዲክላራሲዮን አቅራቢ የመሆን እንዲሁም በጉምሩክ አስተላላፊ የመወከል መብት ይኖረዋል።

፪/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዕቃው ዲክላራሲዮን ውስጥ ለሰፈሩት ዝርዝሮች መሟላትና ትክክለኛነት እንዲሁም ለቀረጥና ታክስ ክፍያው ተጠያቂነት ይኖርበታል።

፫/ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቅራቢው የዕቃውን ዲክላራሲዮን ከማቅረቡ በፊት በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰነውን ሁኔታ ተከትሎ ዕቃውን ለመመርመርና ናሙና ለመውሰድ ይፈቀድለታል።

፬/ የተወሰደ ናሙና ለሚመለከተው ጭነት በቀረበው የዕቃ ዲክላራሲዮን ውስጥ እስከተካተተ ድረስ የተለየ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብበት አይደረግም።

**፱. የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብ**

፩/ የዕቃ ዲክላራሲዮን በቃል፣ በአካል እንቅስቃሴ፣ በፅሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ሊቀርብ ይችላል።

፪/ በፅሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚቀርብ ዲክላራሲዮን ለዚሁ ተብሎ በባለሥልጣኑ በተዘጋጀ ቅጽ መሞላት፣ መፈረምና ለጉምሩክ ፎርማሊቲ አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝሮችን ብቻ መያዝ አለበት።

**፲. የዕቃ ዲክላራሲዮን ደጋፊ ሰነዶች**

፩/ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የዕቃ ዲክላራሲዮን በሚቀርብበት ጊዜ አስፈላጊነቱ በባለሥልጣኑ የሚወሰን ሆኖ የሚከተሉት ደጋፊ ሰነዶች ዋና ቅጂዎቻቸው ወይም የኤሌክትሮኒክስ ቅጂዎቻቸው በአባሪነት መቅረብ አለባቸው፦

ሀ) የማጓጓዣ ሰነድ፤

ለ) የዋጋ ሰነድ፤

ሐ) የባንክ ፈቃድ፤

መ) የዕቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ፤

ሠ) የስሪት አገር የምስክር ወረቀት፤ እና

## PART THREE
## CUSTOMS PROCEDURE

### CHAPTER ONE
### GOODS DECLARATION

**8. Declarant**

1/ Any person having the right to dispose of the goods shall be entitled to act as declarant, and shall be entitled to be represented by a customs clearing agent.

2/ The declarant shall be held responsible for the completeness and accuracy of the particulars given in the goods declaration and the payment of the duties and taxes.

3/ Before lodging the goods declaration the declarant shall be allowed, under such conditions as may be laid down in a directive issued by the Authority, to inspect the goods and to draw samples.

4/ A separate goods declaration may not be required in respect of samples allowed to be drawn, provided that such samples are included in the goods declaration concerning the relevant consignment.

**9. Forms of Goods Declaration**

1/ Goods declaration may be made in writing form, orally, by bodily action or electronically.

2/ Goods declaration to be presented in written form or electronically shall be filled and signed in the form prescribed by the Authority and shall contain the particulars only necessary for completing customs formalities.

**10. Supporting Documents of Goods Declaration**

1/ On the presentation of goods declaration made in written or electronic form, original copies of the following supporting documents or electronic copies shall be submitted as required by the Authority:

a) transportation document;

b) invoice;

c) bank permit;

d) packing list;

e) certificate of origin; and

ረ) ከጉምሩክ ህግ መከበር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁኔታዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በቂ ምክንያት ሲቀርብለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ደጋፊ ሰነዶች ቅጂ ብቻ ሊቀበል ይችላል፡፡

፫/ ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ የሚጠየቀው የማጓጓዣ ሰነድ ዕቃውን ከኢትዮጵያ መውጫ እስከሆነው የጉምሩክ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝ የወጣውን ወጪ የሚያሳይ የአገር ውስጥ ማጓጓዣ ሰነድ ነው፡፡

፬/ በአባሪነት የሚቀርቡ ሰነዶችን በበቂ ምክንያት በወቅቱ ማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ ባለሥልጣኑ ተገቢውን ዋስትና በመጠየቅ ሰነዶቹ በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ በሚወሰን ጊዜ ውስጥ እንዲቀርቡ በመፍቀድ አገልግሎቱን ሊሰጥ ይችላል፡፡

፭/ የዕቃ ዲክላራሲዮን ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ ከዲክላራሲዮኑ ጋር አባሪ ሆነው የቀረቡ ሰነዶችና ዲክላራሲዮኑ እንደ አንድ የማይነጣጠል ሕጋዊ ሰነድ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ በውጭ አገር ቋንቋ የቀረበ ደጋፊ ሰነድ በህጋዊ ተርጓሚ ወደ አማርኛ ወይም ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉሞ እንዲቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡

## ፲፩.ጊዜያዊ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ ስለመፍቀድ

፩/ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቅራቢ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባለው ምክንያት የዕቃ ዲክላራሲዮኑን ለመሙላት የሚያስችል የተሟላ መረጃ ከሌለውና ያለው መረጃም የጉምሩክ ቀረጡን ለመወሰን የሚያስችል ከሆነ የተሟላውን የዕቃ ዲክላራሲዮን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማቅረብ የዋስትና ግዴታ እንዲገባ በማድረግ ጊዜያዊ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ ይፈቀድለታል፡፡

፪/ ጊዜያዊ የእቃ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ ባለሥልጣኑ ሲፈቅድ የቀረጥና ታክስ አወሳሰኑ የተሟላና ትክክለኛ ዲክላራሲዮን መጀመሪያውኑ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ከሚኖረው አፈጻጸም የተለየ አይሆንም፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን መመሪያ ያወጣል፡፡

f) other documents necessary to ensure compliance with customs laws and prescribed by directive issued by the Authority.

2/ Where there are adequate reasons, the Authority may accept only copies of the supporting documents listed under sub article (1) of this Article.

3/ Transportation documents that are required in support of export goods shall be a document that is used as evidence for the cost of transportation of goods up to the customs port of exit.

4/ Where supporting documents cannot be presented to customs on time for adequate reasons, the Authority may, upon requiring a guarantee, allow the documents to be presented within the time to be specified by directive of the Authority after providing the service.

5/ Supporting documents and goods declaration shall constitute a single indivisible legal instrument upon acceptance of the declaration.

6/ The Authority may require any supporting document presented in a foreign language to be translated into Amharic or into English by an official translator.

## 11. Allowing Provisional Goods Declaration

1/ Where, for reasons deemed valid by the Authority, the declarant does not have all the information required to make the goods declaration, a provisional goods declaration shall be allowed to be lodged, provided that it contains the particulars deemed necessary by the Authority for the assessment of customs duties and that the declarant undertakes to produce final goods declaration within a specified period.

2/ If the Authority allows the presentation of a provisional goods declaration, the tariff treatment to be accorded to the goods may not be different from that which would have been accorded had a complete and correct goods declaration been lodged in the first instance.

3/ The Authority shall issue directive for the proper application of the provisions of sub-article (1) of this Article.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም ዲክላራሲዮኑ ከተመዘገበ በኋላ ለማጭበርበር በማሰብ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የተፈጸመ ግድፈት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የዕቃ ዲክላራሲዮን ያልተቀበለው ከሆነ ምክንያቱን በፅሑፍ ለዲክላራሲዮን አቅራቢው መግለጽ አለበት፡፡

## ፲፬.ዲክላራሲዮን ስለማሻሻል

፩/ የዕቃ ዲክላራሲዮን ከተመዘገበ በኋላ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዲክላራሲዮኑ ውስጥ ከተዘረዘሩት መግለጫዎች መካከል አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን ሊያሻሽል ይችላል፡፡ ሆኖም የሚደረገው ማሻሻያ አስቀድሞ መግለጫ ለተሰጠባቸው ዕቃዎች ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ዕቃዎች ላይ ዲክላራሲዮኑ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚያደርግ አይሆንም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ባለስልጣኑ ሰነዶቹን ወይም ዕቃዎቹን እንደሚፈትሽ ለዲክላራሲዮን አቅራቢው ካስታወቀው ወይም በቀረበው የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ውስጥ የሰፈሩት ዝርዝሮች ትክክለኛ አለመሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ በቂ በሆነ ምክንያት ላይ ተመሥርቶ ባለሥልጣኑ ካልፈቀደ በስተቀር ማሻሻያ ማድረግ አይፈቀድም፡፡

## ፲፭.ዲክላራሲዮንን ስለመሠረዝ

፩/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራሲዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ ፭ የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ካልጀመረ ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል፡፡

፪/ የዕቃ ዲክላራሲዮን የቀረበው በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ወይም ከጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ውጪ መሆኑ እና ክፍያ ያለመፈፀሙ ከተረጋገጠ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ሊሰረዝ ይችላል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ዕቃው ከተለቀቀ በኋላ የሚቀርብ የዲክላራሲዮን ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ በቂ ምክንያት ሲኖረው ቀረጥና ታክሱ ከመከፈሉ በፊት ዲክላራሲዮን እንዲሰረዝ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲሰረዝ መፍቀድ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዚህ አዋጅ መሠረት ሊፈጸምበት የሚችልን ቅጣት አያስቀርም፡፡

4/ Notwithstanding the provision of sub-article (3) of this Article errors committed, after presentation of goods declaration, with fraudulent intent or gross negligence shall entail penalty in accordance with this Proclamation.

5/ When the Authority rejects the goods declaration, it shall state the reasons to the declarant in writing.

## 14. Amendment of Declaration

1/The declarant may amend one or more of the particulars of a goods declaration already presented; provided, however, that such amendment may not have the effect of rendering the declaration applicable to goods other than those originally declared.

2/ Notwithstanding the provisions of sub article (1) of this Article, any amendment may not be made, unless authorized by the Authority for good cause, after the Authority has informed the declarant that it intends to examine the documents or goods or it has established that the particulars are incorrect.

## 15. Cancellation of Declaration

1/ Where the declarant fails to proceed with the customs formalities within five working days after the presentation of a goods declaration or after completion of the preparation of an assessment notice, the goods declaration may be cancelled.

2/ Goods declaration may be cancelled upon the request of the declarant, where it is proved that the declaration has been presented contrary to the provisions of this Proclamation or any appropriate customs procedure and payment has not yet been effected.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, the request for cancellation may not be permitted after release of the goods.

4/ The Authority may allow cancellation of the goods declaration on good cause prior to the payment of the duty and tax.

5/ Allowing the cancellation of goods declaration pursuant to this Article may not exonerate the declarant from a penalty that may be imposed in accordance with this Proclamation.

## ምዕራፍ ሁለት

## የጉምሩክ ትራንዚት እና ማጓጓዣ በመቀየር ዕቃን የማጓጓዝ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

### ፲፮. ጠቅላላ

፩/ ባለሥልጣኑ ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው በጉምሩክ ክልል ውስጥ፡-

ሀ) ከመግቢያ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ መዉጫ የጉምሩክ ጣቢያ፤

ለ) ከመግቢያ የጉምሩክ ጣቢያ አገር ውስጥ ወደሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ፤

ሐ) በአገር ውስጥ ከሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ መውጫ የጉምሩክ ጣቢያ፤ ወይም

መ) በአገር ውስጥ ከሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ አገር ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ፤

እንዲጓጓዙ ይፈቅዳል፡፡

፪/ በባለሥልጣኑ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች እስከተሟሉና የሚያስፈልገው ዋስትና እስከቀረበ ድረስ በጉምሩክ ትራንዚት የሚጓጓዝ ዕቃ ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡

፫/ የጉምሩክ ትራንዚት ዕቃዎች በባለሥልጣኑ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ተከብረውና ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ ጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያ ስለመድረሳቸው ዲክላራሲዮን አቅራቢውና አጓጓዡ በጋራና በተናጠል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ በመመሪያ የወሰናቸው ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ፡-

ሀ) የዕቃ ተቀባይ ዕቃውን ወደ ጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ ወደ ራሱ የሥራ ቦታ መጥቶለት እንዲረከብ፤ ወይም

ለ) የዕቃ ላኪ ዕቃውን ወደ መነሻ የጉምሩክ ጣቢያ ማቅረብ ሳያስፈልገው ከራሱ የሥራ ቦታ በቀጥታ መላክ እንዲችል፤

ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

### ፲፯. የጉምሩክ ትራንዚት ዕቃ ዲክላራሲዮን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪(፩) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ተፈላጊ ዝርዝሮችን በግልጽ ያካተተ የንግድ ወይም የማጓጓዣ ሰነድ እንደ ጉምሩክ ትራንዚት ዕቃ ዲክላራሲዮን ገላጭ ክፍል ሆኖ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል፡፡ በዚህ አይነት ተቀባይነት ማግኘቱም በሰነዱ ላይ መገለጽ አለበት፡፡

## CHAPTER TWO

## CUSTOMS TRANSIT AND TRANSHIPMENT

### 16. General

1/ The Authority shall allow goods to be transported under customs control in the customs territory:

a) from a customs station of entry to a customs station of exit;

b) from a customs station of entry to an inland customs station;

c) from an inland customs station to a customs station of exit; or

d) from one inland customs stations to another inland customs station.

2/ Goods being carried under customs transit may not be subject to the payment of duties and taxes, provided the conditions laid down by the Authority are complied with and that any security required has been furnished.

3/ The declarant and the carrier shall jointly and severally be responsible for ensuring that the goods are produced intact at the customs station of destination in accordance with the conditions imposed by the Authority.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Authority may, when it is satisfied that the conditions laid down by its directive are met, authorize:

a) a consignee to receive goods directly at his premises without having to present them at the customs station of destination; or

b) a consignor to send goods directly from his premises without having to present them at the customs station of departure.

### 17. Goods Declaration for Customs Transit

Notwithstanding the provisions of Article 12(1) of this Proclamation, any commercial or transport document setting out clearly the necessary particulars may be accepted as the descriptive part of the goods declaration for customs transit and such acceptance shall be noted on the document.

፭/ ጭነቱ በጉምሩክ ማሸጊያ ታሽጎ መጓጓዝ የሚገባው ሆኖ ሳለ ነገር ግን የማጓጓዣው የተወሰነ ክፍል በአግባቡ ሊታሸግ የማይችል ከሆነ ዕቃውን በሚገባ ለመለየትና ያልተፈቀደ ጣልቃ ገብነት ቢኖር በቀላሉ ለማወቅ፡-

ሀ) የዕቃው ሙሉ ምርመራ መደረግና ውጤቱም በጉምሩክ ትራንዚት ሰነዱ ላይ መመዝገብ፤

ለ) እያንዳንዱ የዕቃ እሽግ በጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ማሠሪያ መታሸግ ወይም መታሰር፤

ሐ) በናሙና፣ ፕላን፣ ንድፍ፣ ፎቶግራፍ ወይም ተመሳሳይ ዘዴ የተደገፈ የዕቃው ትክክለኛ መግለጫ ከጉምሩክ ትራንዚት ሰነዱ ጋር መያያዝ፤

መ) ዕቃው የሚጓጓዝበት የማያወላውል የጉዞ መስመርና የመድረሻ ጊዜ ገደብ መወሰን፤ ወይም

ሠ) ዕቃው በጉምሩክ ታጅቦ እንዲጓጓዝ መደረግ፤

አለበት፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ፊደል ተራ (መ) መሠረት የሚወስነው የጊዜ ገደብ የጉምሩክ ትራንዚቱን ለመፈጸም የሚያስችል በቂ ጊዜ መሆን አለበት፡፡ የጊዜ ገደቡም በዲክላራሲዮን አቅራቢው ወይም በአጓጓዡ ሲጠየቅና ተቀባይነት ያለው ምክንያት መኖሩ በባለሥልጣኑ ሲታመን ሊራዘም ይችላል፡

፯/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ፊደል ተራ (መ) ወይም (ሠ) መሠረት ዕቃው የሚጓጓዝበትን የማያወላውል የጉዞ መስመር እንዲከተል ወይም በጉምሩክ ታጅቦ እንዲጓጓዝ ሊወስን የሚችለው እንደዚህ ዓይነቱ እርምጃ ለጉምሩክ ቁጥጥር አማራጭ የሌለው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የማጓጓዣ የተወሰነ ክፍል መታሸግ አያስፈልገውም ብሎ መወሰን የሚችለው ባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

፲፱. <u>ስለጉምሩክ ማሸጊያዎች</u>

፩/ ለጉምሩክ ትራንዚት አገልግሎት የሚውሉ የጉምሩክ ማሸጊያዎችና ማሰሪያዎች በባለሥልጣኑ መመሪያ የተወሰኑ ዝርዝር መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

፪/ በውጭ አገር ጉምሩክ አማካይነት የተደረጉ የጉምሩክ ማሸጊያዎችና መለያ ምልክቶች፡-

ሀ) በቂ አይደሉም ካልተባለ፤

ለ) አስተማማኝ ካልሆኑ፤ ወይም

5/ If a consignment is, in principle, to be conveyed under customs seal and the transport-unit cannot be effectively sealed, identification shall be assured and unauthorized interference rendered readily detectable by:

a) full examination of the goods and recording the results thereof on the transit document;

b) affixing customs seals or fastenings to individual packages;

c) a precise description of the goods by reference to samples, plans, sketches, photographs, or similar means, to be attached to the transit document;

d) stipulation of a strict routing and strict time limits; or

e) customs escort.

6/ When the Authority fix a time limit for customs transit under paragraph (d) of sub-article (5) of this Article, it shall be sufficient for the purposes of the transit operation. Such time limit may be extended at the request of the declarant or the carrier, and for reasons deemed valid by the Authority.

7/ The Authority shall require goods to follow a prescribed itinerary or to be transported under customs escort in accordance with paragraph (d) or (e) of sub-article (5) of this Article when it considers such a measure to be indispensable for the purpose of customs control.

8/ The decision to waive sealing of a transport-unit under this Article shall be the prerogative of the Authority.

19. <u>Customs Seals</u>

1/ Customs seals and fastenings used in the application of customs transit shall fulfill the requirements stipulated by directive of the Authority.

2/ Customs seals and identification marks affixed by foreign customs shall be accepted for the purposes of the customs transit operation unless:

a) they are considered not to be sufficient;

b) they are not secure; or

ሐ) ባለሥልጣኑ ዕቃውን ለመመርመር ካልወሰነ፤

በስተቀር ለጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸም ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ተቀባይነት ያገኙ የውጭ አገር የጉምሩክ ማሸጊያዎችና ማሰሪያዎች ባለሥልጣኑ እንደሚጠቀማቸው የጉምሩክ ማሸጊያዎችና ማሰሪያዎች ተመሣሣይ የሕግ ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

## ፳. በጉዞ ወቅት ስለሚፈጸም ሥነስርዓት

፩/ በቅድሚያ ፈቃድ መገኘት አለበት ተብሎ በባለሥልጣኑ ካልተወሰነ በስተቀር በመዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያ ላይ የሚደረግ ለውጥ አስቀድሞ ማስታወቅ ሳያስፈልግ ተቀባይነት ይኖረዋል።

፪/የጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ማሰሪያ እንዲወገድ እስካልተደረገ ወይም እስካልተነካካ ድረስ ባለሥልጣኑን ማስፈቀድ ሳያስፈልግ ዕቃን ከአንድ ማጓጓዣ ወደ ሌላ ማጓጓዣ ማዛወር ይቻላል።

፫/ በጉምሩክ ትራንዚት ላይ ያለውን ዕቃ ለይቶ ለማወቅ የሚቻል እስከሆነና ሌሎች የጉምሩክ ፎርማሊቲዎች እስከተሟሉ ድረስ ሌሎች ዕቃዎች በተጫኑበት የማጓጓዣ የተወሰነ ክፍል ውስጥ ተጭኖ እንዲጓጓዝ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል።

፬/ በጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸሙ ላይ በቀጥታ ተጽኖ የሚያመጣ አደጋ ወይም ያልተጠበቀ ሁኔታ ሲከሰት ዲክላራሲዮን አቅራቢው ወይም አጓጓዡ ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኘው የጉምሩክ ጣቢያ ወይም አግባብ ላለው ሌላ የመንግስት አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት።

## ፳፩. ስለጉምሩክ ትራንዚት መጠናቀቅ

፩/ የጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸምን ለማጠናቀቅ ዕቃዎቹ ምንም ለውጥ ሳይደረግባቸውና አገልግሎት ላይ ሳይውሉ፣ የጉምሩክ ማሸጊያው፣ ማሰሪያው ወይም መለያ ምልክቱ ሳይነካካ ከሚመለከተው የዕቃ ዲክላራሲዮን ጋር ለመዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ አለባቸው።

፪/ የመዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያው ዕቃዎቹ በቁጥጥሩ ሥር እንደገቡ ወዲያውኑ ሁሉም ቅድመሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸሙን ለማጠናቀቅ ሁኔታውን ማመቻቸት አለበት።

c) the Authority proceed to an examination of the goods.

3/ When foreign customs seals and fastenings have been accepted pursuant to sub-article (2) of this Article, they shall be afforded the same legal protection as customs seals and fastenings used by the Authority.

## 20. Procedures En Route

1/ A change in the customs station of destination shall be accepted without prior notification except where the Authority have specified that prior approval is necessary.

2/ Transfer of goods from one means of transport to another shall be allowed without authorization by the Authority, provided that any customs seals or fastenings are not broken or interfered with.

3/ The Authority may allow goods to be transported under customs transit in a transport-unit carrying other goods at the same time, provided that it is satisfied that the goods under customs transit can be identified and the other customs requirements shall be met.

4/ The declarant or the carrier shall report accidents or other unforeseen events directly affecting the customs transit operation promptly to the nearest customs station or other appropriate government body.

## 21. Termination of Customs Transit

1/ For the purpose of termination of a customs transit operation, the goods and the relevant goods declaration shall be presented to the customs station of destination within the time limit fixed, without the goods having undergone any change and without having been used, and with customs seals, fastenings or identification marks intact.

2/ The customs station of destination shall, as soon as the goods are placed under its control, arrange without delay for the termination of the customs transit operation after having satisfied itself that all conditions have been met.

፫/ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚዘረዘሩ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር በጉምሩክ ትራንዚት የሚጓጓዙ ዕቃዎች በባለሥልጣኑ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያው ዘንድ ያልደረሱ ከሆነ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡

**፳፪.** <u>**ማጓጓዣ በመቀየር ዕቃን ስለማጓጓዝ**</u>

፩/ በአስመጪው፣ በአጓጓዡ፣ ወይም በጉምሩክ ሥነስርዓት አስፈፃሚው ጥያቄ ዕቃ ከአንድ ማጓጓዣ ወደ ሌላ ማጓጓዣ በመቀየር ሊጓጓዝ ይችላል፡፡

፪/ ማንኛውም ተፈላጊ ዝርዝሮችን የያዘ የንግድ ወይም የማጓጓዣ ሰነድ ለዚህ አንቀጽ ተፈጻሚነት እንደ ዕቃ ዲክላሬሲዮን ተቆጥሮ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማጓጓዣ በመቀየር የሚጓጓዘውን ዕቃ ከአገር በሚወጣ ጊዜ ለመለየትና ያልተፈቀደ ጣልቃ ገብነትን ወዲያውኑ ለማጋለጥ የሚያስችል የጥንቃቄ እርምጃ ዕቃው በሚገባበት ወቅት ሊወስድ ይችላል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ ማጓጓዣ በመቀየር የሚጓጓዝ ዕቃ ከአገር የሚወጣበትን በቂ የሆነ የጊዜ ገደብ ሊወስን ይችላል፡፡

፭/ ማጓጓዣ በመቀየር የሚጓጓዝ ዕቃ ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡

<u>**ምዕራፍ ሦስት**</u>
<u>**የዕቃ አወጣጥ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት**</u>

**፳፫.** <u>**ስለሰነድና ዕቃ ምርመራ**</u>

፩/ ባለሥልጣኑ የሚለቀቁ ዕቃዎች በተመዘገበ ዲክላራሲዮን የተሸፈኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እቃዎቹን መመርመርና የምርመራና ትንተና ናሙናዎችን ለመውሰድ ይችላል፡፡

፪/ ዕቃዎቹ በሚመረመሩበት ወይም ናሙናዎች በሚወሰዱበት ወቅት ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሥፍራው የመገኘት መብት ይኖረዋል፤ ሆኖም ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሥፍራው ካልተገኘ የመጋዘኑ ሃላፊ ባለበት ባለሥልጣኑ ዕቃ የመመርመር ወይም ናሙና የመውሰድ ተግባሩን ያከናውናል፡፡

፫/ ዕቃዎቹ ወደሚፈተሹበት ወይም ናሙናዎቹ ወደ ሚወሰዱበት ሥፍራ ለማጓጓዝ፣ ናሙናዎችን ለመውሰድ እና ለምርመራ የሚያስፈልገው ወጪ እንዲሁም ማናቸውም ከዚህ ሥራ ጋር የተያያዘ ወጪ የዲክላራሲዮን አቅራቢው ኃላፊነት ይሆናል፡፡

3/ If goods on transit are not presented to the customs station of destination within the prescribed time limit for reasons specified in the directive to be issued by the Authority, the guarantee shall be forfeited to the government.

**22. <u>Transshipment</u>**

1/ Transshipment of goods may be allowed upon request submitted by the importer, carrier or by the customs agent.

2/ Any commercial or transport document setting out clearly the necessary particulars shall be accepted as the goods declaration for the application of this Article.

3/ When the Authority considers it necessary, it shall take precautionary measure at importation to ensure that the goods to be transshipped shall be identifiable at exportation and that unauthorized interference shall be readily detectable.

4/ The Authority may fix a sufficient time limit for the exportation of goods declared for transshipment.

5/ Goods admitted to transshipment may not be subjected to the payment of duties and taxes.

**CHAPTER THREE**
**CUSTOMS PROCEDURES FOR CLEARANCE OF GOODS**

**23. <u>Examination of Documents and Goods</u>**

1/ The Authority may, to ensure that goods to be released are covered by a registered declaration, examine the goods and take samples for examination and analysis.

2/ The declarant shall be entitled to be present when the goods are examined or samples are taken; provided, however, that if he fails to appear, the Authority shall proceed to conduct the examination or to take the samples in the presence of the warehouse operator.

3/ The cost of transport of the goods to the place where they are examined or samples are taken, the cost of taking samples and the cost of examination as well as any expense related thereto shall be borne by the declarant.

፬/ በጉምሩክ ህግ መሰረት ለተወሰዱ ናሙናዎች ባለሥልጣኑ ለዲክላራሲዮን አቅራቢው የካሳ ክፍያ የመፈፀም ኃላፊነት የለበትም።

፭/ ምርመራ የተደረገባቸው ዕቃዎች በዕቃ ዲክላራሲዮን ከተሸፈኑት ዕቃዎች ውስጥ ከፊል ብቻ ከሆኑ የምርመራው ውጤት በዚያ ዲክላራሲዮን ለተሸፈኑት ዕቃዎች ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል።

፮/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው የተደረገው ከፊል ምርመራ የቀሩትን ዕቃዎች በተመለከተ ተቀባይነት እንደሌለው ካሰበ በዕቃዎቹ ላይ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል። ለተጨማሪው የምርመራና የትንተና ሥራ የሚያስፈልገውን ወጪ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ይሸፍናል።

፯/ የዕቃ ዲክላራሲዮኑ ማጣራት የማይከናወንበት ከሆነ፣ የጉምሩክ ፎረማሊቲው ዲክላራሲዮኑ ላይ በተገለፀው ዝርዝር መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

፰/ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ የተመለከቱ ሁኔታዎችን የሚያሟሉ ዕቃዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፀምባቸው ሊደረግ ይችላል።

**፳፬. በዕቃዎች ላይ የመለያ ምልክት ስለማድረግ**

፩/ ለዕቃው በቀረበው ዲክላራሲዮን የተገለጸውን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለማስፈፀም ዕቃውን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በዕቃው ላይ መለያ ምልክት ሊያደርግ ይችላል።

፪/ በባለሥልጣኑ በሚወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የማጓጓዣውን ወይም የዕቃውን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የምልክቶቹን መወገድ አስፈላጊ ካላደረጋቸው በስተቀር በዕቃው ወይም በማጓጓዣው ላይ የተለጠፉ ምልክቶች ሊወገዱ ወይም ሊነሱ የሚችሉት በባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀደለት ሰው ይሆናል።

**፳፭. ዕቃዎችን ስለመልቀቅ**

፩/ ዲክላራሲዮን የቀረበላቸው ዕቃዎች በባለሥልጣኑ የሚደረግ ምርመራ ሲያበቃ ወይም ባለሥልጣኑ እንደማይመረምራቸው ሲወስን፦

ሀ) የተከለከሉ ካልሆኑ ወይም ከዕቃዎቹ ጋር በተያያዘ የተፈፀመ ወንጀል ከሌለ፤

ለ) ዕቃዎች የተመደቡበት አግባብነት ያለው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ከተሟላ፤

ሐ) ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎችን በሚመለከት አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ፈቃድ ከቀረበ፤ እና

4/ The Authority may not be liable for payment of any compensation to the declarant for samples taken in compliance with customs law.

5/ Where only parts of the goods covered by the goods declaration are examined the result of such examination shall apply to all goods indicated by the declaration.

6/ Where the declarant considers that the result or partial examination is not valid as regards the remainder of the goods, he may request further examination of the goods and shall cover the expenses incurred by such examination.

7/ Where the goods declaration is not made subject to verification, the customs formalities shall be applied based on the particulars stated in the declarations.

8/ Goods that meet the conditions specified in the directive issued by the Authority may be given priority in undergoing customs procedure.

**24. Placing Identification Mark on Goods**

1/ The Authority shall place identification mark on the goods where identification is required in order to ensure compliance with the procedure for which the goods have been declared.

2/ The identification mark affixed to the goods or the means of transport shall be removed or destroyed by the Authority or by a person authorized by the Authority except in the case of force majeure to be determined by directive of the Authority, where their removal or destruction is essential to ensure the protection of the goods or means of transport.

**25. Release of Goods**

1/ Goods declared shall be released as soon as they are examined by the Authority or the Authority decided not to examine them, provided that:

a) they are not subject to prohibition or an offence is committed in relation to them;

b) where the conditions of placing the goods under the customs procedure in question are fulfilled;

c) in the case of restricted goods, the permit issued by the appropriate body pursuant to the relevant law is presented; and

መ) መከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ከተከፈለ ወይም ዋስትና ከቀረበ፤

ወዲያውኑ መለቀቅ አለባቸው።

፪/ ባለሥልጣኑ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስመጪው በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመክፈል ዋስትና ሰጥቶ እንዲለቀቁ ሊያደርግ ይችላል። ሆኖም በዚህ ዓይነት ለቀረጥና ታክስ ክፍያ የሚሰጠው ጊዜ ከ፲፪ ወራት በላይ ሊሆን አይችልም።

፫/ ቀረጥና ታክስ ለመወሰን ናሙናዎች ተወስደው የቴክኒክ ሰነዶችና የባለሙያ አስተያየት የሚያስፈልግ በሚሆንበት ጊዜ የምርመራው ውጤት ከመታወቁ በፊት ባለሥልጣኑ ዋስትና እንዲቀርብ በማድረግ ዕቃውን መልቀቅ ይችላል።

፬/ የተለየ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በአንድ ዲክላራሲዮን የሚሸፈኑ እቃዎች መለቀቅ ያለባቸው በአንድ ላይ ነው።

## ፳፮. በምትክነትና በማሟያነት ስለሚገቡ እቃዎች

፩/ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲባል ወደ አገር ውስጥ የገባ እቃ በስህተት ወይም በብልሽት ለታለመለት ዓላማ መዋል ካለመቻል ወይም የተሟላ ካለመሆን የተነሳ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመልሶ እንዲወጣ በአስመጪው ጥያቄ ከቀረበ እቃው ከአገር እንዲወጣ ተደርጎ በምትክነት የሚመጣው ተመሳሳይ ዕቃ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር እንዲገባ ሊፈቀድለት ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በምትክነት የሚመጣው ተመሳሳይ ዕቃ ወደ አገር ከመግባቱ በፊት በስህተት ወይም በብልሽት ለታለመለት ዓላማ ሊውል ያልቻለውን ወይም ያልተሟላውን ዕቃ ከአገር እንዲወጣ ማድረግ የማይቻል መሆኑን ባለሥልጣኑ ሲያምንበት ዕቃው በተወሰነ ጊዜ ከአገር እንዲወጣ ለማድረግ አስመጪው ዋስትና እንዲያቀርብ በማድረግ ወይም ዕቃው ለአገልግሎት የማይውል ከሆነ አስመጪው ዕቃውን ለባለሥልጣኑ እንዲያስረክብ በማድረግ የሚመጣው ተመሳሳይ ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በምትክነት ወደ አገር እንዲገባ ሊፈቅድ ይችላል።

፫/ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲባል ወደ አገር የገባው ዕቃ በዲክላራሲዮኑ ላይ ከተገለፀው መጠን ጋር ሲነፃፀር ጉድለት ያለበት መሆኑ በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ ባለሥልጣኑ የቀረው ዕቃ ተሟልቶ እንዲገባ ወይም ባልገባው ዕቃ ላይ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል።

d) any applicable duties and taxes have been paid or security is furnished.

2/ The Authority may, in accordance with a directive issued by the Ministry, release goods upon receiving a guarantee from the importer to secure payment of the taxes and duties within a certain period of time: provided, however, that the period of such deferred payment may not exceed 12 months.

3/ Where samples are taken and technical documents and expert advice is required to determine taxes and duties, the Authority may release the goods with security before the results of such examination are known.

4/ All the goods covered by a declaration shall be released at the same time unless the condition requires otherwise.

## 26. Replacement and Compensatory Goods

1/ Goods imported for home use may be allowed to be re-exported and replaced within one year from the date of importation without additional payment of duties and taxes upon the request of the importer if they are incompatible to their intended purpose due to defect, error of consignment or their incompleteness.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, if the Authority is convinced that the goods found to be incompatible to their intended purpose due to defect, error of consignment or their incompleteness cannot be re-exported before the replacement goods are imported, it may allow the importation of the replacement goods without payment of duties and taxes upon submission of a guarantee for the re-export of the goods within a certain period of time or, if such goods cannot be used for any other purpose, after their delivery to the Authority.

3/ Where it is ascertained by sufficient evidence that goods imported for home use are less than the quantity stated in the goods declaration, the Authority may allow the remaining goods to be imported or refund the amount of tax and duties paid on the remaining goods.

## ምዕራፍ አራት

## ለመንገደኞች ተፈጻሚ ስለሚሆን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

### ፴. በመንገደኞች ስለሚቀርብ የዕቃ ዲክላራሲዮን

፩/ ማንኛውም መንገደኛ ስለያዘው ዕቃ በቃል ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ ሊፈቀድለት ይችላል፤ ሆኖም መንገደኛው ወደ አገር ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ የያዘው ዕቃ የንግድ ባህሪ ያለው ሲሆን በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ መደረግ አለበት፡፡

፪/ ወደ አገር ውስጥ የገባ መንገደኛ ከሚከተሉት የማለፊያ መስመሮች አንዱን መርጦ በማለፍ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ ሊፈቀድለት ይችላል፡-

ሀ) በዋጋ ወይም በብዛት ቀረጥና ታክስ ከማይከፈልበት መጠን በላይ ያልሆኑ ወይም ክልከላ ወይም ገደብ ያልተደረገባቸውን ዕቃዎች የያዙ መንገደኞች እንዲጠቀሙበት በአረንጓዴ ምልክት የተለየውን የማለፊያ መስመር፤ ወይም

ለ) በዋጋ ወይም በብዛት ቀረጥና ታክስ ከማይከፈልበት መጠን በላይ የሆኑ ወይም ክልከላ ወይም ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች የያዙ መንገደኞች እንዲጠቀሙበት በቀይ ምልክት የተለየውን የማለፊያ መስመር፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በመንገደኞች ላይ የሚፈጸመውን የጉምሩክ ቁጥጥርና የያዟቸውን ዕቃዎች የመልቀቅ ተግባር ለማቀላጠፍ አግባብ ካላቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁና በቅድሚያ ሊገኙ የሚችሉ የተሳፋሪዎች መረጃዎች ካሉ እነዚህኑ ሊጠቀም ይችላል፡፡

### ፴፩. በመንገደኞች የተያዙ ዕቃዎች መጋዘን ተከማችተው እንዲቆዩ ስለማድረግ

በመንገደኞች የተያዙ ዕቃዎች፡-

፩/ መንገደኛው ሲጠይቅ፤

፪/ ዕቃዎቹ ወዲያውኑ ሊለቀቁ የማይችሉ ሲሆን፤ ወይም

፫/ ዕቃዎቹ በዚህ ምዕራፍ ሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ሊስተናገዱ የማይችሉ ሲሆን፤

## CHAPTER FOUR

## CUSTOMS PROCEDURE FOR TRAVELERS

### 30. Goods Declaration by Travelers

1/ A traveler may be permitted to make an oral declaration in respect of the goods carried by him; provided, however, that a written or electronic declaration shall be required for goods carried by a traveler which constitute an importation or exportation of a commercial nature.

2/ A traveler on arrival may be allowed to make a declaration by choosing between the following types of channel:

a) a channel, identified by green symbol, that is for the use of travelers carrying goods in quantities or values not exceeding those admissible duty-free and which are not subject to import prohibitions or restrictions; or

b) a channel, identified by red symbol, that is for the use of travelers carrying goods in quantities or values exceeding those admissible duty-free or which are subject to import prohibitions or restrictions.

3/ The Authority, in co-operation with other relevant bodies, may use internationally standardized advance passenger information, where available, in order to facilitate the customs control of travelers and the clearance of goods carried by them.

### 31. Storage of Goods Carried by Travelers

Goods carried by travelers shall be stored, subject to the conditions prescribed by the Authority, pending clearance under the appropriate customs procedure, re-exportation or other disposal in accordance with this Proclamation:

1/ at the traveler's request;

2/ when the goods concerned cannot be cleared immediately; or

3/ where the other provisions of this Chapter do not apply to such goods.

እግባብ ባለው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እስከሚስተናገዱ፣ ወደ ውጭ ተመልሰው እስከሚወጡ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሌላ መንገድ እስከሚወገዱ ድረስ ባለሥልጣኑ የሚወስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በመጋዘን ተከማችተው እንዲቆዩ ይደረጋል::

## ፴፪. ከመንገደኛው ተለይቶ ስለሚጓጓዝ ሻንጣ

፩/ ከመንገደኛው ቀድሞ ወይም ዘግይቶ የሚደርስ ወይም የሚጓጓዝ የመንገደኛ ሻንጣ ከመንገደኛ ጋር አብሮ ለሚጓጓዝ ሻንጣ ተፈጻሚ በሚሆነው ወይም በሌላ ቀለል ባለ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት መሠረት ይስተናገዳል።

፪/ ማንኛውም ውክልና የተሰጠው ሰው ከመንገደኛው ተለይቶ የተጓጓዘን ሻንጣ መንገደኛውን ወክሎ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈጸምበት ለማድረግ ይችላል።

## ፴፫. ለንግድ ዓላማ የማይውሉ ዕቃዎችና የግል መገልገያዎች

፩/ በዚህ አዋጅ ክፍል አራት በሌላ ሁኔታ የተደነገገው ቢኖርም አግባብ ያለው ሆኖ ሲገኝ ለንግድ ዓላማ የማይውሉ በመንገደኞች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጪ የሚወጡ ዕቃዎችን ቀረጥና ታክስ አወሳሰን በሚመለከት ወጥ የሆነ የታሪፍ ምጣኔ ሥርዓት ተፈጻሚ ሊደረግ ይችላል።

፪/ መንገደኞች የግል መገልገያዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር ውስጥ ይዘው ለመግባት ወይም ወደ ውጭ ይዘው ለመውጣት ይፈቀድላቸዋል።

፫/ ተመላሽ ነዋሪ መንገደኞች በጉምሩክ ክልል ውስጥ ለነጻ ዝውውር ተለቀው የነበሩና ይዘዋቸው የወጡ የግል መገልገያዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር ውስጥ መልሰው ለማስገባት ይፈቀድላቸዋል።

፬/ ነዋሪ ላልሆነ መንገደኛ የግል መገልገያዎችን በጊዜያዊነት የማስገቢያ ዲክላራሲዮን ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ መንገደኛው በጉምሩክ ክልል ውስጥ የሚቆይበትን ጊዜ በማገናዘብ የግል መገልገያዎቹ ተመልሰው የሚወጡበትን የጊዜ ገደብ ሊወስን ይችላል።

፭/ ባለሥልጣኑ መንገደኛው በበቂ ምክንያት ሲጠይቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የተወሰነውን የጊዜ ገደብ ሊያራዝመው ይችላል።

፮/ ወደ ጉምሩክ ክልል የሚገቡ ወይም ከጉምሩክ ክልል የሚወጡ መንገደኞች የራሳቸውን መጓጓዣ መጠቀም የሚችሉበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፯/ ነዋሪ ያልሆነ መንገደኛ በጊዜያዊነት ይዞት የገባውን የግል መገልገያ ከገባበት ውጭ በሆነ ሌላ የጉምሩክ ወደብ መልሶ ይዞ ለመውጣት ይችላል።

## 32. Unaccompanied Baggage

1/ A baggage arriving or leaving before or after th traveler shall be cleared under the procedur applicable to accompanied baggage or under anothe simplified customs procedure.

2/ Any authorized person shall be allowed to presen unaccompanied baggage for clearance on behalf o the traveler.

## 33. Non-Commercial Goods and Personal Effects

1/ Notwithstanding any provision to the contrary under Part Four of this Proclamation, a system of flat-rate assessment of duties and taxes may, where appropriate, be applied to non-commercial goods imported or exported by travelers.

2/ Travelers shall be allowed to import or export personal effects free of duties and taxes.

3/ Returning residents shall be permitted to re-import free of duties and taxes personal effects which they took with them at the time of their departure and which were in free circulation in the customs territory.

4/ Where it is necessary to lodge a temporary admission declaration for non-residents' personal effects, the Authority may fix the time limit for the re-exportation of such personal effects by reference to the length of the traveler's stay in the customs territory.

5/ The Authority may, at the request of the traveler on the basis of valid reasons, may extend the time limit fixed pursuant to sub-article (4) of this Article.

6/ The conditions under which travelers entering or leaving the customs territory may use their private means of transport shall be determined by directive to be issued by the Authority.

7/ A non-resident traveler may re-export temporarily admitted personal effects through a customs port other than that through which they were imported.

፰/ ባለሥልጣኑ በአደጋ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የወደመን ወይም በጣም የተጎዳን የግል መገልገያ ነዋሪ ያልሆነው መንገደኛ መልሶ ይዞ እንዲወጣ ማስገደድ የለበትም፡፡

**፴፬. ስለተላላፊ መንገደኞች**

ተላላፊ መንገደኞች የትራንዚት አካባቢውን እስካልለቀቁ ድረስ የጉምሩክ ቁጥጥር አይደረግባቸውም፤ ሆኖም ባለሥልጣኑ በትራንዚት አካባቢው ላይ አጠቃላይ ቁጥጥር ማድረግና የጉምሩክ ወንጀል ተፈጽሟል የሚል ጥርጣሬ ሲኖር አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡

**፴፭. ለመንገደኞች የሚሰጡ የጉምሩክ አገልግሎቶችን ስለሚመለከቱ መረጃዎች**

ባለሥልጣኑ ለመንገደኞች የሚሰጡ የጉምሩክ አገልግሎቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅተው አግባብነት ባላቸው መንገዶች ለመንገደኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## በፖስታ ስለሚገቡና ስለሚወጡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

**፴፮. ስለጉምሩክ ቁጥጥር**

በፖስታ አገልግሎት በኩል ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡

**፴፯. ሪፖርት የማድረግ ግዴታ**

የፖስታ አገልግሎት ሥራ እንዲሠራ የተፈቀደለት ማንኛውም ሰው በፖስታ ወደ አገር ውስጥ ስለገቡትና ወደ ውጭ አገር ስለሚላኩ ዕቃዎች የዕቃ ዝርዝር መግለጫ በማቅረብ ወይም ሌላ የተፈቀደ የማሳወቂያ ዘዴ በመጠቀም ለሚመለከተው የጉምሩክ ሹም ማሳወቅና ዕቃዎቹንም ለክሊራንስ ማቅረብ አለበት፡፡

**፴፰. የፖስታ ዕቃዎች ዲክላራሲዮን**

፩/ በፖስታ አገልግሎት በኩል ወደ አገር ለገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ ዕቃ በላኪው የተሰጠ መግለጫ፣ በዕቃው ላይ የተለጠፈ ምልክት ወይም ከዕቃው ጋር የቀረበ ማናቸውም ደጋፊ ሰነድ፡-

ሀ) የዕቃው ዋጋ በባለሥልጣኑ ከተወሰነው በላይ ያለመሆኑን የሚያረጋግጥ ከሆነ፤

ለ) ዕቃውን ወደ አገር ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ ሠርተፊኬት የማያስፈልገው መሆኑን ሊያረጋግጥ የሚችል ከሆነ፤ እና

8/ The Authority may not require the re-exportation of personal effects of a non-resident traveler which have been destroyed or seriously damaged due to accident or force majeure.

**34. Transit Travelers**

Transit travelers who do not leave the transit area may not be required to pass through any customs control; provided, however, that the Authority may maintain general surveillance of transit areas and take any action necessary when a customs offence is suspected.

**35. Information Concerning the Customs Facilities Applicable to Travelers**

The Authority shall make available, through the appropriate means, information concerning the customs facilities applicable to travelers in the Amharic and English languages.

## CHAPTER FIVE

## CUSTOMS PROCEDURE FOR IMPORTATION AND EXPORTATION OF GOODS THROUGH THE POSTAL SYSTEM

**36. Customs Control**

Goods imported or exported through the postal system shall be subject to customs control.

**37. Duty to Report**

Any person authorized to provide postal services shall report by means of a manifest or in any other approved manner, all goods arriving or departing through the postal system and shall present such goods to a customs officer for clearance.

**38. Postal Goods Declaration**

1/ Where any form completed by the sender, label affixed or supporting documents produced in respect of goods imported or to be exported through the postal system shows that:

a) the goods have a value not exceeding the value determined by the Authority;

b) importation or exportation of the goods does not require certification; and

ሐ) ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ ከአገር ውስጥ ፍጆታ ውጪ ባለ ሌላ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የማይመደብ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሆነ፤

ተቀባይነት ያገኘ ዲክላራሲዮን እንደቀረበበት ዕቃ ተቆጥሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ይከናወንበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ውጪ ለሆነና በፖስታ አገልግሎት በኩል ወደ አገር ውስጥ ለገባ ወይም ወደ ውጭ ለሚላክ ዕቃ ራሱን የቻለ የዕቃ ዲክላራሲዮን ተሞልቶ መቅረብ አለበት፡፡

**፴፱. ውክልና ስለመስጠት**

ባለሥልጣኑ ለፖስታ አገልግሎት ድርጅቶች ወደ አገር ውስጥ በሚገቡና ከአገር በሚወጡ ዕቃዎች ላይ ቀረጥ እና ታክስ እንዲሰበስቡ የውክልና ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## በንግድ አገልግሎት ማጓጓዣዎች እና በጉዞ እቃዎች ክምችት ላይ ስለሚፈጸም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

**፵. የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣን በጊዜያዊነት እንዲገባ ስለመፍቀድ**

፩/ ማንኛውም ጭነት የያዘ ወይም ያልያዘ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣ፡-

ሀ) በጉምሩክ ክልል ውስጥ ለአገር ውስጥ ማጓጓዣ አገልግሎት የማይውል ከሆነ፤ እና

ለ) በአጠቃቀም ምክንያት ከሚደርስበት መደበኛ እርጅና፣ ከቅባቶችና ነዳጅ መደበኛ ፍጆታና ከአስፈላጊ ጥገናዎች በስተቀር ምንም ለውጥ ሳይደረግበት ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ ለማድረግ ታስቦ ከሆነ፤

ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በጊዜያዊነት ወደ ጉምሩክ ክልል እንዲገባ ይፈቀዳል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ለጉምሩክ ቁጥጥር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በውጭ አገር በአግባቡ የተመዘገበ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣ በጊዜያዊነት እንዲገባ ሲፈቅድ ዋስትና እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የማጓጓዙ ሥራ ሂደት የሚጠይቃቸውን ሁኔታዎች በማገናዘብ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣው ተመልሶ የሚወጣበትን የጊዜ ገደብ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

c) the imported goods do not require to be placed under a different procedure other than the customs procedure applicable to goods for home use;

such form, label or supporting documents shall be considered as an acceptable declaration for the purpose of customs formalities.

2/ A separate goods declaration shall be required for goods imported or to be exported through the postal system and are not covered by the provisions of sub-article (1) of this Article.

**39. Delegation**

The Authority may delegate postal service providers to collect duties and taxes on goods imported and exported through the postal system.

## CHAPTER SIX

## CUSTOMS PROCEDURE APPLICABLE TO MEANS OF TRANSPORT FOR COMMERCIAL USE AND STORES

**40. Temporary Admission of Means of Transport for Commercial Use**

1/ Any means of transport for commercial use, whether loaded or not, shall be allowed to be brought temporarily into the customs territory relieved from payment of duties and taxes, provided that:

a) it is not used for internal transport in the customs territory; and

b) it is intended for re-exportation without having undergone any change except normal depreciation due to its use, normal consumption of lubricants and fuel and necessary repairs.

2/ The Authority may require security for temporary admission of means of transport for commercial use duly registered abroad when it considers it essential for the purposes of customs control.

3/ The Authority may fix a time limit for the re-exportation of means of transport for commercial use, taking into account all the circumstances of the transport operations intended.

፬/ ባለሥልጣኑ በሚመለከተው ሰው ጥያቄና ተቀባይነት ባለው ምክንያት ላይ ተመሥርቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተወሰነውን የጊዜ ገደብ ሊያራዝም ይችላል፡፡

## ፵፩. <u>መለዋወጫዎችና መሣሪያዎች በጊዜያዊነት እንዲገቡ ስለመፍቀድ</u>

፩/ ለጭነት መጫኛ፣ ማራገፊያ፣ አያያዝ ወይም አጠባበቅ የሚያስፈልግ ልዩ መሣሪያ ከንግድ አገልግሎት ማጓጓዣው ተነጥሎ አገልግሎት ላይ ሊውል የሚችል ቢሆንም ባይሆንም ከንግድ አገልግሎት ማጓጓዣው ጋር ተመልሶ የሚወጣ እስከሆነ ድረስ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ከንግድ አገልግሎት ማጓጓዣው ጋር በጊዜያዊነት ወደ ጉምሩክ ክልል እንዲገባ ይፈቀዳል፡፡ ሆኖም አስመጪው የተቀየረውን አካል ከአገር ማስወጣት ወይም ለባለሥልጣኑ ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

፪/ በጊዜያዊነት ወደ ጉምሩክ ክልል አስቀድሞ የገባ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣን በመጠገን ወይም በማደስ ሂደት በማጓጓዣው ላይ የተገጠሙ አካላትንና በማጓጓዣው ላይ አገልግሎት የሚሰጡ መሣሪያዎችን ለመተካት የሚያገለግሉ መለዋወጫዎችና መሣሪያዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ ጉምሩክ ክልል እንዲገቡ ይፈቀዳል፡፡

## ፵፪. <u>የመድረሻ ዲክላራሲዮን</u>

ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ህጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን የያዘ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣ ስለመድረሱ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## ፵፫. <u>የመውጫ የጉምሩክ ሥነሥርዓት</u>

፩/ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣን የሚመለከተው የመውጫ የጉምሩክ ሥነሥርዓት እንደ አግባቡ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦

ሀ) የመውጫ ዲክላራሲዮን ለባለሥልጣኑ ማቅረብን፤

ለ) የማጓጓዣውን ጭነት በጉምሩክ ማሸጊያ እንዲታሸግ ማድረግን፤

ሐ) ጉዞው የተወሰነ የጉምሩክ መስመርን እንዲከተል ማድረግን፤ እና

መ) ያልተፈቀደ የመውጫ መዘግየትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እርምጃዎች መውሰድን፡፡

፪/ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣ ወደ ጉምሩክ ክልል ከገባበት የጉምሩክ ጣቢያ ውጪ በሆነ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ ተመልሶ እንዲወጣ ይፈቀድለታል፡፡

4/ The Authority may, at the request of the person concerned and for reasons deemed valid, extend the period fixed pursuant to sub-article (3) of this Article.

## 41. <u>Temporary Admission of Parts and Equipment</u>

1/ Special equipment for the loading, unloading, handling or protection of cargo, whether or not it is capable of being used separately from the means of transport for commercial use, which is imported with the means of transport for commercial use and is intended to be re-exported therewith, shall be allowed to be brought temporarily into the customs territory relieved from payment of import duties and taxes.

2/ Parts and equipment which are to be used, in the course of repair or maintenance, as replacements for parts and equipment incorporated in or used on a means of transport for commercial use already temporarily imported into the customs territory, shall be allowed to be brought temporarily into the customs territory relieved from payment of duties and taxes; provided, however, that the importer shall re-export or handover the replaced part to the Authority.

## 42. <u>Declaration of Arrival</u>

The Authority may require the lodging of a declaration of arrival of a means of transport for commercial use containing the particulars necessary to ensure compliance with the customs law.

## 43. <u>Customs Procedures for Departure</u>

1/ Customs procedures applicable upon the departure of means of transport for commercial use may, as appropriate, include:

a) the lodging of a declaration of departure with the Authority;

b) the affixing of customs seals;

c) the designation of a specified customs route; and

d) the taking of measures for monitoring unauthorized delay in the departure.

2/ A means of transport for commercial use shall also be permitted to depart from the customs territory through a customs station other than that through which it arrived.

**፵፬. <u>በሚገባ አውሮፕላን ወይም ባቡር ላይ የተጫነ የጉዞ እቃ ክምችት</u>**

፩/ ወደ ጉምሩክ ክልል በገባ አውሮፕላን ወይም ባቡር ላይ የተጫነ ለመንገደኞችና ለማጓጓዣው ሠራተኞች ፍጆታ እንዲውል የተጫነ ዕቃ ወይም ለማጓጓዣው አገልግሎት አሰጣጥ ወይም ጥገና አስፈላጊ የሆነ ዕቃ ከማጓጓዣው ሳይራገፍ እስከቆየ ድረስ ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በዓለም አቀፍ የባቡር ማጓጓዣ ላይ ለመንገደኞችና ለባቡሩ ሠራተኞች ፍጆታ እንዲውል የተጫነ እቃ፡-

ሀ) የተገዛው የባቡሩ ጉዞ ካቋረጣቸው አገራት ከሆነ፤ እና

ለ) በተገዛበት አገር ተከፋይ የሆነው ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ከሆነ፤

ቀረጥና ታክስ አይከፈልበትም፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በአውሮፕላኑ ወይም በባቡሩ ላይ ስለተጫነው የጉዞ ዕቃ ክምችት የተለየ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ መጠየቅ የለበትም፡፡

፬/ አውሮፕላኑ በጉምሩክ ክልል ውስጥ በሚገኝ አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ አውሮፕላን ማረፊያ የሚያርፍ ከሆነ በአውሮፕላን ማረፊያው ለሚቆይበትና ከአንዱ ወደ ሌላው ማረፊያ በሚያደርገው በረራ ወቅት ለፍጆታ የሚያስፈልገውን የጉዞ ዕቃ ክምችት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲያሟላ ይፈቀድለታል፡፡

፭/ አጓጓዡ ዕቃውን ባልተፈቀደ ዓላማ እንዳያውል ለመከላከል እንደአስፈላጊነቱ ክምችቱን መቆለፍን ጨምሮ አግባብ ያላቸውን እርምጃዎች እንዲወስድ ባለሥልጣኑ ሊያዘው ይችላል፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አውሮፕላኑ ወይም ባቡሩ በጉምሩክ ክልል በሚቆይበት ወቅት የጉዞ ዕቃ ክምችቱ ተራግፎ በሌላ ቦታ እንዲቆይ ለማዘዝ ይችላል፡፡

**፵፭. <u>የጉዞ እቃ ክምችት አቅርቦት</u>**

፩/ ወደ ውጭ አገር መጨረሻ መዳረሻ የሚጓዝ አውሮፕላን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆኖ የሚከተሉትን የጉዞ ዕቃ ክምችቶች ጭኖ ለመሄድ ይችላል፡-

ሀ) ባለሥልጣኑ የመንገደኞችንና የአውሮፕላኑን ሰራተኞች ቁጥር፣ በረራው የሚሸፍነውን ርቀት እንደዚሁም በአውሮፕላኑ ውስጥ አስቀድሞ የሚገኘውን የጉዞ ዕቃዎች ክምችት መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት በቂ ነው ብሎ የሚወስደው የጉዞ ዕቃዎች ክምችት፤

**44. <u>Stores on Board Arriving Aircraft or Train</u>**

1/ Stores for consumption by the passengers and the crew of an aircraft or train arriving in the customs territory or stores necessary for the operation and maintenance of the aircraft or the train which are on board such means of transport shall be exempted from import duties and taxes provided that they remain on board.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, stores for consumption by the passengers and the crew imported as provisions on international express trains shall be exempted from import duties and taxes provided that:

a) such goods are purchased in the countries crossed by the international train in question; and

b) any duties and taxes chargeable on such goods in the country where they were purchased are paid.

3/ The Authority may not require the presentation of a separate declaration of stores remaining on board the aircraft or the train.

4/ When an aircraft is to land at one or more airports in the customs territory, the issue of stores, free of duties and taxes, shall be allowed for consumption on board both during the stay of the aircraft at such intermediate airports and during its flight between such airports.

5/ The Authority may require the carrier to take appropriate measures to prevent any unauthorized use of the goods including sealing of the stores, when necessary.

6/ The Authority may require the removal of stores from the aircraft or train for storage elsewhere during its stay in the customs territory when it considers it necessary.

**45. <u>Supply of Stores</u>**

1/ An aircraft which depart for an ultimate foreign destination shall be entitled to take on board, exempted from duties and taxes:

a) stores in such quantities as the Authority deem reasonable having regard to the number of the passengers and the crew, to the length of the flight and to any quantities of such stores already on board;

ለ) በአውሮፕላኑ ውስጥ አስቀድሞ የሚገኘውን የጉዞ ዕቃዎች ክምችት ግምት ውስጥ በማስገባት ለአውሮፕላኑ በረራና ጥገና አገልግሎት ያስፈልጋል ተብሎ የሚገመት መጠን ያለው የጉዞ ዕቃዎች ክምችት፡፡

፪/ ወደ ጉምሩክ ክልል የገባ አውሮፕላን በጉምሩክ ክልል ውስጥ ለመጨረሻ መዳረሻ ጉዞው የሚያስፈልገውንና የተጓደለበትን የጉዞ ዕቃ ክምችት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ለማሟላት ይችላል፡፡

፫/ ወደ ጉምሩክ ክልል የገባ አውሮፕላን በጉምሩክ ክልል ውስጥ በሚቆይበት ወቅት ለሚኖረው ፍጆታ የሚያስፈልገው የጉዞ ዕቃዎች ክምችት በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች መሠረት ይዞ እንዲገባ በሚፈቀድለት ተመሳሳይ አኳኋን እንዲቀርብለት ባለሥልጣኑ ይፈቅድለታል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ ከጉምሩክ ክልል የሚወጣ አውሮፕላን የጫነውን የጉዞ ዕቃዎች ክምችት በሚመለከት ለጉምሩክ ቁጥጥር የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ብቻ የያዘ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብለት ሊያዝ ይችላል፡፡

፵፮. <u>የጉዞ ዕቃ ክምችትን በሌላ መንገድ አገልግሎት ላይ እንዲውል ስለማድረግ</u>

ወደ ጉምሩክ ክልል ውስጥ በገባ አውሮፕላን ወይም ባቡር ላይ የሚገኝ የጉዞ ዕቃ ክምችት፡-

፩/ አግባብነት ያላቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ፎርማሊቲዎች መሟላት እንደተጠበቁ ሆነው ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሊለቀቅ ወይም ሌላ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሊፈጸምበት፤ ወይም

፪/ በባለሥልጣኑ አስቀድሞ ሲፈቀድ ዓለም አቀፍ ጉዞ ወደሚያደርግ ሌላ አውሮፕላን ወይም ባቡር እንደየአግባቡ እንዲተላለፍ ሊደረግ፤

ይችላል፡፡

<u>ምዕራፍ ሰባት</u>

<u>የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎች</u>

፵፯. <u>የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎች</u>

ለዚህ ምዕራፍ አፈጻጸም "የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃ" ማለት በሚመለከተው የመንግሥት አካል ጥያቄ መሠረት ለአደጋ ተጎጂዎች መርጃ እንዲውሉ የሚሰጡ ዕቃዎችን፣ ተሽከርካሪዎችንና ሌሎች መጓጓዣዎችን፣ ምግቦችን፣ መድኃኒቶችን፣ አልባሳትን፣ ብርድ ልብሶችን፣ ድንኳኖችን፣ ተገጣጣሚ ቤቶችን፣ የውሃ ማጣሪያና ማጠራቀሚያዎችን እና ሌሎች ለኑሮ መሠረታዊ የሆኑ ዕቃዎችን ያጠቃልላል፡፡

b) stores for consumption necessary for its operation and maintenance, in such quantities as are deemed reasonable for operation and maintenance during the flight having regard also to any quantities of such stores already on board.

2/ Replenishment of stores exempted from duties and taxes shall be allowed for an aircraft which has arrived in the customs territory and which needs to replenish its stores for the journey to its final destination in the customs territory.

3/ The Authority shall allow stores for consumption supplied to an aircraft during its stay in the customs territory to be issued under the same conditions as are applicable in this Chapter to stores for consumption held on board arriving aircraft.

4/ The Authority may require a declaration of stores taken on board aircraft upon departure from the customs territory, containing minimum information necessary for the purpose of customs control.

46. <u>Other Disposal of Stores</u>

Stores on board aircraft or train having arrived in the customs territory shall be allowed:

1/ to be cleared for home use or to be placed under another customs procedure, subject to compliance with the conditions and formalities applicable in each case; or

2/ subject to prior authorization by the Authority, to be transferred respectively to other aircraft or train in international traffic.

## <u>CHAPTER SEVEN</u>

## <u>CONSIGNMENT FOR EMERGENCY RELIEF</u>

47. <u>Emergency Relief Consignment</u>

For the purpose of this Chapter, "emergency relief consignment" may include goods, vehicles and other means of transport, foodstuffs, medicaments, clothing, blankets, tents, prefabricated houses, water purifying and water storage items, and other goods of prime necessity, forwarded as aid, upon the request of the appropriate government body, to those affected by disaster.

**፵፰. <u>የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎች ስለሚስተናገዱበት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት</u>**

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎችን በሚመለከት፡-

ሀ) ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብ እንዲኖር ወይም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የመጨረሻው ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጊዜያዊ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብ፤

ለ) ዕቃዎቹ ከመድረሳቸው በፊት ዲክላራሲዮኑና ደጋፊ ሰነዶቹ እንዲቀርቡ፣ እንዲመረመሩና እንዲመዘገቡ በማድረግ ዕቃዎቹ እንደደረሱ እንዲለቀቁ፤

ሐ) ዕቃዎቹ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ ወይም ከጉምሩክ ጣቢያ ውጭ ሆነው እንዲስተናገዱ እና በዚህም ምክንያት ማንኛውም ክፍያ እንዳይጠየቅባቸው፤

መፍቀድ ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎችን በሚመለከት ምርመራ ለማካሄድና ናሙና ለመውሰድ የሚችለው ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ይሆናል፡፡

፫/ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ተላላፊ የሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎች ምንጊዜም ቅድሚያ ተሰጥቷቸው መስተናገድ አለባቸው፡፡

**፵፱. <u>ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለማድረግ</u>**

በሚመለከተው የመንግስት አካል ውሳኔ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ ወደ ውጭ የሚላኩ የአስቸኳይ ጊዜ የዕርዳታ ዕቃዎች ሊከፈልባቸው ይችል ከነበረው ቀረጥና ታክስ ነፃ ይደረጋሉ፡፡

## <u>ምዕራፍ ስምንት</u>

## <u>የጉምሩክ መጋዘን ሥነ ሥርዓት</u>

**፶. <u>ዕቃዎችን ወደ ጉምሩክ መጋዘን ስለማስገባት</u>**

፩/ ጉምሩክ ወደብ የደረሰ ማናቸውም ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን መግባት አለበት፡፡

፪/ ማናቸውም ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የገባ ዕቃ ዝርዝር ሁኔታው እየተገለፀ በመጋዘኑ መዝገብ ላይ ይመዘገባል፡፡

**48. <u>Customs Procedure for Clearance of Emergency Relief Consignment</u>**

1/ In the case of emergency relief consignments the Authority may allow:

a) lodging of a simplified goods declaration or of a provisional goods declaration subject to the production of final goods declaration within a specified period;

b) lodging, checking and registering of the goods declaration and supporting documents prior to the arrival of the goods, and their release upon arrival;

c) clearance outside the designated hours of business or away from customs stations and the waiver of any charges in this respect.

2/ The Authority may conduct examination or sampling of goods of emergency relief consignments in exceptional circumstances.

3/ Clearance of emergency relief consignments for import, export or transit shall be carried out as a matter of priority.

**49. <u>Exemption from Duties and Taxes</u>**

Consignments for emergency relief shall be imported or exported, upon decision of the appropriate government body, free of duties and taxes otherwise payable.

## <u>CHAPTER EIGHT</u>

## <u>CUSTOMS WAREHOUSE PROCEDURE</u>

**50. <u>Warehousing of Goods</u>**

1/ Goods arriving at any customs port shall be deposited in temporary customs storage or bonded customs warehouse.

2/ Particulars of goods stored in temporary customs storage shall be registered in the warehouse register book.

፫/ ማናቸውም ወደ ቦንድድ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ በመጋዘን ዲክላራሲዮን ተመዝግቦ ለባለሥልጣኑ መቅረብና መፈቀድ አለበት፡፡

፬/ በጊዜያዊ የጉምሩክ ማከማቻ ውስጥ የሚከማቹ ዕቃዎች ቅርጽና ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው መቆየታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ መያዝ አለባቸው፡፡

፭/ አደጋ ሊያስከትሉ፣ በሌሎች ዕቃዎች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ወይም አያያዛቸው ልዩ የመጋዘን ዝግጅት የሚጠይቅ ዕቃዎች ለዚሁ ዓላማ ተብለው በተለየ ሁኔታ ዲዛይን በተደረጉ የጉምሩክ መጋዘኖች ብቻ ይስተናገዳሉ፡፡

፮/ ወደ መጋዘን መግባት ያለባቸው ዕቃዎች ወደ ተባለው መጋዘን ያልገቡ እንደሆነ የመጋዘኑ ኃላፊ ይህንኑ እንዳወቀ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

፯/ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ በሚገባበት ጊዜ ሊጠየቅ የሚገባው ሰነድ ዕቃው ለባለሥልጣኑ በቀረበ ጊዜ ዕቃውን ለመለየት ያገለገለው ሰነድ ይሆናል፡፡

፰/ በጭነት መግለጫው ወይም በሌላ የንግድ ሰነድ የተገለጹት ዕቃዎች በሙሉ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የሚገቡ ከሆነ ባለሥልጣኑ የሚጠይቀው ሰነድ የጭነት መግለጫውን ወይም የንግድ ሰነዱን ይሆናል፡፡

**፶፩. <u>ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ስለሚቆዩበት ጊዜ</u>**

፩/ ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ትራንስፖርት ወደ አገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት አለበት፡፡

፪/ ማናቸውም በአየር ትራንስፖርት ወደ አገር የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት አለበት፡፡

፫/ የቀረጥ ነፃ መሸጫ መደብርን ሳይጨምር ወደጉምሩክ ቦንድ መጋዘን የገባ ማናቸውም የንግድ ዕቃ ወደመጋዘን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በ፬ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞበት ከመጋዘን መውጣት አለበት፡፡ ወደ ቀረጥ ነፃ መደብር የገባ ዕቃ የጉምሩክ ሥነሥርዓት የሚፈፀምበት ጊዜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

3/ Goods to be deposited in a bonded customs warehouse shall be entered in a warehouse declaration and presented to the Authority for approval.

4/ Goods stored in temporary customs storage shall be subject to such handlings which are necessary for ensuring their preservation without altering their form and nature.

5/ Goods which constitute a hazard, which are likely to affect other goods or which require special installations shall be accepted only by customs warehouses specially designed to receive them.

6/ Where delivery of the goods to the intended warehouse has not been made, the warehouse operator shall forthwith report to the Authority the non-delivery of the goods to the warehouse.

7/ The document to be required when goods are placed under temporary storage shall be that used to describe the goods when they are produced to the Authority.

8/ The Authority shall accept the cargo declaration or another commercial document as the document to be required to place the goods under temporary storage, provided that all the goods mentioned in that cargo declaration or that other commercial document are placed in a temporary store.

**51. <u>Time Limit of Storage in Customs Warehouse</u>**

1/ Goods imported by using sea or land transport and stored in a temporary customs storage shall undergo customs procedures and be removed within 60 days from the date of storage.

2/ Goods imported by using air transport and stored in a temporary customs storage shall undergo customs formalities and be removed within 30 days from the date of storage.

3/ Any commercial good other than goods in a duty free shop stored in customs bonded warehouse shall undergo customs procedures and be removed within four months from the date of storage. The period under which goods stored in a duty free shop have to undergo customs procedures shall be determined by regulation to be issued by the Council of Ministers.

፬/ ወደጉምሩክ ቦንድ መጋዘን የገባ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ለሚውሉ ምርቶች ማምረቻ የሚውል መሳሪያ፣ መለዋወጫ እና ግብዓት ወደመጋዘን ከገባበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞበት ከመጋዘን መውጣት አለበት፡፡

፭/ በስህተት ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የገባ የቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚ ድርጅት ዕቃ በ፲፪ የስራ ቀናት ውስጥ ወደ ጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን መተላለፍ አለበት፡፡

፮/ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከተከናወነበት በኋላ ከ፯ የሥራ ቀናት በላይ በማከማቻው ሊቆይ አይችልም፡፡

፯/ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪)፣ (፫)፣ (፬) እና (፭) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ካልወጣ ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወር ይደረጋል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች ከመወገዳቸው በፊት የዕቃው ባለቤት ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችን ከከፈለ እቃዎቹን በ፯ የሥራ ቀናት ውስጥ የመረከብ መብት ይኖረዋል፡፡

፱/ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ የተወሰነለት የመቆያ ጊዜው ከመድረሱ በፊት የመጋዘን ፈቃዱ ከተሰረዘ ቀሪውን ጊዜ ለማጠናቀቅ ወደ ሌላ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን እንዲዛወር ይደረጋል፡፡

፲/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሰረት ዕቃዎችን ወደ ሌላ የጉምሩክ መጋዘን ማዘዋወር የሚያስከትለውን ማናቸውንም ወጪ ፈቃዱ የተሰረዘበት የማከማቻ ባለቤት ይከፍላል፡፡

፲፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተወሰኑ የጊዜ ገደቦችን በበቂ ምክንያት ሊያራዝም ይችላል፡፡

## ፶፪. <u>ዕቃዎች ከጉምሩክ መጋዘን ስለሚወጡበት ሁኔታ</u>

፩/ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች በጉምሩክ ሕግ መሠረት ካልሆነና እንደአግባቡ ለሚከተሉት ዓላማዎች ሲባል ተመዝግበው ካልወጡ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ከማከማቻው ወይም ከመጋዘኑ ሊወጡ አይችሉም፡-

4/ Any machinery, equipment and input to be used for producing goods for domestic consumption and stored in custom bonded warehouse shall undergo customs formalities and be removed within one year from the date of storage.

5/ Goods owned by a person who is permitted to use bonded warehouse but mistakenly stored in temporary customs storage shall, within 12 working days, be transferred to the bonded warehouse.

6/ Goods stored in temporary customs storage or bonded warehouse may not be kept for more than 7 working days after the completion of customs formalities.

7/ Goods stored in temporary customs storage or bonded warehouse and not removed within the time limit specified in sub-article (1), (2), (3), (4) and (5) of this Article shall be transferred to government customs warehouse.

8/ If the owner of goods transferred to government customs warehouse pursuant to sub-article (7) of this Article pays the taxes and duties payable and other costs prior to their disposal, he shall have the right to take the goods within 7 working days from the date of such payment.

9/ Where the permit granted for a temporary customs storage or bonded warehouse is cancelled before the expiry of the time limit prescribed for storage of goods, the goods shall be transferred to another temporary customs storage or bonded warehouse for the remaining time of storage.

10/ Any expense for transferring goods to another customs warehouse pursuant to sub-article (7) of this Article shall be covered by the owner of the storage whose permit has been cancelled.

11/ The Authority may, for good cause, allow extension of the time limit provided for in this Article.

## 52. <u>Removal of Goods from Customs Warehouse</u>

1/ Goods stored in temporary customs storage or bonded customs warehouse may not be removed from such warehouse except in accordance with the customs law and upon due entry for any of the following purposes as may be appropriate:

ሀ) የሚፈለግባቸው ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ ሲለቀቁ፤

ለ) በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ለሚያመርት ፋብሪካ እንዲዛወሩ ሲፈቀድ፤

ሐ) ወደ ሌላ የጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወሩ ወይም በተላላፊነት እንዲወጡ ሲፈቀድ፤

መ) ወደ ውጭ እንዲላኩ ሲፈቀድ፤ ወይም

ሠ) ወደ ቀረጥ ነፃ መሸጫ መደብር እንዲገቡ ሲፈቀድ፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፴፪(፱) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከጉምሩክ መጋዘን ከመውጣቱ በፊት በአደጋ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የጥራት ደረጃው የቀነሰ፣ የተበላሸ ወይም የተጎዳ ዕቃ የጥራት ደረጃው መቀነሱ፣ መበላሸቱ ወይም መጎዳቱ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ የጥራት ደረጃው እንደቀነሰ፣ እንደተበላሸ ወይም እንደተጎዳ ይቆጠራል፡፡

## ፶፫. በትርፍነት ስለተገኘ ዕቃ

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፵፫(፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም የቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ሃላፊ በዕቃ ዲክላራሲዮኑ፣ በጭነት ማኒፌስት ወይም በትራንዚት ሰነድ ከተገለፀው መጠን በላይ ዕቃ ያገኘ እንደሆነ በትርፍ የተገኘውን ዕቃ ዲክላራሲዮኑ ለቀረበለት የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሪፖርት በቀረበበት ትርፍ ዕቃ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ ወዲያውኑ መከፈል አለበት፡፡

## ፶፬. በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ስለሚፈቀዱ ሥራዎች

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወስድ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የገቡ ዕቃዎች ባለቤት ወይም ባለይዞታ ወይም ዕቃዎችን የመቆጣጠር መብት ያለው ማንኛውም ሰው የዕቃዎችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚረዱ ሥራዎችን ወይም ዕቃዎቹን እንደገና የማሸግ፣ የመከፋፈል ወይም በየፈርጁ የመመደብ ሥራዎችን እንዲያከናውን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ፶፭. ለናሙና ወጪ ስለሚደረጉ ዕቃዎች

፩/ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎችን በሚከተሉት ምክንያቶች ለናሙና በሚሆን መጠን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከመጠናቀቁ በፊት ወጪ ማድረግ ይቻላል:-

ሀ) ዕቃውን በተገቢው ታሪፍ ለመመደብ ዓይነቱንና የተሰራበትን ጥሬ ዕቃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

a) released for home use upon payment of taxes and duty due thereon;

b) transferred to a factory manufacturing under customs control;

c) transferred to another customs warehouse or released for transit;

d) released for export; or

e) released for sale in the duty free shop.

2/ Without prejudice to the provision of Article 132 (9) of this Proclamation, goods deteriorated, spoiled or damaged by accident or force majeure before leaving the customs warehouse shall be considered as if they had been imported in their deteriorated, spoiled or damaged state; provided, however, that such deterioration, spoilage or damage is established to the satisfaction of the Authority.

## 53. Goods Found in Excess of Entry

1/ Without prejudice to the provision of Article 143 (2) of this Proclamation where the operator of a temporary customs storage or bonded customs warehouse finds goods in excess of entry in the goods declaration, cargo manifest or transit documents, he shall immediately report the excess to the branch of the Authority having received the goods declaration.

2/ The duties and taxes in respect of excess goods reported pursuant to sub-article (1) of this Article shall be paid forthwith.

## 54. Operations Permitted in Customs Warehouse

The Authority may, subject to such safeguards as it may consider necessary, authorize the owner, possessor or person having control over goods stored in temporary customs storage, to make operations necessary for the preservation of the goods or repacking, breaking bulk or grouping of packages.

## 55. Goods Taken for Sample

1/ Samples of goods stored in a customs warehouse may be removed from the warehouse in a quantity sufficient to:

a) ascertain the type and the material content of goods to classify them under the proper tariff headings;

ለ) የዕቃውን ዋጋ ለመተመን የዕቃውን ዓይነት፣ ጥራትና የተመረተበትን አገር ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

ሐ) የዕቃው ናሙና ለፍርድ ቤት ወይም ለፖሊስ ምርመራ እንዲቀርብ ሲታዘዝ፤

መ) በዋጋ ሰነዱ ላይ የተሰጠው ዋጋ ለተጠቀሰው ዕቃ መሆኑን ለማረጋገጥ፤

ሠ) የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በሚፈቅዳቸው ሌሎች ምክንያቶች፡፡

፪/ ለናሙና የተወሰዱ ዕቃዎች በወጡበት መጠንና ሁኔታ ሥራው እንደተጠናቀቀ ወደ መጋዘን መመለስ አለባቸው፡፡ ሆኖም በተፈጥሯቸው ወይም ለማነፃፀሪያ የሚፈለጉ በመሆናቸው ምክንያት ሊመለሱ የማይችሉ ሲሆን ለቀረጥና ታክስ እንዲሁም ለሌሎች ሂሳቦች አተማመን በመጋዘን ውስጥ እንዳሉ ይቆጠራል፡፡

**፶፮. በጉምሩክ መጋዘኖች ላይ ስለሚፈጸም የጉምሩክ ቁጥጥር**

፩/ ማንኛውም የጉምሩክ መጋዘንና ወደ መጋዘኑ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡

፪/ በባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ጉምሩክ መጋዘን መግባት አይችልም፡፡

፫/ በጉምሩክ መጋዘኖችና ወደ ጉምሩክ መጋዘን በገቡ ዕቃዎች ላይ የሚፈጸም የጉምሩክ ቁጥጥር የሚከተሉትን ለማረጋገጥ የሚወሰድ ማናቸውንም እርምጃ ይጨምራል፡-

ሀ) ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገቡና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞባቸው የሚለቀቁ ዕቃዎች ባለሥልጣኑ በወሰነው የመዝገብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መመዝገባቸውንና በየጊዜው ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩(፯) የተመለከቱት ዕቃዎች ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እንዲተላለፉ መደረጋቸውን፤

ሐ) ዕቃዎች እንደየአይነታቸውና እንደፀባሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለጉምሩክ ቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን፤

መ) የጉምሩክ መጋዘኑ በተሰጠው ፈቃድ መሰረት እየተሠራበት መሆኑን፡፡

b) ascertain the type, quality and origin of goods for valuation purpose;

c) satisfy a court or police order requiring the presentation of sample for inspection;

d) ascertain the price indicated on the invoice is actually related to the specified item;

e) other purposes determined by the Director General of the Authority.

2/ Goods removed as sample shall be returned in the same quantity and condition as soon as the purpose for which they are taken out is fulfilled; provided, however, that where it is not possible to return them due to their nature or due to their being used for analysis, it shall be presumed as they are warehoused for the purpose of assessment of duties, taxes and other charges.

**56. Customs Control on Customs Warehouses**

1/ Any customs warehouse and goods deposited in the warehouse shall be under customs control.

2/ No person, other than authorized by the Authority, may enter a customs warehouse.

3/ Customs control on customs warehouse and goods deposited in customs warehouse shall include any measure taken to ascertain the following:

a) the registration and periodical reporting, in accordance with the manner specified by the Authority, of goods stored in and cleared from a customs warehouse;

b) the transfer of goods referred to in Article 51(7) of this Proclamation to government customs warehouse;

c) the segregation of goods stored in a customs warehouse on the basis of their type and nature to enable their safe storage and accessibility for customs control;

d) the customs warehouse is operated in accordance with the permit given with respect to it.

## ፶፯. ዕቃዎችን ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ስለማስተላለፍ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩(፯) መሠረት ወደመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን መተላለፍ የሚገባቸው ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙበት ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ሃላፊ ዕቃዎቹን፡-

ሀ) ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን፤ ወይም

ለ) ባለሥልጣኑ ወደ ሚወስነው ሌላ ማከማቻ ቦታ ማዛወር፤

አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ሃላፊ ዕቃዎቹን ወደ መንግሥት መጋዘን ወይም ባለሥልጣኑ ወደ ሚወስነው ሌላ ማከማቻ ቦታ ማዛወር ያልቻለ እንደሆነ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) በመጋዘን ሃላፊው ወጪ ዕቃዎቹን ራሱ ማዛወር፤ ወይም

ለ) አስቀድሞ የሚወስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ዕቃዎቹ በነበሩበት መጋዘን እንዲቆዩ መወሰን፤

ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ የተያዙ ዕቃዎች፡-

ሀ) ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እንዲተላለፉ ሊያደርግ፤ ወይም

ለ) ተከማችተው በሚገኙበት የንግድ ቦታ እንዲቆዩ ለመወሰን፤

ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) መሠረት ዕቃዎች የተዛወሩበት ማከማቻ ቦታ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) (ለ) መሠረት እንዲቆዩበት የተደረገ መጋዘን ወይም የንግድ ቦታ እነዚህኑ ዕቃዎች በሚመለከት እንደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ይቆጠራል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት እንደ መንግሥት ጉምሩክ መጋዘን የተቆጠረ መጋዘን፣ ማከማቻ ቦታ ወይም የንግድ ቦታ ሃላፊ ለዕቃዎቹ ደህንነትና ለቀረጥና ታክሱ ሃላፊ ይሆናል፡፡

## 57. Transfer of Goods to Government Customs Warehouse

1/ The operator of a temporary customs storage where goods to be transferred to government customs warehouse in accordance with Article 51(7) of this Proclamation are stored shall transfer the goods to:

a) government customs warehouse; or

b) any other storage place designated by the Authority.

2/ Where the operator referred to in sub-article (1) of this Article fails to transfer the goods to the government customs warehouse or to the storage place designated by the Authority, the Authority may:

a) itself transfer the goods at the cost of the warehouse operator;

b) decide the goods to remain in such warehouse subject to certain conditions prescribed by the Authority.

3/ Where goods are seized due to contravention of customs law, the Authority may:

a) transfer the goods to government customs warehouse; or

b) decide the goods to remain in business premises where they are stored.

4/ The storage place where goods are transferred pursuant to sub-article (1) (b) of this Article or the warehouse or business premises where goods are stored pursuant to sub-article (2) (b) or (3) (b) of this Article shall be deemed to be a government customs warehouse with respect to such goods.

5/ The person in charge of the warehouse, storage place or business premises deemed to be a government customs warehouse pursuant to sub-article (4) of this Article shall be responsible for the safety of the goods as well as for the duties and taxes thereon.

**፶፰. የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን መዝገብ**

፩/ ባለሥልጣኑ በመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ወይም እንደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን በሚቆጠር መጋዘን፣ ማከማቻ ቦታ ወይም የንግድ ቦታ የተከማቹ ዕቃዎችን በሚመለከት የሚከተሉትን መረጃዎች መዝግቦ መያዝ አለበት፡-

ሀ) የዕቃውን ዝርዝር፤

ለ) የዕቃውን መለያ ምልክት፤

ሐ) የአስመጪውን ወይም የላኪውን ስምና አድራሻ፤

መ) ያጓጓዡን ስምና አድራሻ፤

ሠ) ዕቃዎቹ የተከማቹበትን የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ወይም እንደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የተቆጠረውን መጋዘን፣ የማከማቻ ቦታ ወይም የንግድ ቦታ ስያሜና አድራሻ፤ እና

ረ) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን።

፪/ ባለሥልጣኑ ከዕቃዎቹ ወደ አገር ውስጥ መግባት ወይም ወደ ውጭ መላክ እና መጓጓዝ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ቅጅ መውሰድና መያዝ አለበት።

**፶፱. ስለመጋዘን ኪራይ**

፩/ የመጋዘን ኪራይ እንደሚከተለው ይታሰባል:-

ሀ) ለኪራይ አገልግሎት ወደ ተቋቋመ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸው እስከሚለቀቁ ወይም ወደ ሌላ የጉምሩክ መጋዘን እስከሚዛወሩ ለቆዩበት ጊዜ፤

ለ) ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች:-

(፩) የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ ተይዘው ወይም በባለቤቱ ተትተው የተወረሱ ከሆኑ ከተሸጡበት ጊዜ ጀምሮ ገዢው እስከሚረከብ ለቆዩበት ጊዜ፤

(፪) የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ ተይዘውና ተወርሰው ከሽያጭና ከስጦታ ውጪ በሌላ መንገድ የሚወገዱ ከሆነ ወደመጋዘኑ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚወገዱ ለቆዩበት ጊዜ፤

(፫) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩(፯) መሠረት ወደ መጋዘኑ የገቡ ከሆነ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸው እስከሚለቀቁ ወይም ተሸጠው ገዢው እስከሚረከብ ለቆዩበት ጊዜ።

**58. Government Customs Warehouse Records**

1/ The Authority shall keep records of goods stored in a government customs warehouse or in a warehouse, storage place or business premises deemed to be government customs warehouse, containing the following particulars:

a) description of the goods;

b) distinguishing marks of the goods;

c) the name and address of the importer or exporter;

d) the name and address of the carrier;

e) the designation and address of the government customs warehouse or the warehouse, storage place or business premises where the goods are stored; and

f) other necessary information.

2/ The Authority shall take and keep copies documents relating to the importation or exportation and carriage of the goods.

**59. Warehouse Fee**

1/ Warehouse fees shall be calculated as follows:

a) for goods stored in a temporary customs storage or bonded customs warehouse, established for rental use, from the date of deposit until released upon completion of customs procedures or their transfer to another customs warehouse;

b) for goods stored in government customs warehouse:

(1) if they are forfeited upon seizure due to contravention of the customs law or forfeited due to being abandoned by the owner, from the date of sales until the buyer takes delivery of them;

(2) if they are disposed otherwise than by sale or donation upon being seized and forfeited due to contravention of the customs law, from the date of deposit until disposal;

(3) if they are stored in the warehouse pursuant to Article 51(7) of this Proclamation, from the date of deposit until released upon completion of customs procedures or until the buyer takes delivery of them in case of sale.

፪/ የጉምሩክ መጋዘን ኪራይ ማስከፈያ ተመን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

፫/ በዋስትና ሊለቀቁ የማይችሉ የተያዙ ዕቃዎች ባለቤቱ እንዲወስዳቸው በዚህ አዋጅ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ ውሳኔው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ በመጋዘን ለቆዩበት ጊዜ የመጋዘን ኪራይ አይከፈልባቸውም፡፡ በዚህ አይነት ባለቤቱ እንዲወስዳቸው የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጣቸው ዕቃዎች ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተፈፅሞባቸው ከመጋዘን መውጣት አለባቸው፡፡

፬/ በዋስትና ሊለቀቁ የማይችሉ የተያዙ ዕቃዎች በተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን የነበሩ ከሆነ ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን ተዛውረው መቆየት አለባቸው፡፡

## ፷. ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን እያሉ የባለቤትነት መብት ስለማስተላለፍ

፩/ ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ እያሉ የባለቤትነቱ መብት ወደ ሌላ ሰው እንዲተላለፍ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፴ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ እያሉ የባለቤትነት መብቱ የተላለፈለት ሰው ከዕቃዎቹ ጋር በተያያዘ በቀድሞው ባለቤት ላይ በህግና በውል የተጣሉ ግዴታዎችንና ገደቦችን እንዲሁም በህግ መሠረት የተሰጡ ውሳኔዎችን ማክበር ይኖርበታል፡፡

## ፷፩. የተተው ዕቃዎችን ስለማስወገድ

፩/ የጉምሩክ ህግ መተላለፍ ያልተፈጸመባቸውና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ባለቤቱ በጽሑፍ እንደማይወስዳቸው ገልጾ የተዋቸው ዕቃዎች፡-

ሀ) የገበያ ዋጋ ያላቸው ከሆነ ባለሥልጣኑ በሽያጭ ያስወግዳቸዋል፤ ወይም

ለ) የገበያ ዋጋ የሌላቸው ከሆነ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ዘዴዎች እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡

፪/ የጉምሩክ ህግ መተላለፍ ያልተፈጸመባቸውና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ (፯) መሠረት ወደመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች የአንቀጽ ፶፩ (፭) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

2/ The rate of customs warehouse fees shall be determined by regulation of the Council of Ministers.

3/ Seized goods that could not be released against security shall be exempted from warehouse charge from the date of seizure until released by a final decision in accordance with this Proclamation. Such goods shall be removed from the warehouse within two months from the date the final decision for their release is rendered.

4/ If goods that could not be released against security are stored in a licensed customs warehouse, they shall be transferred and stored in government customs warehouse.

## 60. Transfer of Ownership of Goods in Customs Warehouse

1/ The Authority may permit transfer of ownership to another person while the goods are stored in customs warehouse.

2/ Without prejudice to Article 130 of this Proclamation, the person to whom ownership of goods stored in customs warehouse is transferred shall have the obligation to observe the obligations and restrictions imposed on the previous owner by virtue of the law or contract in connection with goods as well as decisions rendered in accordance with the law.

## 61. Disposal of Abandoned Goods

1/ Goods abandoned by the owner in writing before the expiry of the period stipulated under Article 51 (1), (2) or (3) of of this Proclamation and not related to a contravention of customs law shall be disposed by the Authority:

a) by way of sale if they have market value; or

b) by other means to be determined by directive of the Authority if they have no market value.

2/ Goods transferred to government customs warehouse pursuant to Article 51 (7) of this Proclamation and not related to a contravention of customs law shall, without prejudice to Article 51 (5), be disposed by the Authority:

ሀ) የገበያ ዋጋ ያላቸው ከሆኑ ባለሥልጣኑ በሽያጭ ያስወግዳቸዋል፤ ወይም

ለ) የገበያ ዋጋ የሌላቸው ከሆኑ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ዘዴዎች እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡

**፷፪. የተወረሱ ዕቃዎችን ስለማስወገድ**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተወረሱ ዕቃዎች፡-

ሀ) የገበያ ዋጋ ያላቸው ከሆኑ ባለሥልጣኑ በሽያጭ ያስወግዳቸዋል፤ ወይም

ለ) በህግ በተደነገገ ክልከላ ወይም ገደብ ምክንያት በጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ወይም የገበያ ዋጋ የሌላቸው ከሆኑ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ዘዴዎች እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) አግባብ ባለው ህግ መሠረት ቅርስ ሊባሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ወይም ሚኒስቴሩ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል የሚላቸውን ዕቃዎች አግባብነት ላለው የመንግስት አካል ያስተላልፋል፤

ለ) ለሰብዓዊ እርዳታ ሊውሉ የሚችሉ እቃዎችን አግባብ ላላቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

**፷፫. የሽያጭ ሥርዓት**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ ወይም አንቀጽ ፷፪ መሠረት የሚፈጸም የዕቃዎች ሽያጭ የሃራጅ ወይም የግልጽ ጨረታ ሥርዓትን የተከተለ ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅት አማካኝነት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሸጡ ዕቃዎች የባለቤትነት መብት ለገዥው እንዲተላለፍ የሚያስችል ማስረጃ መስጠት አለበት፡፡

**፷፬. የሽያጭ ገቢና የማስወገጃ ወጪዎች**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ (፩) (ሀ) ወይም ፷፪ (፩) (ሀ) መሠረት የተገኘ የሽያጭ ገቢ ከዕቃዎቹ ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ የከፈላቸው ወጪዎች ተቀንሰው ተራፊው ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ (፪) (ሀ) መሠረት የተገኘ የሽያጭ ገቢ፡-

ሀ) የቀረጥና ታክስ ሂሳብ፤

a) by way of sale if they have market value; or

b) by other means to be determined by directive of the Authority if they have no market value.

**62. Disposal of Forfeited Goods**

1/ Goods forfeited in accordance with this Proclamation shall be disposed by the Authority:

a) by way of sale if they have market value; or

b) by other means to be determined by directive of the Authority if they cannot be used due to legal prohibition or restriction or if they have no market value.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) (a) of this Article, the Authority:

a) shall transfer goods classified as cultural heritage by the relevant law or goods that the Ministry determines to be used by public bodies to the appropriate government body;

b) may transfer goods to be used for humanitarian aid to the appropriate charity organizations.

**63. Procedures of Sale**

1/ Sale of goods in accordance with Article 61 or Article 62 of this Proclamation shall follow auction or open tender procedures or sale through a public enterprise.

2/ The Authority shall provide the buyer of goods sold pursuant to sub-article (1) of this Article with evidence that enable transfer of ownership.

**64. Proceeds of Sale and Cost of Disposal**

1/ The proceeds obtained from the sale of goods under Article 61(1) (a) or Article 62 (1) (a) of this Proclamation shall, after deducting expenses incurred by the Authority in relation to the goods, be paid to the government.

2/ The proceeds obtained from the sale of goods under Article 61(2)(a) of this Proclamation shall, after deducting:

a) duties and taxes;

ለ) ከዕቃዎቹ ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ የከፈላቸው ወጪዎች፣

ሐ) የመጋዘን ኪራይ እና የማጓጓዣ ወጪ፣ እና

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) በተመለከቱት ሂሳቦች ላይ በባንክ የማበደሪያ ተመን መሠረት የሚሰላ ወለድ፣

እንደ ቅደም ተከተሉ ተቀንሶ ተራፊው ለዕቃዎቹ ባለቤት ተመላሽ ይደረጋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ተመላሽ የሚደረገው ገንዘብ ባለመብት ሽያጩ በተፈፀመ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልጠየቀ ገንዘቡ ለመንግሥት ፈሰስ ይደረጋል።

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ (፩)(ለ) ወይም (፪)(ለ) ወይም አንቀጽ ፷፪(፩)(ለ) መሠረት ዕቃዎችን ለማስወገድ ባለሥልጣኑ ያወጣውን ወጪ እንደሁኔታው ከዕቃዎቹ ባለቤት ወይም ጥፋተኛ ከሆነው ሰው የማስመለስ መብት ይኖረዋል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው ወደ ውጭ ተመልሰው ስለሚላኩ ወይም ወደ አገር ውስጥ ተመልሰው ስለሚገቡ እቃዎች

### ፷፭. የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው ወደ ውጭ ለመላክ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች

፩/ የምርት ሂደታቸውን በአገር ውስጥ እንዲያጠናቅቁ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡና ከነዚሁ የተገኙ የማካካሻ ምርቶች ወደ ውጭ አገር እንዲላኩ የሚፈቀድበት ሁኔታ በውጭ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት መሠረት ይፈጸማል።

፪/ ዕቃዎች የጥገና ሂደታቸውን በአገር ውስጥ እንዲያጠናቅቁ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው መውጣት አለባቸው። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ባለሥልጣኑ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል።

### ፷፮. የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው እንዲመለሱ ወደ ውጭ አገር ስለሚላኩ ዕቃዎች

፩/ ዕቃዎች የምርት ሂደታቸውን በውጭ አገር

b) expenses incurred by the Authority in relation to the goods;

c) the warehouse fee and transportation expenses; and

d) interest calculated at bank lending rate on the amounts referred to under paragraphs (a), (b) and (c) of this sub article;

in the preceding order be paid to the owner of the goods.

3/ If the amount of refund referred to in sub-article (2) of this Article is not claimed by the owner of the goods within six months from the date of sale of the goods, it shall be surrendered to the government.

4/ The Authority shall have the right to claim reimbursement of the costs of disposal of goods under Article 61(1) (b) or (2) (b) or Article 62(1) (b) of this Proclamation from the owner of the goods or from the offender, as the case may be.

## CHAPTER NINE

## CUSTOMS PROCEDURE FOR INWARD OR OUTWARD PROCESSING

### 65. Inward Processing

1/The authorization of temporary importation of goods for manufacturing or processing and the exportation of compensating products resulting thereof shall be governed by the Export Trade Duty Incentive Schemes.

2/Goods may be temporarily imported for repair at home.

3/Goods temporarily imported pursuant to sub-article (2) of this Article shall be re-exported within six months from the date of their importation; provided, however, that the Authority may authorize the extension of such period where necessary.

### 66. Outward Processing

1/ Goods may, upon authorization by the Authority in accordance with directive of the Ministry, be

እንዲያጠናቅቁ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር ሊላኩ ይችላሉ፡፡

፪/ ዕቃዎች በአገር ውስጥ ለመጠገን የማይችሉ መሆናቸው ተረጋግጦ በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ በውጭ አገር ተጠግነው እንዲመለሱ በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር ሊላኩ ይችላሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት በጊዜያዊነት ወደ ውጭ የተላኩ ዕቃዎች የምርት ወይም የጥገና ሂደት ውጤት የሆኑ የማካካሻ ምርቶች ዕቃዎቹ በጊዜያዊነት ከተላኩ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ አገር ውስጥ ተመልሰው መግባት አለባቸው፤ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም ወጪ ዕቃዎችን የሚመለከቱ ቅድመ ሁኔታዎችና ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው እንዲመለሱ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር የተላኩበትን ሥነ ሥርዓት የቀጥታ ወደ ውጭ መላክ የዕቃ ዲክላራሲዮን በማቅረብ እንዲቋረጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

## ፷፯. የቀረጥና ታክስ ክፍያ

፩/ የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው እንዲመለሱ በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ አይከፈልባቸውም፡፡ ሆኖም የማካካሻ ምርቶቹ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ (፫) መሠረት ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ ካልገቡ በዕቃዎቹ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከሚወሰን ቅጣት ጋር የሚከፈል ይሆናል፡፡

፪/ በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማካካሻ ምርቶች ወደ ውጭ አገር ሲላኩ ወይም ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ በዕቃዎቹ ላይ የሚፈለግባቸው ቀረጥና ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ አወሳሰን ዘዴ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡ ሆኖም የጥገና ውጤት የሆኑ ማካካሻ ምርቶችን የሚመለከት ቀረጥና ታክስ የሚሰላው በጥገና ወጪው ላይ ተመሥርቶ ይሆናል፡፡

temporarily exported for manufacturing or processing abroad.

2/ Goods may, upon authorization by the Authority after ascertaining that they cannot be repaired at home, be temporarily exported for repairing abroad.

3/ Compensating products resulting from the manufacturing, processing or repair of goods temporarily exported pursuant to sub-article (1) or (2) of this Article shall be re-imported within a year from the date of the temporary export of the goods; provided, however, that the Authority may authorize the extension of such period where necessary.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (3) of this Article, the outward processing may be terminated by declaring the goods for outright exportation subject to compliance with the conditions and formalities applicable to the exportation of goods.

## 67. Duties and Taxes

1/ The temporary export of goods for outward processing shall be exempt for payment of duties and taxes; provided, however, that the duty and tax applicable to the goods together with penalties determined by directive of the Ministry shall be payable if the compensating products are not re-imported in accordance with Article 66 (3) of this Proclamation.

2/ Without prejudice to provisions of other laws, the exportation or importation of compensating products shall be subject to the payment of duties and taxes applicable to such goods.

3/ The method of calculation of duties and taxes payable under sub-article (1) of this Article shall be prescribed by directive of the Ministry; provided, however, that the duties and taxes relating to compensating products resulting from repairing shall be calculated on the basis of cost of the repair.

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው እንዲመለሱ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ወይም ወደ ውጭ አገር የተላኩ ዕቃዎች ለውጥ ሳይደረግባቸው በነበሩበት ሁኔታ የሚመለሱ ወይም ያለክፍያ ተጠግነው የሚመለሱ ከሆነ ቀረጥና ታክስ አይከፈልባቸውም፡፡

## ምዕራፍ አሥር

## ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ለአገር ውስጥ ፍጆታ የምርት ሂደታቸውን እንዲያጠናቅቁ ስለሚደረግበት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

### ፷፰. ሥነ ሥርዓቱ በጥቅም ላይ እንዲውል ስለመፍቀድ

፩/ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የምርት ሂደታቸውን እንዲያጠናቅቁ በባለሥልጣኑ ሊፈቀድ የሚችለው፡-

ሀ) አሠራሩ የሂደቱ ውጤት የሆኑትን ምርቶች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ከተደረጉት ዕቃዎች የተገኙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሲሆን፤ እና

ለ) የምርት ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ዕቃዎቹን ቀድሞ ወደነበሩበት ሁኔታ መልሶ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲሰጡ ለማድረግ የማይቻል ሲሆን፤

ነው፡፡

፪/ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የምርት ሂደታቸውን እንዲያጠናቅቁ በማድረግ ተግባር ላይ በመደበኛነት ለሚሠማራ ሰው ሂደቱን የሚሸፍን አጠቃላይ ፈቃድ ባለሥልጣኑ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ሊደረጉባቸው የሚችሉ ዕቃዎች ዓይነት፣ ፈቃድ ለመስጠት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና የጉምሩክ ቁጥጥሩን የሚመለከቱ እርምጃዎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

፬/ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የምርት ሂደታቸውን እንዲያጠናቅቁ የማድረግ ተግባር የዕቃዎቹ አስመጪ ከሆነው ሰው ውጪ በሌላ ሰው እንዲከናወን የሚፈቀድበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

4/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article goods temporarily imported or exported for inward or outward processing shall be re-exported or re-imported with exemption from duties and taxes if they are returned in the same state or after being repaired free of charge.

## CHAPTER TEN

## CUSTOMS PROCEDURE FOR PROCESSING OF IMPORTED GOODS FOR HOME USE UNDER CUSTOMS CONTROL

### 68. Authorization to Use the Procedure

1/ The Authority may authorize the processing of imported goods, under customs control, before clearance for home use if:

a) the operation allows to ascertain that the products resulting from the processing of goods for home use have been obtained from the imported goods; and

b) the original state of the goods cannot be economically recovered after the processing.

2/ The Authority may grant to a person who carries out regular processing of imported goods for home use, under customs control, general authorization covering his operations.

3/ The categories of goods to which the provisions of sub-article (1) and (2) of this Article may be applied, the requirements to be fulfilled to grant authorization and the measure constituting the customs control shall be specified by directive to be issued by the Authority.

4/ The conditions of authorization of processing of imported goods for home use, under customs control, by a person other than the importer of the goods shall be prescribed by directive to be issued by the Authority.

### ፷፱. የቀረጥና ታክሱ አከፋፈል

ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የምርት ሂደታቸውን እንዲያጠናቅቁ ሲደረግ እነዚህ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲለቀቁ የሚችሉት ምርቶቹን ለማምረት ወደአገር ውስጥ በገቡት ጥሬ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል በሚገባው ታሪፍ መሠረት ቀረጥና ታክስ ከተከፈለ በኋላ ይሆናል፡፡

### 69. Payment of Duties and Taxes

The products obtained from the processing of imported goods, before clearance for home use, under customs control, shall be liable to the import duties and taxes payable on the raw materials as an input for such products before sale for domestic consumption.

### ፸. ሥነ ሥርዓቱ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

፩/ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ከመለቀቃቸው በፊት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው የምርት ሂደታቸውን እንዲያጠናቅቁ የሚደረግበት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ወደአገር የገቡት ጥሬ ዕቃዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ መሠረት ቀረጥና ታክሱ ተከፍሎባቸው ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲለቀቁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ መሠረት የተፈቀደው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ይቋረጣል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ምክንያት ኖሮ ወደአገር የገቡት ጥሬዕቃዎች ሌላ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈጸምባቸው በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ መሠረት የተፈቀደው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ይቋረጣል፤ ሆኖም ተፈጻሚ እንዲሆን የሚፈቀደውን ሌላውን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎችና ገደቦች መከበር ይኖርባቸዋል፡፡

### 70. Termination of the Procedure

1/ The customs procedure authorized under Article 68 of this Proclamation shall terminate where the raw materials imported under customs control are cleared for home use upon payment of the applicable duties and taxes in accordance with Article 69 of this Proclamation.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the customs procedure authorized under Article 69 of this Proclamation shall terminate where the Authority, on the basis of justifiable grounds, authorize the placing of the raw materials imported under another customs procedure, subject to compliance with the conditions and formalities applicable to the later procedure.

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡበት ወይም ወደ ውጭ አገር ስለሚላኩበት እና ተመልሰው ስለሚገቡበት ወይም ስለሚላኩበት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

## CHAPTER ELEVEN

## CUSTOMS PROCEDURE FOR TEMPORARY IMPORTATION OR EXPORTATION AND RE-IMPORTATION OR RE-EXPORTATION OF GOODS

### ፸፩. በጊዜያዊነት ዕቃዎችን ስለማስገባት

፩/ ንግድን ከማስተዋወቅ፣ ከቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ከቱሪዝምና ከባሕል ልውውጥ፣ ከግንባታ ሥራ፣ ከምክር አገልግሎት ወይም ከዕርዳታ ሥራ ጋር የተያያዙ ዕቃዎች የመጡበት ምክንያት እንደተጠናቀቀ በመጡበት አኳኋን እንዲወጡ ሆኖ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በዋስትና በጊዜያዊነት እንዲገቡ በባለሥልጣኑ ሊፈቀድ ይችላል፤ ሆኖም መለዋወጫዎችና ሌሎች አላቂ እቃዎች በጊዜያዊነት ሊገቡ አይችሉም፡፡

### 71. Temporary Importation

1/ Goods necessary for trade promotion, technology transfer, tourism and cultural exchange, construction works, consultancy services or relief may temporarily be imported, upon the authorization of the Authority and upon furnishing security, without payment of duties and taxes subject to their re-export at the completion of such tasks; provided, however, that spare parts and other consumable goods may not be temporarily imported.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ውጪ እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡባቸው ሌሎች ሁኔታዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ዕቃዎች በሌላ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተመደቡ ዕቃዎችንም እንዲጨምር ሊደረግ ይችላል፡፡

፬/ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባን ዕቃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ከተደረገበት ዓላማ ውጪ በጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ነው፤ ሆኖም በጉምሩክ ክልል ቆይታ ጊዜው የዕቃውን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ተግባራት ሊከናወኑበት ይችላል፡፡

፭/ ከግንባታ ሥራዎች ወይም ከምክር አገልግሎት ጋር በተያያዘ በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎች አገር ውስጥ እንዲቆዩ በተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ ዕቃዎቹን በጊዜያዊነት ለማስገባት መብት ላላቸው ሰዎች እንዲተላለፉ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፮/ በጊዜያዊነት ገብተው ተመልሰው በሚወጡ ያገለገሉ ዕቃዎች እርጅና ዋጋ ላይ ዕቃዎቹ ሲወጡ ባለው ታሪፍ መሰረት ቀረጥና ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

፯/ በጊዜያዊነት ያስገባውን ዕቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ለሌላ የሚያስተላልፍ ሰው ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እስከተላለፈበት ጊዜ ድረስ በሚታሰበው የእርጅና ቅናሽ ላይ ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፰/ ከፕሮጀክት ሥራዎች ጋር በተያያዘ በጊዜያዊነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች አገልግሎት ላይ የዋሉበት ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ለተከናወነው ስራ የመጨረሻ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ወይም የፕሮጀክቱ ጊዜ ከተራዘመ ይህንኑ የፕሮጀክቱ ባለቤት ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት፡፡

፱/ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች በአገር ውስጥ የሚቀሩበት ሁኔታና የቀረጥና ታክስ ክፍያው አፈፃፀም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፸፪. ዕቃዎች በጊዜያዊነት እንዲገቡ ስለማይፈቀድበት ሁኔታ**

፩/ ዕቃዎች ተለይተው በማይታወቁበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ፈቃድ ላይሰጥ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ የዕቃዎቹ ተለይተው አለመታወቅ ዕቃዎቹ

2/ The Ministry may, by directive determine conditions other than those stated under sub article (1) of this Article under which temporary importation of goods without payment of duties and taxes may be permitted.

3/ Temporary importation pursuant to sub-article (1) or (2) of this Article may also be granted for goods already placed under another customs procedure.

4/ It is prohibited to use goods imported on temporary basis other than the purpose for which they are imported; provided, however, that they shall be allowed to undergo operations necessary for their preservation during their stay in the customs territory.

5/ The Authority may permit the transfer of temporarily imported goods for construction works or consultancy services, within the authorized period, to other duty free right holders with respect to similar goods.

6/ Duties and taxes shall be paid on the depreciated values of temporarily imported goods upon their re-exportation based on the tariff currently applicable.

7/ Any person who transfers temporarily imported goods to another person in accordance with sub article (5) of this Article shall have the obligation to pay duties and taxes on the depreciated value of the goods calculated for the period from the date of importation until the date of transfer.

8/ The project owner where temporarily imported goods, without payment of duties and taxes, are deployed shall inform the authority, in writing, the completion of the project, prior to settlement of final payments, or any period of extension of the project.

9/ The conditions under which temporarily imported goods may be allowed to remain at home and the manner of payment of duties and taxes shall be determined by the directive to be issued by Ministry.

**72. Refusal of Authorization**

1/ The Authority may refuse to authorize the use of temporary importation procedure where it is impossible to identify the goods.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Authority may authorize the use of

ካላቸው ተፈጥሯዊ ባህሪና ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ በሥርዓቱ ያለአግባብ የመጠቀም ሁኔታ ሊከሰት ያለመቻሉን ካረጋገጠ ዕቃዎቹ በጊዜያዊነት እንዲገቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ፸፫. <u>በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎች አገር ውስጥ የሚቆዩበት ጊዜ</u>

፩/ ከቱሪዝምና ከባህል ልውውጥ ወይም ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር የተያያዙ ዕቃዎች ወደ አገር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው መውጣት አለባቸው፡፡

፪/ ንግድ ለማስተዋወቅ የገቡ ዕቃዎች የማስተዋወቁ ተግባር በተጠናቀቀ በሁለት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ መውጣት አለባቸው፡፡

፫/ ለግንባታ ሥራ፣ ለምክር አገልግሎት፣ ከእርዳታ ሥራ ጋር በተያያዘ ወይም በፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች በፕሮጀክቱ ስምምነት የተገለፀው የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ወይም ፕሮጀክቱ ወይም የእርዳታ ሥራው እንደተጠናቀቀ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ተመልሰው መውጣት አለባቸው፡፡

፬/ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ በዚህ አዋጅ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ተመልሶ ከአገር ሊወጣ የማይችል መሆኑን አስመጪው ከጠየቀና በቂ ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ባለሥልጣኑ የጊዜ ገደቡን ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ዕቃው አገር ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግሥት ገቢ ተደርጐ በዕቃው ላይ ተገቢው የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖበት አገር ውስጥ ሊቀር ወይም ከአገር ሊወጣ ይችላል፡፡

፮/ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ከመንግሥት አካላት ውጪ በሆነ ማንኛውም ሰው በቀረበ ክስ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በመያዙ ምክንያት ተመልሶ ሊወጣ ካልቻለ ተመልሶ የሚወጣበት የጊዜ ገደብ መቆጠሩ ዕቃው ተይዞ በቆየበት ጊዜ መጠን ይቋረጣል፡፡

## ፸፬. <u>በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከቀረጥ ነፃ ስለማድረግ</u>

ሚኒስቴሩ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከቀረጥ ነፃ ሊሆኑ ስለሚችሉበት ሁኔታ ሊወስን ይችላል፡፡

temporary importation procedure where, in view of the nature of the goods or of the operations to be carried out, the absence of identification measures is not liable to give rise to any abuse of the procedure.

## 73. <u>Time Limit for Temporarily Imported Goods to Stay at Home</u>

1/ Imported goods for tourism, cultural exchange or technology transfer shall be re-exported within six months.

2/ Imported goods for trade promotion and welfare services shall be re-exported within two months from the date of completion of the trade promotion or welfare service.

3/ Imported goods for construction works, consultancy services, welfare services or as per a project agreement shall be re-exported within the period specified in the project agreement or within three months after the completion of the project or welfare services.

4/ The Authority may extend the time limit where the importer proves on acceptable ground that the goods imported temporarily cannot be re-exported within the specified time.

5/ The security provided for temporarily imported goods shall be transferred to the government treasury and the goods may, upon the completion of the appropriate customs formalities, remain in the country or be re-exported, if the goods are not re exported within two months after the completion of the specified period, unless the period is extended in accordance with sub-article (4) of this Article.

6/ When temporarily imported goods cannot be re-exported as a result of a seizure other than a seizure made at the suit of private persons, the requirement of re-exportation shall be suspended for the duration of the seizure.

## 74. <u>Total or Partial Relief for Temporary Admission</u>

The Ministry may determine the conditions under which the temporary admission procedure may be used with partial or total relief from import duties.

**፸፭. በጊዜያዊነት ወጥተው የሚመለሱ ዕቃዎች**

፩/ በሚከተሉት ምክንያቶች በጊዜያዊነት ለመውጣት የጉምሩክ ፎርማሊቲ የተከናወነባቸው ዕቃዎች ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ተመልሰው መግባት ይችላሉ:-

ሀ) ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሄደ ሰው የሄደበትን ሥራ ለማከናወን የተጠቀመባቸው ተሽከርካሪዎች፣ መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች፤

ለ) ለንግድና ለባህል፣ ወይም ለማናቸውም ዓይነት ትርዒቶች ወይም ኤግዚቢሽኖች ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች::

፪/ በሚኒስቴሩ በወጣ መመሪያ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር ወጥተው ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው መግባት የሚችሉት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው የመጡ እንደሆነ ነው::

**፸፮. ተመልሰው ስለሚወጡና ተመልሰው ስለሚገቡ እቃዎች**

፩/ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ተብሎ የተመዘገበ ዕቃ ያልተከለከለ ወይም አገባቡ የጉምሩክ ህግን የማይፃረር ከሆነ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከመከናወኑ በፊት ወደ ውጭ ተመልሶ እንዲወጣ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ የቀረጥና ታክሱን ፭ በመቶ ተከፍሎበት እንዲወጣ ሊፈቀድ ይችላል::

፪/ የአገር ውስጥ ምርት ሆነው ወደ ውጭ ከተላኩ በኋላ በሽያጭ ውሉ ወይም በንግድ ግንኙነት የተመለከተውን የጥራት ደረጃ ባለማሟላታቸው ምክንያት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ:: ሆኖም ለእነዚህ ዕቃዎች ማምረቻ በዋለው ግብዓት ላይ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ በተደነገገው መሠረት ሳይከፈል ቀርቶ የነበረው ቀረጥና ታክስ መከፈል አለበት::

፫/ በባለጉዳዩ ጥያቄ መሠረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በአሳማኝ ምክንያት ሊራዘም ይችላል::

**፸፯. ዕቃን በጊዜያዊነት የማስገባት ወይም የማስወጣት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ**

እንደ አግባቡ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎችን የሚመለከቱ ቅድመ ሁኔታዎችና ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ዕቃዎች በጊዜያዊነት የገቡበትን ወይም የወጡበትን ሥነ ሥርዓት

**75. Temporary Export and Re-Importation of Goods**

1/ Goods exported temporarily by completing customs formalities for the following reasons may be allowed to re-enter the country without payment of duties and taxes:

a) vehicles, equipment and machinery taken out by a person for the purpose of carrying out his work abroad;

b) goods exported for trade fair, exhibition or cultural show.

2/ Goods may be eligible for exemption from duties if returned from abroad within one year, unless a longer period is specified in a directive issued by the Ministry.

**76. Re-Exportation and Re - Importation of Goods**

1/ Goods imported and declared for home use that are not prohibited or the entrance of which is not contrary to the customs law may be re-exported at the request of the importer before completing customs formalities upon payment of 5% of the duties and taxes to be paid on the goods.

2/ Exported domestic goods that have been returned within one year because of their failure to meet the quality standards specified by the contract of sale or business relation that has been the basis for their export shall be relieved from duties and taxes; provided, however, that duties and taxes not paid on the raw materials as per the provisions of the Export Trade Duty Incentive Schemes Proclamation shall be paid.

3/ The period specified in sub-article (2) of this Article may be extended at the request of the interested party on justifiable grounds.

**77. Termination of the Procedure**

The temporary importation or exportation procedure may be terminated by declaring the goods for outright importation or exportation of the goods subject to

የቀጥታ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ወደ ውጭ የመላክ የዕቃ ዲክላራሲዮን በማቅረብ እንዲቋረጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትን በኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ስለማከናወን

**፸፰. ጠቅላላ**

፩/ በባለሥልጣኑ በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲጠቀም የተፈቀደለት ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማከናወን ይችላል፡-

ሀ) ማጓጓዣዎች ስለመድረሳቸው ወይም ስለመነሳታቸው እና በነዚሁ ላይ ስለተሳፈሩ መንገደኞች ወይም ስለተጫኑ ዕቃዎች ሪፖርቶችን ማቀነባበርና ማቅረብ፣

ለ) የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ማከናወን፣

ሐ) ክፍያዎችን መፈጸም፣ እና

መ) የዕቃ መልቀቅያ ትዕዛዝ መቀበል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት አጠቃቀም ደጋፊ ሰነዶች በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንዲቀርቡ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡

፫/ የወጪና ገቢ ዕቃዎችን በሚመለከት የአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የሚመለከታቸው የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና የፋይናንስ ተቋማት በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባለሥልጣኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፡፡

**፸፱. ተጠቃሚዎችን ስለመመዝገብ**

ማንኛውም በባለሥልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን እንዲፈቀድለት የሚፈልግ ሰው፡-

፩/በባለሥልጣኑ የተወሰነውን ደረጃ የጠበቀ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ፋሲሊቲ በማሟላት፣

፪/ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓቱን የአጠቃቀምና የደህንነት መመሪያዎች የሚያከብር ስለመሆኑ ማረጋጫ በመስጠት፣

፫/ ዲጂታል ፊርማውን ከተፈቀደለት ውጪ ሌላ ሰው እንደማይጠቀም ማረጋገጫ በመስጠት፣

compliance with the conditions and formalities applicable to the importation or the exportation of goods, as the case may be.

## CHAPTER TWELVE

## COMPLETION OF CUSTOMS PROCEDURE THROUGH ELECTRONIC INFORMATION EXCHANGE SYSTEM

**78. General**

1/ Any person who is authorized to use the electronic information exchange system developed by the Authority may, electronically:

a) process and submit reports on the arrival or departure of a means of transport and travellers taken on board or goods loaded;

b) complete customs formalities;

c) effect payments; and

d) receive order of release of goods.

2/ The use of the electronics information exchange system under sub-article (1) of this Article includes the presentation of supporting documents electronically.

3/ The Authority shall facilitate the use of its electronic information exchange system by the relevant government agencies and financial institutions to enable the provision of single window service with respect to the importation and exportation of goods.

**79. Registration of Users**

Any person interested to secure authorization to use the electronic exchange system of the Authority shall be registered with the Authority upon:

1/ installing an electronic information exchange facility that meet the standard set by the Authority;

2/ assuring compliance with the usage and security requirements of the electronic information exchange system;

3/ confirming that the digital signature may not be used by a person other the authorized person;

፬/ ከተፈቀደለት ውጪ ሌላ ሰው ዲጂታል ፊርማውን ተጠቅሞ ቢገኝ ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ የማስታወቅ ሃላፊነቱን እንደሚወጣ በማረጋገጥ፤ እና

፭/ በባለሥልጣኑ ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ስምምነት በመፈረም፤

በባለሥልጣኑ መመዝገብ አለበት፡፡

## ፹. መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ስለመላክና ስለመቀበል

፩/ የባለሥልጣኑን የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመጠቀም የሚላክ ማንኛውም መረጃ ከተፈቀደው የዲጂታል ፊርማ ጋር ተያይዞ መላክ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ተልኳል የሚባለው በላኪው በራሱ ወይም መልዕክቱን በሚመለከት ጉዳይ ላኪውን ወክሎ ለመሥራት ሥልጣን በተሰጠው ሰው የተላከ ሲሆን ነው፡፡

፫/ በባለሥልጣኑና የተፈቀደለት የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠቃሚው መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ስለመቀበላቸው መተማመኛ አሰጣጥን በተመለከተ የተወሰነ ፎርም ለመከተል ያደረጉት ስምምነት በሌለ ጊዜ የመልዕክቱ መድረስ መተማመኛ በማንኛውም ዘዴ ሊሰጥ ወይም መድረሱን በበቂ ደረጃ ሊያመላክት በሚችል ድርጊት ሊገለጽ ይችላል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑና የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ ተጠቃሚ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ መልዕክት አስገዳጅነት የሚኖረው መልዕክቱ ስለመድረሱ መተማመኛ ሲሰጥ ነው የሚል ስምምነት ካላቸው ይኸው መተማመኛ በስምምነቱ በተገለጸው ጊዜ ወስጥ ካልተሰጠ መረጃው እንዳልተላከ ይቆጠራል፡፡

## ፹፩. በኤሌክትሮኒክስ የሚላኩ መረጃዎችን ስለማረጋገጥ

በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የተላኩ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ ኦሪጅናል ዶኩሜንቶችን አስቀርቦ ማየት ይችላል፡፡

## ፹፪. የወረቀት ሰነድ ስለመጠቀም

፩/ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ ባለመሥራቱ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ መላክ ወይም መቀበል በማይቻልበት ጊዜ ተጠቃሚውና ባለሥልጣኑ መረጃዎችን በወረቀት መለዋወጥ ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የኤሌክትሮኒክስ ስርዓቱ በሚሰራበት ጊዜ ተጠቃሚው የተለመደውን የጉምሩክ ሥነሥርዓት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማከናወን አለበት፡፡

4/ confirmation that if the digital signature is used by a person other than the authorized person, to inform the Authority immediately; and

5/ signing the agreement prepared by the Authority.

## 80. Sending and Receipt of Electronics Messages

1/ Any information sent through the use of the Authority's electronic information exchange system shall attached with the authorized digital signature.

2/ Any electronic information is deemed to be sent if it was sent by the originator or by a person who had the authority to act on behalf of the originator in respect of that communication.

3/ Where the Authority and registered user have not agreed that an acknowledgement of receipt of electronics communication be given in a particular form, an acknowledgement may be given by any communication, or by a conduct sufficient to indicate that the electronic communication is received.

4/ Where the Authority and the registered user have agreed that an electronic communication shall be binding on the receipt of an acknowledgement, such electronic communication shall be deemed not to have been sent unless the acknowledgement has been so received within the time agreed upon.

## 81. Verification of Electronics Information

The Authority may require the submission of original documents to check the veracity of electronically transmitted information.

## 82. Use of Paper Documents

1/ Where the user and the Authority cannot send or receive information electronically due to failure of the electronic information exchange system, they may communicate with each other by paper documents.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the user shall perform the usual customs procedures electronically when the electronic system works.

**፹፫. የተጠቃሚነት መብትን ስለማገድና ምዝገባን ስለመሠረዝ**

፩/ ማንኛውም የባለሥልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠቃሚ ከባለሥልጣኑ ጋር ባደረገው ስምምነት የተመለከቱ ግዴታዎችን ያላከበረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን እስከሚያስተካክል ድረስ በሥርዓቱ የመጠቀም መብቱ ታግዶ ይቆያል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በሚከተሉት ምክንያቶች የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተጠቃሚን ምዝገባ ሊሠርዝ ይችላል:-

ሀ) ምዝገባው የተከናወነው ተጠቃሚው ባቀረበው የሀሰት ማስረጃ ላይ ተመስርቶ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ለ) ተጠቃሚው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለእግዱ ምክንያት የሆኑትን ጉድለቶች ያላስተካከለ እንደሆነ፤

ሐ) ተጠቃሚው የጉምሩክ ህጎች በመጣስ ወይም በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሶ የተቀጣ ከሆነ፤ ወይም

መ) በማናቸውም ምክንያት የተጠቃሚው የንግድ ድርጅት የተዘጋ ከሆነ፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት በኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት የመጠቀም መብትን ከማገዱ ወይም ምዝገባውን ከመሠረዙ በፊት እርምጃው የሚወስድበትን ምክንያት ለተጠቃሚው በጽሑፍ በማሳወቅ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

## ቀለል ያለ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

**፹፬. ሥነ ሥርዓቱ ስለሚፈቀድላቸው ሰዎች**

፩/ ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብና የዕቃ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት ተፈጻሚ እንዲሆን የሚፈቀደው ባለሥልጣኑ ያወጣውን መመዘኛ አሟልተው ለተመረጡና ለተመዘገቡ ሰዎች ነው፡፡

፪/ ሥነ ሥርዓቱ ተፈጻሚ እንዲሆንላቸው የሚፈቀድላቸውን ሰዎች ለመምረጥ ባለሥልጣኑ የሚያወጣው መመዘኛ ለላኪዎችና ለኢንዱስትሪ አምራቾች ልዩ ትኩረት የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

**፹፭. ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብ**

ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን አቀራረብ ሥነ ሥርዓት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል:-

**83. Suspension of Use Right and Cancelation of Registration**

1/ Where any user of the Authority's electronics information exchange system fails to comply with the terms of the agreement entered with the Authority, his use right shall be suspended until he rectifies the irregularities within the period specified by the Authority.

2/ The Authority may cancel the registration of a user of the electronics information exchange system where:

a) it is proved that the registration was based on false information submitted by the user;

b) the user fails to rectify the irregularities caused the suspension with the time specified pursuant to sub-article (1) of this Article;

c) the user has been convicted for an offence committed in violation of customs law or a breach of trust; or

d) the business of the user ceases operation for any reason.

3/ The Authority shall, before taking an action of suspension of use right or cancelation or registration under this Article, notify the user, in writing, the reasons for taking the action and give him the opportunity to present his opinion.

## CHAPTER THIRTEEN

## SIMPLIFIED CUSTOMS PROCEDURE

**84. Authorized Persons**

1/ The application of simplified customs procedure shall be allowed for selected and registered persons upon fulfilling criteria specified by the Authority.

2/ The Authority shall give special consideration to exporters and manufacturers in setting the criteria for the selection of authorized persons.

**85. Simplified Procedure for Goods Declaration**

Simplified procedure for goods declaration may include the following:

፩/ ዕቃዎችን ለመለየት የሚያስፈልጉ ውስን መረጃዎች እስከቀረቡ ድረስ የተሟላው የዕቃ ዲክላራሲዮን በቀጣይነት እንዲቀርብ በመፍቀድ ዕቃዎቹን መልቀቅን፣

፪/ ዕቃዎችን አዘውትሮ ከውጭ ለሚያስመጣ ወይም ወደ ውጭ ለሚልክ በሥርዓቱ እንዲጠቀም ለተፈቀደለት ሰው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለሁሉም ዕቃዎች የተጠቃለለ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርብ መፍቀድን፣

፫/ በሥርዓቱ እንዲጠቀም በተፈቀደለት ሰው መዝገብ ላይ በሠፈሩ መረጃዎች አማካይነት የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብና በቀጣይነትም በሚቀርብ ተጨማሪ የዕቃ ዲክላራሲዮን እንዲደገፍ መፍቀድን፡፡

**፹፮. ቀለል ያለ የዕቃ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት**

ቀለል ያለ የዕቃ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት የዕቃ አወጣጥ ሥርዓቱ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የሥራ ቦታ ወይም ባለሥልጣኑ በሚወስነው ሌላ ቦታ እንዲፈጸም የሚፈቅድ ሥርዓት ይሆናል፡፡

**፹፯. የቀረጥና ታክስ ዕዳዎችን በራስ ትመና ስለመወሰን**

በሥርዓቱ እንዲጠቀም የተፈቀደለት ሰው የቀረጥና ታክስ ዕዳውን የንግድ መዝገቦቹን ተጠቅሞ እራሱ እንዲተምንና አግባብነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ሌሎች የጉምሩክ ግዴታዎቹን ማክበሩን እራሱ እንዲያረጋግጥ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

**፹፰. ኦዲትን መሠረት ያደረገ የጉምሩክ ቁጥጥር**

ባለሥልጣኑ ቀለል ያለ የዕቃ ዲክላራሲዮን ትክክለኛና ተዓማኒነት ያለው መሆኑን እና ሌሎች የጉምሩክ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በሥርዓቱ እንዲጠቀም የተፈቀደለትን ሰው መዝገቦችን፣ ሪኮርዶችን፣ የንግድ አሠራር ሥርዓቶችን እና የንግድ መረጃዎችን በመመርመር ኦዲትን መሠረት ያደረገ የጉምሩክ ቁጥጥር ያካሂዳል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለ ጉምሩክ ቀረጥና ታክስ

### ምዕራፍ አንድ
### የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን

**፹፱. መርህ**

፩/ ቀረጥንና ሌሎች በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጠየቁ ክፍያዎችን ለማስላት እንዲሁም የውጭ ንግድን

1/ release of the goods on the provision of the minimum information necessary to identify the goods and permit the subsequent completion of the final goods declaration;

2/ allowing consolidated goods declaration for all imports or exports in a given period where goods are imported or exported frequently by the same person;

3/ allowing the lodgment of goods declaration by means of an entry in the records of the authorized person to be supported subsequently by a supplementary goods declaration.

**86. Simplified Procedure for Clearance of Goods**

Simplified procedure for clearance of goods shall consist of a procedure that allows the clearance of goods at the declarant's business premises or another place authorized by the Authority.

**87. Self-Assessment of Customs Duty and Tax Liabilities**

The Authority may allow use of the authorized person's commercial records to self-assess duty and tax liabilities and, where appropriate, to ensure compliance with other customs requirements.

**88. Audit Based Customs Control**

The Authority shall use audit based customs control to satisfy itself as to the accuracy and authenticity of simplified goods declarations and compliance with other customs requirements through the examination of the relevant books, records, business systems and commercial data held by the authorized persons.

## PART FOUR
## CUSTOMS DUTIES AND TAXES

### CHAPTER ONE
### DETERMINATION OF DUTIABLE VALUE

**89. Principles**

1/ The dutiable value for the purposes of applying the customs tariff and calculating other import charges,

በሚመሩ ህጎች የተዘረዘሩትን ታሪፍ ያልሆኑ እርምጃዎች በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል የሚተመነው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናል፡፡

፪/ ወደ አገር ለሚገባ ማናቸውም ዕቃ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሚሆነው እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈለ ጠቅላላ ወጪ ነው፡፡

፫/ ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው ዕቃው የተሸጠበትና ከኢትዮጵያ መውጫ እስከሆነው የጉምሩክ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝ የሚያስፈልገው ወጪ ድምር ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ ስለተዘረዘሩት የዋጋ መተመኛ ዘዴዎች አፈፃፀም እና በእነዚሁ ዘዴዎች መሠረት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መወሰን በማይቻልበት ጊዜ እንዲሁም ላገለገሉ ዕቃዎች ተፈጻሚ ስለሚሆኑት የዋጋ መተመኛ ዘዴዎች ባለሥልጣኑ መመሪያ ያወጣል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በግብይት ዋጋ መሠረት ቀረጥና ታክሱን መወሰን ባልተቻለ ጊዜ በዚህ አዋጅ መሰረት ቀረጥና ታክሱን ለመወሰን የሚያስችል መረጃ ያደራጃል፡፡

## ፺. የግብይት ዋጋ

፩/ ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ዕቃ የግብይት ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ለተሸጠው ዕቃ በትክክል የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ዋጋ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፯ የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች የታከለበት ይሆናል፡፡ ሆኖም:-

ሀ) በህግ ወይም ህግን መሠረት ባደረገ ልዩ ውሳኔ ከተጣሉ ገደቦች ዕቃዎቹ እንደገና ሊሸጡ የሚችሉበትን መልክዓ ምድራዊ አካባቢ ከሚወስኑ ገደቦች ወይም በዕቃዎቹ ዋጋ ላይ የጎላ ተፅኖ ከማያሳድሩ ገደቦች በስተቀር ገዥው የገዛቸውን ዕቃዎች ለሌላ የሚያስተላልፍበትን ሁኔታ ወይም አጠቃቀሙን አስመልክቶ ሌሎች ተጨማሪ ገደቦች ሊደረጉ አይችሉም፤

ለ) የዕቃው ሽያጭ ወይም ዋጋው ሊተመን የማይችሉ ሁኔታዎች ወይም ገደቦች የተጣለበት ሊሆን አይችልም፤

ሐ) በገዥው ከሚፈጸም የመልሶ ሽያጭ፣ ማስተላለፍ ወይም አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ከሚገኝ ገቢ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሻጩ የሚከፈል ገንዘብ ሊኖር አይችልም፤

መ) ገዥውና ሻጩ ግንኙነት ያላቸው ከሆነ የግብይት

as well as for applying non-tariff measures prescribed by laws governing foreign trade shall be determined in accordance with the provisions of this Part.

2/ The dutiable value for imported goods shall be the actual total cost of the goods up to the first entry point to the customs territory of Ethiopia.

3/ The dutiable value for export goods shall be the actual total costs of the goods up to the final exit point from the customs territory of Ethiopia.

4/ The Authority shall issue directive on the manner of application of the valuation methods stipulated in this Proclamation, and to prescribe other methods to be applicable in the case where the methods stipulated under this Proclamation could not be applied and be applicable in the case of second hand goods.

5/ The Authority shall organize a data base that enables him to determine the duties and taxes of imported goods based on this Proclamation, where the duties and taxes cannot be determined based on transaction value.

## 90. Transaction Value

1/ The transaction value of imported goods shall be the transaction value that is actually paid or payable for the goods when sold for export to Ethiopia, and adjusted where necessary, as set forth in Article 97 of this Proclamation; provided, however, that:

a) there are no restrictions as to the disposal or use of the goods by the buyer, other than restrictions imposed by law or by particular decisions issued based on such law, a limit in the geographical area in which the goods may be resold or limits that may not substantially affect the value of the goods;

b) the sale or price of the goods is not subject to some conditions or restrictions for which a value cannot be determined;

c) no part of the proceeds of any subsequent resale, disposal or use of the goods by the buyer may accrue directly or indirectly to the seller,

d) where the buyer and seller are related, the

ዋጋው የቀረጥና ታክስ መተመኛ ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡

፪/ ገዥና ሻጭ ግንኙነት አላቸው ሊባል የሚችለው፡-

ሀ) አንዱ የሌላው የንግድ ድርጅት ባለሥልጣን ወይም ዳይሬክተር ከሆነ፤

ለ) በሕጋዊ መንገድ ዕውቅና ያገኙ የንግድ ሸሪኮች ከሆኑ፤

ሐ) የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ካላቸው፤

መ) አንዱ የሌላውን የንግድ ድርጅት አክስዮኖች ከ፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በባለቤትነት ከያዘ፤

ሠ) አንዱ ሌላውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠር ከሆነ፤

ረ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሶስተኛ ወገን ቁጥጥር የሚደረግባቸው ከሆነ፤

ሰ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሶስተኛ ወገን ላይ ቁጥጥር የሚያደርጉ ከሆነ፤ ወይም

ሸ) እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ካላቸው፤

ነው፡፡

፫/ ሻጭና ገዥው ግንኙነት ሲኖራቸው በሽያጩ ዙሪያ ያሉት ሁኔታዎች ተመርምረው በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በዋጋው ላይ ተፅኖ እንዳላሳደረ ሲታመን የግብይት ዋጋው ተቀባይነት ያገኛል፡፡

፬/ የሻጭና ገዥው ግንኙነት በዋጋው ላይ ተፅኖ ማሳደሩን ለማመን የሚያስችል ምክንያት ሲኖር ባለሥልጣኑ ይህንኑ ለአስመጭው መግለጽ አለበት፡፡

፭/ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል በተፈጸመ ሽያጭ የዕቃዎቹ ዋጋ፡-

ሀ) በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት በሌላቸው ገዥና ሻጭ መካከል በተከናወነ ሽያጭ ወደ ኢትዮጵያ በተላኩ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይነት ካላቸው ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፫ በተወሰነው መሠረት ከአንድ ዓይነት ወይም ከተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር፤ ወይም

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፬ በተወሰነው መሠረት ከአንድ ዓይነት ወይም ከተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር፤

የሚቀራረብ መሆኑን አስመጪው ለማረጋገጥ ከቻለ የዕቃዎቹ የግብይት ዋጋ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

transaction value shall be considered as the basis for valuation of duty if it is accepted by the Authority.

2/ A buyer and a seller shall be deemed to be related if:

a) one of them is an officer or director of the other's business;

b) they are legally recognized partners in business;

c) they have employer-employee relationship;

d) one of them directly or indirectly owns, controls or holds 5 percent or more of the outstanding voting stocks or shares of the other's business;

e) one of them directly or indirectly controls the other;

f) both of them are directly or indirectly controlled by a third party;

g) both of them directly or indirectly control a third party; or

h) they are related by consanguinity or affinity up to the second degree.

3/ Where an examination of the circumstances surrounding a sale between a buyer and a seller who are related shows that the relationship did not influence the price, the transaction value shall be accepted.

4/ Where there are grounds for considering that the relationship of the seller and the buyer influenced the price, the Authority shall communicate same to the importer.

5/The transaction value of goods in case of a sale between related persons shall be acceptable where the importer can prove that such value closely approximates to:

a) the transaction value in sales, between buyers and sellers who are not related, of identical or similar goods for export to Ethiopia during the same period;

b) the transaction value of identical or similar goods as determined under Article 93 of this Proclamation; or

c) the transaction value of identical or similar goods as determined under Article 94 of this Proclamation.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተጠቀሱትን ማነፃፀሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ የንግድ ደረጃ ልዩነት፣ የብዛት ልዩነት፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፮ መሠረት በዋጋ ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች እና ሻጩ ከገዢው ጋር ባልተዛመደበት ሁኔታ ያወጣቸው ወጪዎች እና ሻጩ ከገዢው ጋር በተዛመደበት ሁኔታ ደግሞ እነዚህ ወጪዎች በሻጩ ያልተከፈሉ መሆናቸው ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተጠቀሱት ማነፃፀሪያዎች በአስመጪው አነሳሽነት በጥቅም ላይ የሚውሉ ይሆናል፡፡

## ፺፩. አንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን

፩/ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺ መሠረት ሊወሰን ካልቻለ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡና በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ በተላኩ አንድ ዓይነት ዕቃዎች የግብይት ዋጋ መሰረት ይወሰናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የግብይት ዋጋን መወሰን ካልተቻለ የንግድ ደረጃው ወይም የብዛቱ ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ በተለየ የንግድ ደረጃ ወይም ብዛት ወደ አገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ መጠቀም ይቻላል፡፡

፫/ የግብይት ዋጋው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፮ (፩) የተጠቀሱትን ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዣ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ የገቡትንና አንድ ዓይነት የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከሰቱ የማጓጓዣ፣ የመጫን፣ የማውረድ የአያያዝና የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

## ፺፪. የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን

፩/ ወደአገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺ እና አንቀጽ ፺፩ መሠረት ሊወሰን ካልቻለ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡና በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ በተላኩ ተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ መሠረት ይወሰናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የግብይት

6/ In applying the tests under sub-article (5) of this Article, due account shall be taken of demonstrated differences in commercial levels, quantity levels the appropriate amount determined pursuant to Article 96 of this Proclamation and costs incurred by the seller in sales in which he and the buyer are not related and where such costs are not incurred by the seller in sales in which he and the buyer are related.

7/ The tests set forth under sub-article (5) of this Article shall be used at the initiative of the importer for comparison purpose.

## 91. Valuation of Identical Goods

1/ Where the transaction value of imported goods cannot be determined on the basis of Article 90 of this Proclamation, it shall be determined by taking the transaction value of identical goods sold for export to Ethiopia at the same commercial level and in substantially the same quantity at or about the same time as the goods being valued.

2/ Where it is impossible to determine the transaction value in accordance with sub-article (1) of this Article, the transaction value of identical goods sold at a different commercial level or in different quantities by making adjustments to take account of differences attributable to the commercial level or to the quantity.

3/ Where the transaction value includes costs referred to in Article 96 (1) of this Proclamation, the adjustment shall take into account the differences in transport, loading, unloading, handling and insurance costs associated with the transport of the imported goods and that of the identical goods to the port of entry into the customs territory which may arise from differences in distance and means of transport.

## 92. Valuation of Similar Goods

1/Where the transaction value of imported goods cannot be determined on the basis of Article 90 and Article 91 of this Proclamation, it shall be determined by taking the transaction value of similar goods sold for export to Ethiopia at the same commercial level and in substantially the same quantity at or about the same time as the goods being valued.

2/ Where it is impossible to determine the transaction value in accordance with sub-article (1) of this

ዋጋን መወሰን ካልተቻለ የንግድ ደረጃው ወይም የብዛቱ ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ በተለየ የንግድ ደረጃ ወይም ብዛት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ተመሳሳይ ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ መጠቀም ይቻላል፡፡

፫/ የግብይት ዋጋው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፮(፩) የተጠቀሱትን ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዣ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ የገቡትንና ተመሳሳይ የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ ወጪ የተደረገውን የማጓጓዣ፣ የመጫን፣ የማውረድ፣ የአያያዝና የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

## ፺፫. ወደኋላ የማስላት ዘዴ

፩/ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፺ እስከ አንቀጽ ፺፪ በተደነገገው መሰረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ በተቀራራቢ ወቅት ወደ አገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች ግንኙነት በሌላቸው ገዢና ሻጭ መካከል በገቡበት ሁኔታ በከፍተኛ ብዛት በተሸጡበት ነጠላ ዋጋ ላይ በመመሥረትና የሚከተሉትን ከዋጋው ላይ በመቀነስ ይወሰናል:-

ሀ) ለዕቃዎቹ አብዛኛውን ጊዜ የሚከፈለውን ኮሚሽን ወይም የሚደመረውን የጠቅላላ ወጪና የትርፍ መጠን፤

ለ) ለዕቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የሚከፈሉትን የማጓጓዣ፣ የኢንሹራንስና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች፤ እና

ሐ) ዕቃዎቹ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ የሚከፈለውን ቀረጥ፣ ታክስና ሌሎች ክፍያዎች፡፡

፪/ ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃና ወደ አገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በተቀራራቢ ጊዜ በአገር ውስጥ ካልተሸጡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወሰነው የግብይት ዋጋ ከሶስት ወራት ባልበለጠ የጊዜ ልዩነት ውስጥ ወደ አገር ውስጥ በገቡና በተሸጡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች ነጠላ ዋጋ ላይ ይመሠረታል፡፡

፫/ ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ እና አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በገቡበት ሁኔታ ካልተሸጡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወሰነው የግብይት ዋጋ በዕቃዎቹ ላይ የተከናወነው ቀጣይ የምርት ሂደት ያስከተለው ተጨማሪ ዕሴት ተቀንሶ ይተመናል፡፡

Article, the transaction value of similar goods sold at a different commercial level or in different quantities by making adjustments to take account of differences attributable to the commercial level or to the quantity.

3/ Where the transaction value includes costs referred to in Article 96 (1) of this Proclamation, the adjustment shall take into account the differences in transport, loading, unloading, handling and insurance costs associated with the transport of the imported goods and that of the identical goods to the port of entry into the customs territory which may arise from differences in distance and means of transport.

## 93. Deductive Value Method

1/ Where the transaction value of imported goods cannot be determined as set forth from Article 90 to Article 92 of this Proclamation, it shall be determined by using the unit price of the imported goods, identical or similar goods imported at or about the same time as the goods being valued and which are sold in Ethiopia in their original state in the greatest aggregate quantity to persons who are not related to the seller; provided, however, that the price shall be reduced by:

a) the amount of commission usually payable or the profit and general expense equal to that usually reflected in sales within Ethiopia of such goods;

b) the usual charges for the transport, insurance and other related costs to be incurred within Ethiopia for the goods; and

c) import duties, taxes and other charges payable with respect to the goods.

2/ In case where the imported goods, identical or similar imported goods are not sold in Ethiopia at or about the same time, as the goods being valued, the customs value to be determined under sub-article (1) of this Article shall be based on the unit price of the identical or similar imported goods which are sold in Ethiopia in their original state within a period having a time difference not longer than three months.

3/ In case where the imported goods and identical or similar imported goods are not sold in their original state, the transaction value to be determined under sub-article (1) of this Article shall be calculated by deducting the additional value resulting from the subsequent processing of the goods.

## ፺፬. በወጪ ስሌት ላይ የተመሰረተ ዋጋ

፩/ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፺ እስከ አንቀጽ ፺፫ በተደነገገው መሰረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ፦

ሀ) የዕቃዎቹን የማምረቻ ወይም የማዘጋጃ ወጪዎች፤

ለ) ዕቃዎቹ ወደ ኢትዮጵያ በተላኩበት አገር ተቀራራቢ ደረጃ ወይም ዓይነት ያላቸው ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ አብዛኛውን ጊዜ የሚያስከትሉትን ጠቅላላ ወጪና የሚያስገኙትን የትርፍ መጠን፤ እና

ሐ) ዕቃዎቹን እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ለማድረስ የሚያስወጣውን የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፤ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪን፤

በሚያካትት ስሌት ላይ ተመሥርቶ ይወሰናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት የግብይት ዋጋን ለመወሰን በአምራቹ ፈቃድ የሚገኘውን መረጃ ለማረጋገጥ፣ የሚመለከተው የአምራቹ አገር መንግስታዊ አካል ጉዳዩን በቅድሚያ እንዲያውቀው በማድረግ የማይቃወመው መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

## ፺፭. ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ዋጋ መወሰን

፩/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፺ እስከ አንቀጽ ፺፬ በተደነገገው መሰረት ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎችን የግብይት ዋጋ ለመወሰን ካልተቻለ በአገር ውስጥ ያለውን ወቅታዊ መረጃ በመጠቀምና ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች አጠቃላይ መርህ ጋር የተጣጣመ ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ይወሰናል።

፪/ አስመጭው ሲጠይቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተተመነው ዋጋና የአተማመን ዘዴው በጽሁፍ ይገለጽለታል።

## ፺፮. በግብይት ዋጋ ላይ የሚጨመሩ ክፍያዎች

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺ መሰረት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ላይ የሚከተሉት መደመር አለባቸው፦

ሀ) በገዥው የሚሸፈኑ ወጪዎች ሆነው ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ ያልተካተቱ፦

(፩) ከግዥ ኮሚሽን በስተቀር ማናቸውም ዓይነት የኮሚሽንና የድለላ ክፍያ፤

(፪) ከዕቃዎቹ ተነጥለው ሊታዩ የማይችሉ የዕቃ መያዣዎች ወጪ፤

## 94. Computed Value Method

1/ Where the transaction value of imported goods cannot be determined as set forth from Article 90 to Article 93 of this Proclamation, it shall be based on a computed value, consisting of the sum of:

a) the cost of manufacturing or processing of the goods;
b) an amount representing the general expenses and profit equal to that usually reflected in the sale of goods of the same class or kind by producers in the country of export; and
c) the transport, loading, unloading, handling and insurance costs associated with the transport of the goods to the port of entry into the customs territory of Ethiopia.

2/ In verifying, with the consent of the manufacturer, data necessary for determining customs value pursuant to the provisions of this Article, the relevant government body of the manufacturer's country shall be informed in advance and shall be ascertained that it does not object such verification.

## 95. Fallback Method

1/ Where the transaction value of imported goods cannot be determined under the provisions from Article 90 to Article 94 of this Proclamation, it shall be determined based on the data available in Ethiopia and using equitable methods consistent with the general principles embodied in the provisions of this Proclamation.

2/ The importer shall, when it so requests, be informed, in writing, of the transaction value determined under the provisions of sub-article (1) of this Article and the method used thereto.

## 96. Costs to be Included in Transaction Value

1/ In determining the customs value of imported goods in accordance with Article 90 of this Proclamation, the following costs shall be added to the price actually paid or payable for the imported goods:

a) expenses incurred by the buyer, and not included in the price actually paid or payable for the goods, in respect of:

(1) commission and brokerage charges except buying commission;

(2) the cost of packages which are treated as integral part, for customs purposes, of the goods;

(፫) ዕቃዎቹን ለማሸግ የወጣ የጉልበትም ሆነ የማቴሪያል ወጪ፣

(፬) ዕቃዎቹን እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪ፤

(፭) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ)(፬) የተደነገገው ቢኖርም ዕቃዎቹ በአየር የተጓጓዙ በሚሆንበት ጊዜ ለአየር ትራንስፖርት የተከፈለው አንድ ሦስተኛ ወጪ፤

ለ) ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ አስቀድመው ያልተካተቱ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ለማምረት በአስመጪው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያለ ክፍያ ወይም በአነስተኛ ክፍያ የቀረቡና አስፈላጊው የወጪ ማስተካከያ የተደረገባቸው ግብዓቶች፣ ክፍሎችና ሌሎች ዕቃዎች፣ የእጅ መሣሪያዎች፣ ቅርጽ ማውጫዎችና ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች፣ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ የዋሉ አላቂ ዕቃዎች፣ ከኢትዮጵያ ውጪ ለተከናወኑ የኢንጂነሪንግ፣ የሥነ-ጥበብ፣ የዲዛይንና የፕላን ሥራዎች የተደረጉ ወጪዎች፤

ሐ) ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ ያልተካተቱና በገዢው በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲከፈሉ በሽያጭ ውሉ የተደነገጉ የአዕምሯዊ ንብረት ሮያሊቲና ፈቃድ ክፍያዎች፤

መ) ዕቃዎቹን መልሶ በመሸጥ፣ ለሌላ በማስተላለፍ ወይም በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ ለሻጩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚከፈሉ ክፍያዎች።

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በግብይት ዋጋ ላይ የሚደመሩ ማናቸውም ተጨማሪ ክፍያዎች በተጨባጭና ሊለኩ በሚችሉ መረጃዎች ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው።

፫/ የግብይት ዋጋ ለመወሰን በዕቃው የተከፈለ ወይም የሚከፈል ዋጋ ላይ የሚደመር ክፍያ በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ይሆናል። ክፍያውም በሌተር ኦፍ ክሬዲት ወይም በህግ በተፈቀደ ሌላ የክፍያ ሥርዓት አማካይነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊፈጸም ይችላል።

## ፺፯. በግብይት ዋጋ ውስጥ የማይካተቱ ክፍያዎች

፩/ ለዕቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ውስጥ ተለይተው እስከተቀመጡ ድረስ የሚከተሉት ክፍያዎች በግብይት ዋጋ ውስጥ አይካተቱም፡-

(3) the cost of packing, whether for labor or materials;

(4) the transport, loading, unloading, handling and insurance costs associated with the transport of the goods to the port of entry into the customs teritory;

(5) notwithstanding the provisions of sub-article (1) (a)(4) of this Article where goods are transported by air, one-third of cost paid for air transport;

b) the cost, apportioned as appropriate and where supplied directly or indirectly by the buyer free of charge or at reduced costs for use in the production and sale for export of the imported goods, to the extent that such cost has not been included in the price actually paid or payable, materials, components and similar items, tools, dyes, moulds, casts and similar items, materials consumed in the production of the imported goods and engineering development, art work, design work and plans and sketches undertaken outside Ethiopia and necessary for the production of the imported goods;

c) royalties for intellectual property rights and license fees related to the goods that the buyer is required to pay, either directly or indirectly, as a condition of sale of the goods, to the extent that such royalties and license fees are not included in the price actually paid or payable;

d) the value of any part of the proceeds of any subsequent resale, disposal or use of the goods that accrues directly or indirectly to the seller.

2/ Additions to the price actually paid or payable shall be made under this Article on the basis of objective and quantifiable data.

3/ No additions may be made to the price actually paid or payable in determining the customs value, except as provided in this Article. Such payments may be made directly or indirectly by a letter of credit or any other legally acceptable means of payment.

## 97. Charges not to be Included in Transaction Value

1/ Provided that they are shown separately from the price actually paid or payable, the following may not be included in the transaction value:

ማስከፈያ ዋጋ ተቀባይነት ያላገኘበት ምክንያት በጽሑፍ ለአስመጪው ወይም ለወኪሉ ይገለጽለታል፡፡

## ፻. የዋጋ አተማመን ዘዴዎች ተፈጻሚ የሚሆኑባቸው ሌሎች ሁኔታዎች

በዚህ አዋጅ ክፍል አራት የተመለከቱት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን ዘዴዎች በሚከተሉትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ:-

፩/ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ከጉምሩክ ቁጥጥር ከተለቀቁ በኋላ በድጋሚ ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምበት ሁኔታ ሲያጋጥም፤

፪/ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞባቸው ከተለቀቁ በኋላ ኦዲት የሚካሄድባቸውን ዕቃዎች በሚመለከት፤

፫/ ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን እና በጊዜያዊነት ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን ዋጋ አተማመን በሚመለከት፡፡

## ፻፩. የገንዘብ ምንዛሬ

ወደ አገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ ከአገር የሚወጡ ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚሰላው ስለዕቃዎቹ የቀረበው የዕቃ ዲክላራሲዮን በተመዘገበበት ቀን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገለጸውን የገንዘብ ምንዛሬ ልክ በመጠቀም ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የታሪፍ አመዳደብ

## ፻፪. መርህ

፩/ ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት ይሆናል፡፡

፪/ ጭነቱ በተለያየ የታሪፍ አመዳደብ ላይ የሚመደቡ ዕቃዎችን የያዘ በመሆኑ ምክንያት ዕቃዎችን የመመደብ ወይም የዕቃ ዲክላራሲዮን የማዘጋጀት ሥራው አድካሚ ሆኖ ሲገኝና የጉምሩክ የታሪፍ ምጣኔ ልክ የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ በዲክላራሲዮን አቅራቢው ጥያቄ መሠረት ሚኒስቴሩ አጠቃላይ ጭነቱን ከፍተኛ ታሪፍ በሚመደብበት የታሪፍ መደብ ላይ በመመደብ የታሪፍ ምጣኔ ልክ እንዲወሰን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፫/ የዓለም የጉምሩክ ድርጅት ስለሸቀጦች አመዳደብ የሚያወጣው ሰነድ ስለዕቃዎች የታሪፍ አመዳደብ ወሳኝ ማስረጃ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

determined under the provisions of Article 90 of this Proclamation; and the reason for such decision shall be provided in writing to the declarant.

## 100. Other Conditions in which Valuation Methods be Applicable

The valuation methods of dutiable stipulated by the provisions of Part Four of this Proclamation shall also be applicable to:

1/ goods that have been released from customs control without paying duties and taxes undergo another customs procedure to pay duties and taxes;

2/ goods which may undergo post customs clearance audit;

3/ the valuation of non-commercial imported goods and temporarily imported goods.

## 101. Exchange Rate

The customs value of imported or exported goods shall be calculated on the basis of the official exchange rate declared by the National Bank of Ethiopia on the day the goods declaration has been registered.

## CHAPTER TWO

## TARRIF CLASSIFICATION

## 102. Principles

1/ Duties on goods imported into the customs territory shall be paid at the rates specified by the Customs Tariff Regulation.

2/ Where classification of goods and drawing up of goods declaration becomes difficult due to a consignment containing goods falling under different tariff classifications, the Ministry may, at the request of the person presenting the declaration, allow that the customs duty for the entire consignment be charged on the basis of the tariff classification of the goods which are subject to the highest rate of customs duty.

3/ Documents prepared by the World Customs Organization in relation to classification of goods shall be taken as conclusive evidence.

**፻፫. የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብን በተመለከተ አስገዳጅ መረጃዎች ስለመስጠት**

፩/ ከአስመጪው ወይም ከወኪሉ በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብን በተመለከተ ባለሥልጣኑ አስገዳጅ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀውን መረጃ የሚጠቀም ሰው ያቀረበው የዕቃ ዝርዝር መግለጫ አስገዳጅ መረጃውን ለማግኘት አስቀድሞ ከሰጠው መረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ መቻል አለበት፡፡

፫/ የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብን በተመለከተ የተሰጠ አስገዳጅ መረጃ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተቀባይነቱን ያጣል፡-

ሀ) አስገዳጅ መረጃው በአመልካቹ በቀረበ የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ መረጃ ላይ የተመሰረተ ከሆነ፤

ለ) በደንቦች ወይም መመሪያዎች መለወጥ ምክንያት አስገዳጅ መረጃው በሥራ ላይ ካሉት ደንቦች ወይም መመሪያዎች ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤

ሐ) አስገዳጅ መረጃው የተሰጠው ተገቢው ሥልጣን በሌለው ሰው ከሆነ፤

መ) አስገዳጅ መረጃው ከተሻረ ወይም ከተሰረዘና መሻሩ ወይም መሰረዙ ለመረጃው ባለቤት የተገለፀ ከሆነ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ለ) የተገለፀው ሁኔታ ሲከሰት ደንቡ ወይም መመሪያው በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ መረጃው የማያገለግል ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የዕቃዎች የሥሪት አገር

**፻፬. የዕቃዎች ሥሪት አገር አወሳሰን**

፩/ አንድን ምርት በማምረት ሂደት ሁለትና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው አገሮች ተሳታፊ በሚሆኑበት ሁኔታ የምርቱ የሥሪት አገር ነው የሚባለው የመጨረሻው መሠረታዊ የምርት ሥራ የተካሄደበት ወይም የኢኮኖሚያዊ እሴት መሠረታዊ ለውጥ የተደረገበት አገር ይሆናል፤ ሆኖም የምርት ሂደቱ በዚሁ አገር ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ፋብሪካ ውስጥ የተከናወነና ሂደቱም በወሳኝ መልኩ በምርቱ ላይ ለውጥ ያስከተለ ወይም አዲስ ምርት ያስገኘ መሆን አለበት፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም ሲባል የዕቃውን የሥሪት አገር ለመወሰን የሚከተሉት መስፈርቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡-

**103. Binding Information Regarding Tariff Classification**

1/ At the request of an importer or his agent, the Authority shall issue binding information in respect of the classification of goods.

2/ The person using information referred to under sub-article (1) of this Article shall be able to prove that the goods declared correspond in every respect to those described in the information previously provided by him to get the binding information.

3/ Binding information regarding tariff classification shall become invalid:

a) where it is based on inaccurate or incomplete information supplied by the applicant;

b) where regulations or directives have been changed, and the information no longer conforms to the applicable regulations or directives;

c) where the binding information was not provided by the competent person;

d) where the information has been annulled or revoked, and the holder of the information has been notified of such annulment or revocation.

4/ When the situations referred to in sub-article (3) (b) of this Article occur, the information shall become invalid as of the date such regulations or directives become effective.

## CHAPTER THREE

## ORIGIN OF GOODS

**104. Determination of Country of Origin**

1/ Where two or more countries are involved in the production of a product, the origin of the product shall be the country in which the last substantial manufacturing or transformation process of economic value took place; provided, however, that such process was carried out in a plant equipped for this purpose and led to a substantial transformation of the product or the creation of a new product altogether.

2/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, the criteria for determining country of origin, shall be the following:

ሀ) የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ፣

ለ) የተጨማሪ እሴት መቶኛ መመዘኛ፣ እና

ሐ) የማምረቻ ወይም የዝግጅት ሥራ ሂደት መመዘኛ፡፡

፫/ በምርት ግብዓቶች ላይ የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎችና የምርት ሂደቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተደነገገው የተሟላ ሥራ ሂደት ሆነው ይቆጠራሉ፡፡

፬/ ማናቸውም የሥራ ወይም የምርት ክንውን የዚህን አዋጅ የስሪት አገር አወሳሰን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ዓላማ በማድረግ የተከናወነ መሆኑ ከተረጋገጠ ከሥሪት አገር ድንጋጌዎች አንፃር ትክክለኛ ክንውን ሆኖ አይቆጠርም፡፡

**፻፭. የዕቃዎች የሥሪት አገርን ለመወሰን ግምት ውስጥ የማይገቡ ሁኔታዎች**

የሚከተሉት የአሰራር ሂደቶች የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ የሚያስከትሉ ሆነም አልሆነ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የሥሪት አገር ለመወሰን ከግምት ውስጥ አይገቡም፡-

፩/ በምርት ማጓጓዝ ወይም ክምችት ወቅት ምርቱን ባለበት ሁኔታ ለማቆየት የሚከናወኑ ተግባራት፣

፪/ ዕቃዎችን የማጓጓዝ ሂደት ለማቀላጠፍ ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፣

፫/ ዕቃዎችን ለማሸግ ወይም ለሽያጭ ለማዘጋጀት ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፣

፬/ ዕቃዎችን በአየር የማናፈስ፣ የማስጣት፣ የማድረቅ፣ የማቀዝቀዝ፣ የተበላሹ ክፍሎችን የመቀየር፣ ማለስለሻ የመቀባት ወይም ዝገት የማስወገድ፣ ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች በዕቃው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቀለም የመቀባት፣ የማጠብ፣ የማጽዳት፣ የማበጠር፣ የመፈተግ፣ የመለየት፣ የመመዘን፣ የመሞከር፣ የመለካት፣ የማሸግ፣ እሽጎችን የመፍታት፣ መልሶ የማሸግ፣ የመከፋፈል፣ ምልክት የማድረግ፣ በውሃ ወይም በሌላ ፈሣሽ ነገር አያያዝ ማድረግ፣ በጨው የመንከር፣ የመላጥ፣ የመከካት፣ የመውቃት እና የእንስሳት ዕርድ የመሳሰሉ ቀላል ሂደቶች ክንውን፣

፭/ የተሟላ የምርት ውጤት ለማስገኘት የሚከናወን ቀላል የመገጣጠም ሥራ፣

፮/ ከላይ የተዘረዘሩትን የሥራ ሂደቶች በማጣመር የሚከናወን ማንኛውም የሥራ ሂደት፡፡

a) change of tariff classification;

b) the ad valorem percentage criterion; and

c) the criterion of manufacturing or processing operation.

3/ Working or processing methods because of which the products obtained tariff classification other than that covering the various non-originating materials used shall be regarded as complete process referred to in sub-article (1) of this Article.

4/ Any processing or working the sole object of which is to circumvent the rules of origin, provided for under this Proclamation, may not be deemed authentic.

**105. Conditions not Considered when Determining Country of Origin**

The following operations may not be taken into consideration when determining the origin of imported goods, whether or not accompanied by a change in the tariff classification:

1/ operations carried out to insure that the goods are preserved in good condition during transport or storage;

2/ operations carried out to facilitate transportation of goods;

3/ operations carried out to package or prepare goods for sale;

4/ simple operations on goods such as ventilation, spreading out, drying, cooling, removal of damaged parts, greasing or rust removal, adding a coat of paint to protect against natural elements, washing, cleaning, sifting or screening, sorting or classifying, scaling, testing or calibration, packaging or breaking up of assembled packages or repackaging, dividing the bulks, affixing marks, labels or other distinguishing signs on the packages of goods, dilution by water or any other aqueous solution, ionization, salting, peeling, crushing, removal of seeds from fruits and slaughtering of animals;

5/ simple assembly of parts to constitute a complete product;

6/ any combination of the above.

**፻፮. የሥሪት አገርን ለመወሰን የሚረዱ ሰነዶችን ስለማቅረብ**

፩/ ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ህጐችን ለማስፈፀም ሲባል የዕቃዎችን የሥሪት አገር የሚያረጋግጥ ሰነድ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በቀረበለት ሰነድ ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው የዕቃውን የሥሪት አገር በተመለከተ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል።

**፻፯. የዕቃዎች የሥሪት አገር መግለጫ**

፩/ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች እና የእነዚህ ዕቃዎች ማሸጊያ የተሠሩበትን አገር የሚያስረዳ መግለጫ በቀላሉ ሊፋቅ፣ ሊነሳና ሊለወጥ በማይችል አኳኋን በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈባቸው ሊሆን ይገባል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘረውን የማያሟላ ዕቃ ወደመጣበት አገር እንዲመለስ ይደረጋል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው የሥሪት አገር መግለጫ የሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

**፻፰. የታሪፍ ቅናሽ ከሚሰጣቸው አገሮች የሚመጡ ዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰን ድንጋጌዎች**

በዓለም አቀፍ፣ በአካባቢያዊ ወይም በሁለትዮሽ የንግድ ስምምነት መሰረት የታሪፍ ቅናሽ ወይም የቀረጥ ነፃ መብት የሚሰጣቸው አገሮች የስሪት አገር አወሳሰን ድንጋጌዎች በስምምነቶቹ መሰረት የሚወሰኑ ይሆናል።

## ምዕራፍ አራት

## ስለቀረጥ፣ ታክስ እና የአገልግሎት ክፍያዎች

**፻፱. ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ**

በህግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ ወይም በሚኒስቴሩ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር በማናቸውም የገቢ ወይም የወጪ ዕቃ ላይ ቀረጥና ታክስ ይከፈላል።

**፻፲. ቀረጥና ታክስ የመክፈል ሃላፊነት**

፩/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዕቃው ላይ የሚከፈለውን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሳይከፈል በቀረ ቀረጥና ታክስ ላይ የሚወሰነውን ቅጣትና ወለድ የመክፈል ሃላፊነት አለበት።

**106. Production of Documents**

1/ The Authority may, for the purpose of applying customs law, order the production of documents that show the country of origin of goods.

2/ Where the Authority has doubts as to the authenticity of documents produced pursuant to sub-article (1) of this Article, it may require any additional proof in respect of the country of origin of goods.

**107 Origin Marking**

1/ The name of the country of origin of imported goods shall be affixed, in English, on each good and the package thereof in a manner that such marking cannot be easily deleted, removed or altered.

2/ Goods that do not meet the requirements under sub-article (1) of this Article shall be returned to the exporting country.

3/ The provisions of sub-article (1) and (2) of this Article may not apply to personal effects not destined for commercial use.

4/ The Authority shall by a directive specify the manner under which the rules of country of origin markings are to be applied.

**108. Rules of Preferential Origin of Goods**

The rules on preferential origin of goods shall be determined in accordance with rules of country of origin contained in international, regional or bilateral agreements providing for reduction or relief from duties or taxes.

## CHAPTER FOUR

## PAYMENT OF CUSTOMS DUTIES, TAXES AND SERVICE CHARGES

**109. Obligation to Pay Customs Duties and Taxes**

Unless otherwise provided by law or decided by the Ministry, duties and taxes shall be payable for any imported or exported goods.

**110. Liability for Payment of Customs Duties and Taxes**

1/ The declarant shall be liable for payment of the duties and taxes imposed on the goods as well as penalties and interests incurred due to default hereof.

**፻፲፬. ክፍያ ስለሚፈጸምበት መንገድ**

በዕቃዎች ላይ የተወሰነው ቀረጥና ታክስ በጥሬ ገንዘብ ወይም በህግ በሚታወቅ ማንኛውም የክፍያ መንገድ ይፈጸማል፡፡

**፻፲፭. የአገልግሎት ክፍያዎች**

ባለሥልጣኑ ከጉምሩክ ፎርማሊቲ ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለው የአገልግሎት ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## የቀረጥና ታክስ ክፍያን ለመሸፈን ስለሚሰጥ ዋስትና

**፻፲፮. ዋስትና ስለማቅረብ**

ባለሥልጣኑ የቀረጥና ታክስ ክፍያ መከፈሉን ወይም ከቀረጥና ታክስ ነጻ መብት ጋር የተያያዙ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ዋስትና እንዲቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፻፲፯. ዋስትና የሚጠየቅባቸው ሁኔታዎች**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፲፮ አጠቃላይ አነጋገር እና ዋስትናን የሚመለከቱ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ባለሥልጣኑ ዋስትና እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡-

፩/ የጉምሩክን ፎርማሊቲ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ለማሟላት ተጨማሪ ጊዜ ሲያስፈልግ የጉምሩክ ፎርማሊቲው ሳይከናወን ዕቃዎቹን ለመልቀቅ፤

፪/ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ተመልሰው መውጣታቸውን ወይም ካልወጡ ቀረጥና ታክሱ መከፈሉን ለማረጋገጥ፤

፫/ ተላላፊ ዕቃዎች በተወሰነው መስመር ተጓጉዘው በተፈቀደ መውጫ በር ከአገር መውጣታቸውን ወይም መራገፊያቸው ወደሆነው የጉምሩክ ጣቢያ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ፤

፬/ የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው ወደ ውጭ ለመላክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ ከገቡ ዕቃዎች የተገኙ ማካካሻ ምርቶች ወደ ውጭ መላካቸውን ወይም ካልተላኩ ቀረጥና ታክሱ መከፈሉን ለማረጋገጥ፤

፭/ በታሪፍ አመዳደብ እና በዋጋ አተማመን ረገድ በአስመጪውና በባለሥልጣኑ መካከል የተፈጠረው ያለመግባባት የመጨረሻ ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው እንዲለቀቁ ለማድረግ፤

**114. Mode of Payment**

Payment of duties and taxes shall be in cash or any other legal means of payment.

**115. Service Charges**

The service charges to be collected by the Authority for services it renders in connection with customs formalities shall be determined by regulation to be issued by the Council of Ministers.

## CHAPTER FIVE

## SECURITIES TO GUARANTEE PAYMENT OF CUSTOMS DUTIES AND TAXES

**116. Furnishing of Security**

The Authority may require the provision of security to guarantee the payment of duties and taxes or compliance with the requirements related to a duty and tax exemption privilege.

**117. Conditions for Requiring Security**

Without prejudice to the generality of Article 116 of this Proclamation and other provisions requiring the furnishing of security, the Authority may require the furnishing of security for the following reasons:

1/ to release goods without the completion of customs formalities when additional time is required to produce complete documents necessary for the completion of customs procedures;

2/ to ensure the re-exportation of goods imported on temporary basis without payment of duties and taxes or , in case of default, to ensure the payment of the duties and taxes;

3/ to ensure that transit goods exit through the approved customs route or arrive at the predetermined customs point of destination;

4/ to ensure the exportation of compensating products obtained from goods imported without payment of duties and taxes for inward processing or , in case of default, to ensure the payment of the duties and taxes;

5/ to release goods without payment of taxes and duties until the dispute between the importer and the Authority on classification or valuation of the goods imported are resolved;

፮/ የቀረጥና የታክሱ ክፍያ ከሚፈፀምበት ጊዜ እንዲዘገይ የተፈቀደ ሲሆን ክፍያው እስከሚፈፀም ድረስ፡፡

**፩፻፲፰. የዋስትና ዓይነት**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠየቅ ዋስትና የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ፣ የባንክ የዋስትና ሰነድ፣ የኢንሹራንስ ቦንድ ወይም በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ መሥሪያ ቤቶችን የሚመለከት ሲሆን በጽሑፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት ሊሆን ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ለአንድ የቀረጥና ታክስ እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያዎች አንድ ዋስትና ብቻ ይጠይቃል፤ ሆኖም በባለዕዳው ጥያቄ መሠረት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ኦፕሬሽኖች ምክንያት የሚከሰት ክፍያን የሚሸፍን ዋስትና እንዲሰጥ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ዋስትናውን እዳው ከሚመለከተው ሰው ውጪ በሆነ በሌላ ሰው እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፬/ዋስትና እንዲያቀርብ የሚጠየቅ ሰው በዚህ አዋጅ ከተደነገጉት የዋስትና ዓይነቶች አንዱን መምረጥ ይችላል፤ ሆኖም ባለሥልጣኑ የተመረጠው ዋስትና ከሚፈጸመው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ጋር የማይጣጣም ከሆነ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

**፩፻፲፱. ዋስትናን የተመለከቱ መብትና ግዴታዎች**

፩/ ባለሥልጣኑ የተቀበለው የዋስትና ዓይነት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲያገለግል ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ዋስትና የተገባለት ግዴታ ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸመ ዋስትናው ቀሪ ይሆናል፡፡ ባለሥልጣኑ ዋስትና የተገባለት ግዴታ የተፈፀመ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፫/ ባለዕዳው ግዴታውን ሳይወጣ በቀረ ጊዜ ዋስትና ሰጪው ክፍያውን ወዲያውኑ መፈጸም አለበት፡፡

፬/ ዋስትና ሰጪው እና ባለዕዳው በአንድነትና በነጠላ እዳውን ከነወለዱና ወጪው የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

፭/ ዋስትና ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ክፍያውን ሳይፈጽም ከቀረ ባለሥልጣኑ በገቢ ግብር አዋጅ በተመለከተው ሥነ ሥርዓት መሠረት የባለዕዳውን ወይም የዋስትና ሰጪውን ንብረት በመያዝ ክፍያው እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል፡፡

6/ to ensure payment of taxes and duties where deferred payment is allowed.

**118. Form of Security**

1/ Where a security is required to be furnished pursuant to this Proclamation, such security shall be by cash deposit, bank guarantee, insurance bond or in case of public bodies a written undertaking.

2/ The Authority shall require only one security to be furnished in respect of one payment of duties and taxes and service charges; provided, however, that at the request of the debtor, the Authority may permit comprehensive security to be furnished to cover payments arising from two or more customs operations.

3/ The Authority may authorize the furnishing of the security by a person other than the debtor.

4/ Any person required to furnish a security shall be allowed to choose any form of security prescribed under this Proclamation; provided, however, that the Authority may reject such security where it is incompatible with the applicable customs procedure.

**119. Rights and Obligations Related to Security**

1/The Authority may require that the type of security chosen be maintained for a specified period.

2/Any security shall be extinguished upon the full settlement of the debt. The Authority shall, when requested, issue evidence showing the extinction of the secured debt.

3/ Where the debtor fails to discharge his obligations the guarantor shall immediately effect the payment.

4/ The guarantor and the debtor shall be jointly an severally liable for the secured amount of deb including interests and costs incurred.

5/ Where the guarantor fails to effect payment i accordance with sub-article (3) of this Article, th Authority may apply the procedure prescribed und the Income Tax Proclamation to seize the property the debtor or the guarantor for the payment of th debt.

**፻፳. <u>የዋስትና መጠን</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ ዋስትና መጠን ዋስትናው በሚቀርብበት ጊዜ የሚፈለገው ቀረጥ፣ ታክስና የአገልግሎት ክፍያ መጠን በእርግጠኝነት የሚታወቅ ከሆነ ከዚሁ ማነስ የለበትም፡፡

፪/ የሚፈለገውን የቀረጥ፣ የታክስና የአገልግሎት ክፍያ መጠን በእርግጠኝነት ማወቅ ባልተቻለ ጊዜ ዋስትናው ባለሥልጣኑ በገመተው ከፍተኛ የቀረጥ፣ የታክስና የአገልግሎት ክፍያ መጠን ይሆናል፡፡

፫/ የቀረበው ዋስትና በማናቸውም ምክንያት የእዳ ክፍያውን የማይሸፍን ሆኖ ከተገኘ ባለዕዳው ተጨማሪ ዋስትና ማቅረብ ወይም የመጀመሪያውን ዋስትና በሌላ መተካት አለበት፡፡

## <u>ምዕራፍ ስድስት</u>

## <u>ስለ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት፣ በልዩነት ስለሚፈለግ ቀረጥና ታክስ እና ስለቀረጥና ታክስ ተመላሽ</u>

**፻፳፩. <u>የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቀው የተለቀቁ ዕቃዎችን ዲክላራሲዮን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ዕቃውን ለማስመጣት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በተሳተፈ ሰው እጅ የሚገኙ መዛግብትን፣ ሪኮርዶችን፣ የንግድ አሰራሮችን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጉምሩክ ነክ የንግድ መረጃዎችን በመመርመር የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የሚያደርገው የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት በባለሥልጣኑ ጽሕፈት ቤት ወይም ዕቃዎቹን በማስመጣትና በመላክ የንግድ ሥራ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በተሳተፈው ሰው ቅጥር ግቢ ወይም ለምርመራ የተፈለጉት መረጃዎችና ሰነዶችን በያዘ ሌላ ማናቸውም ሰው ቅጥር ግቢ ሊከናወን ይችላል፡፡

፫/ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲቱ ግኝት የጉምሩክ ፎርማሊቲ የሚመራባቸው ድንጋጌዎች መጣሳቸው ከተረጋገጠ የፍትሐብሔር ወይም የወንጀል ወይም የሁለቱንም ኃላፊነት የሚያስከትል ውጤት ይኖረዋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሊካሄድ የሚችለው የዕቃ ዴክላራሲዮን ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

፭/ ኦዲተሩ በዚህ አዋጅ ለጉምሩክ ሹም የተሰጠው ሥልጣን ይኖሩታል፡፡

**120. <u>Amount of Security</u>**

1/ The amount of security to be furnished pursuant to the provisions of this Proclamation may not be less than the amount of duties, taxes and service charges where such amount can be established with certainty at the time when the security is furnished.

2/ In cases, where the amount of duties, taxes and service charges cannot be established with certainty, the amount of security shall be equal to the maximum amount estimated by the Authority.

3/ Where it is found that the security furnished does not cover the debt due to any cause, the debtor shall furnish additional security or replace the original security with a new one.

## <u>CHAPTER SIX</u>

## <u>POST- CLEARANCE AUDIT, DIFFERED PAYMENT AND REFUND OF DUTIES AND TAXES</u>

**121. <u>Post-Clearance Audit</u>**

1/ The Authority may, after the release of goods, undertake post-clearance audit to verify the accuracy of goods declarations through the examination of the books, records, business systems and other relevant customs commercial data held by persons directly or indirectly involved in the import or export of the goods.

2/ The Authority's post-clearance audit may be carried out at the premises of the Authority or the premises of the person who is directly or indirectly involved in the business operations of the import or export of the goods or at the premises of any other person in possession of the data and documents subject to the inspection.

3/ The findings of post-clearance audit, if it reveals that the provisions governing customs formalities have been breached, entails civil or criminal liability or both.

4/ Post clearance audit under this Article may be carried out within five years from the date a goods declaration has been accepted.

5/ Post Clearance Auditors shall have the same power as customs officers as prescribed under this Proclamation.

## ፻፳፪. በልዩነት ስለሚፈለግ ቀረጥና ታክስ

፩/ ቀረጥና ታክስ በማናቸውም ምክንያት ያልተከፈለ ወይም ሊከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረሰበት እንደሆነ ባለሥልጣኑ ዲክላራሲዮን አቅራቢውን ያልተከፈለውን ወይም በልዩነት ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊያስከፍል ይችላል፡፡

፪/ ለቀረጥና ታክሱ ያለመከፈል ወይም በማነስ መከፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው የሆነ እንደሆነ ሳይከፈል በቀረው ቀረጥና ታክስ ላይ ፲ በመቶ ቅጣትና የባንክ ወለድ ተጨምሮ ይከፈላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚከፈለው ወለድ መጠን ቀረጥና ታክሱ እንዲከፈል በተጠየቀበት ወቅት በሥራ ላይ ባለው ከፍተኛው የንግድ ባንክ የማበደሪያ ወለድ ተመን መሠረት የሚሰላ ይሆናል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ ኦዲት የሚያደርግ መሆኑ በጽሑፍ ካሳወቀ በኋላ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ መኖሩን ከገለጸና ለመክፈል ፍቃደኛ ከሆነ ከቀረጥና ታክሱ እና ወለዱ ክፍያ በስተቀር ቅጣት እንዳይጣልበት ባለሥልጣኑ ሊወስን ይችላል፡፡

፭/ ያልተከፈለውን ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው በቂ ምክንያት ሲያቀርብ ዕዳው ከነወለዱ በተወሰነ ጊዜ ተከፍሎ እንዲያልቅ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተጠየቀውን ቀረጥና ታክስ ከነመቀጫና ወለዱ ያልከፈለ ባለዕዳ በሥራ ላይ ባለው የገቢ ግብር አዋጅ የተመለከተው ንብረትን ይዞ የማስፈፀም ስርዓት ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡

## ፻፳፫. በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ

፩/ በዕቃዎች አሰያየም፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሳብ አሰራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ለከፋዩ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሊታይ የሚችለው ዕቃው የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖበት ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ውጭ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ከቀረበ ነው፡፡

## 122. Deferred Payment

1/ Where the post-clearance audit reveals that the duty and tax is not paid or paid in a lesser amount, the Authority may collect the outstanding amount from the declarant within five years from the date of default of such payment.

2/ Where the payment was deferred due to the fault of the declarant, a penalty of 10% and bank interest thereof shall be paid in addition to the duties and taxes.

3/ The amount of interest to be paid under sub-article (2) of this Article shall be calculated at the highest current lending interest rate applied by commercial bank.

4/ Notwithstanding the provisions of sub article (2) of this Article, the Authority may exonerate the declarant from penalty except the payment of the duties and taxes with interest where the declarant discloses and consents to pay the deferred amount following the written notification of the audit schedule of the Authority.

5/ Where the person responsible for the payment of the deferred amount of the duties and taxes so requests, on sufficient grounds, the Authority may allow the payment to be effected on instalment basis together with interest thereon.

6/ The seizure procedure prescribed under the Income Tax Proclamation in force shall be applicable to the property of a debtor who has failed to settle the payment of duties and taxes together with the penalty and interest claimed under this Article.

## 123. Refund of Overcharged Duties and Taxes

1/ Refund of duties and taxes shall be granted if the duties and taxes are overcharged as a result of incorrect commodity classification, tariff setting, valuation or other calculation mistakes.

2/ Claims for refund of duties and taxes under sub-article (1) of this Article shall be considered if it is submitted within one year after the goods are imported or exported upon completion of customs formalities.

**፩፻፳፬. <u>የዕቃ ዲክላራሲዮን ውድቅ በመደረጉ ምክንያት ተመላሽ ስለሚሆን የቀረጥና ታክስ ክፍያ</u>**

፩/ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ የሚደረገው፡-

ሀ) የዕቃ ዲክላራሲዮን በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰረዘና በዚሁ ዲክላራሲዮን መሠረት የተከፈለ ቀረጥና ታክስ የነበረ ሲሆን፤ እና

ለ) የዕቃ ዲክላራሲዮንን ለማሠረዝ ማመልከቻ ሊቀርብ በሚችልበት የጊዜ ገደብ ውስጥ በሚመለከተው ሰው ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ አቤቱታ የቀረበ እንደሆነ፤

ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም በዕቃው ላይ የቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ሌላ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሊፈፀምበት የሚገባ ሆኖ ከተገኘ ቀረጥና ታክሱ ተመላሽ ሳይደረግ አግባብነት ያለው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈፀምበት ይደረጋል፡፡

**፩፻፳፭. <u>የጥራት ደረጃቸው በቀነሰ፣ በተበላሹ፣ በተጎዱ፣ ጉድለት በታየባቸው ዕቃዎች ምክንያት ተመላሽ ስለሚሆን ቀረጥና ታክስ</u>**

፩/ ዕቃ በጉዞ ላይ ወይም በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እያለ የጥራት ደረጃው ከቀነሰ፣ ከተበላሸ፣ ከተጎዳ፣ ከወደመ ወይም ከጎደለ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ በዚሁ መጠን ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፪/ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ አስመጪው ከሻጩ ጋር ባደረገው ውል ላይ በተገለጸው መጠን ወደ አገር ውስጥ ሳይገባ የቀረ ከሆነ በጐደለው ዕቃ ላይ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የቀረጥና ታክስ ክፍያ ተመላሽ ጥያቄ ቀረጥና ታክሱ በተከፈለ በ፲፪ ወራት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

**፩፻፳፮. <u>የቀረጥና ታክስ እዳን ቀሪ ስለማድረግ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፳፭(፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃ በጉዞ ላይ ወይም በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እያለ ከተበላሸ ወይም ከወደመ የሚፈለግበት ቀረጥና ታክስ ቀሪ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቀረጥና ታክሱ ቀሪ የተደረገው ዕቃው በአስመጪው ጥፋት በመበላሸቱ ምክንያት ከሆነ ዕቃው በአስመጪው ኪሳራ በባለሥልጣኑ እንዲወገድ ወይም እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

**124. <u>Refund of Duties and Taxes for Invalidated Goods Declaration</u>**

1/ Duties and taxes shall be refunded where:

a) a goods declaration is cancelled and duties and taxes have been paid; and

b) an application is submitted by the person concerned within the prescribed period for submission of the application for invalidation of the goods declaration.

2/ Notwithstanding the provision of sub - article (1) of this Article, where there is another appropriate customs procedure requiring the payment of taxes and duties on the same goods, such procedure shall be accomplished instead of refunding taxes and duties.

**125. <u>Refund of Duties and Taxes for Deteriorated, Spoiled, Damaged, Destroyed or Short-landed Goods</u>**

1/ The duties and taxes which have been paid in respect of goods which have been deteriorated, spoiled, damaged or destroyed during voyage or while under customs control or short-landed shall be refunded proportionately.

2/ The duties and taxes which have been paid in respect of goods which have been short-landed, when compared with the quantity specified in the contract entered by the importer with the seller, shall be refunded.

3/ No refund of duties and taxes may be granted under sub article (1) or (2) of this Article unless the claim is presented within twelve months from the date of payment of the duties and taxes.

**126. <u>Remission of Duties and Taxes</u>**

1/ Without prejudice to Article 125(1) of this Proclamation the duties and taxes payable in respect of goods which has been damaged or destroyed during voyage or while under customs control shall be remitted.

2/ If the tax is remitted in accordance with sub-article (1) of this Article due to the reason that the goods are damaged by the fault of the importer, the Authority shall dispose or re-export such goods at the expense of the importer.

፻፳፯. በስህተት ተመላሽ ወይም ቀሪ የተደረገን ቀረጥና ታክስ ስለማስከፈል

በስህተት ተመላሽ ወይም ቀሪ የተደረገ ቀረጥና ታክስ ለባለሥልጣኑ ተመልሶ ይከፈላል፡፡

፻፳፰. ስለ ማቻቻል

ባለሥልጣኑ የተመላሽ ጥያቄ ያቀረበው ሰው ያለበትን የቀረጥና ታክስ እዳ ከባለሥልጣኑ በሚጠይቀው ተመላሽ ክፍያ እንዲቻቻል ሊወስን ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት

፻፳፱. የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት አሰጣጥ

የገቢና ወጪ ዕቃዎችን በሚመለከት የቀረጥ ነፃ መብት በህግ፣ ኢትዮጵያ ተቀዋይ ወገን በሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፻፴. ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር ስለገባ ዕቃ

፩/ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር የገባን ዕቃ ቀረጥና ታክሱ ሳይከፈልበት ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ማንኛውም ሰው ማስተላለፍ ወይም የቀረጥ ነፃው መብት ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ መገልገል ወይም በሌሎች ሰዎች ይዞታና አገልግሎት እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር የገባ ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ተመልሶ ከአገር ሊወጣ ወይም ተመሳሳይ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ላለው ሰው ሊተላለፍ ወይም ቀረጥና ታክሱ ተከፍሎበት ለሌላ ሰው ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ቀረጥና ታክሱም የሚሰላው ዕቃው በተላለፈበት ጊዜ በሚያወጣው ዋጋና ፀንቶ ባለው የታሪፍ ልክ መሠረት ይሆናል፡፡

፫/ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የጠፋ ወይም ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ አስመጪው ለባለሥልጣኑ ይህንኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ ለኢንቨስትመንት ሥራ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት የተሰጠው ሰው ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሆነው የገቡ ዕቃዎችን ለሌላ ሰው ሲያስተላልፍ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሲመልስ በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የክሊራንስ ሰነድ የማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

127. Recovery of Duties and Taxes Refunded or Remitted by Error

Any amount of duties and taxes refunded or remitted by error shall be recovered by the Authority.

128. Set off

The Authority may set off any refund claim against any amount of duties and taxes owed by the claimant.

## CHAPTER SEVEN

## DUTY AND TAX EXEMPTIONS

129. Granting Duty and Tax Exemptions

Duty and Tax exemptions with respect to import and export goods may be granted by law, international agreement to which Ethiopia is a party or by directive to be issued by the Ministry.

130. Duty and Tax Exempted Imports

1/ It is prohibited to transfer duty and tax exempted imported goods to a person who is not enjoying similar privileges or use them for a purpose other than which the duty free privilege is granted or place them under the possession and service of others, before payment of the duties and taxes applicable to them.

2/ Any duty and tax exempted imported goods may be re-exported or transferred to a person who enjoys similar privilege without payment of duties and taxes or transferred to any person upon payment of the duties and taxes. The duties and taxes shall be calculated at the value of the goods and tariff rates prevailing during the time of disposal.

3/ Where duty and tax exempted imported goods are lost or damaged the importer shall forthwith report to the Authority.

4/ Any person who enjoys duty and tax exemptions privilege for investment purpose shall be required to produce a clearance document from the Authority prior to the transfer of duty and tax exempted imported goods to other persons or the return of his investment permit.

፭/ የሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ ወይም መዝጋቢ አካልም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ሁኔታ መሟላቱን የማረጋገጥ እና ክትትል የሚያስፈልጋቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን እንዳወቀ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፮/ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር የገባን ዕቃ በዋስትና ማስያዝ የሚቻለው ከባለሥልጣኑ ጋር በቀረጥና ታክሱ አከፋፈል ረገድ ስምምነት ላይ ሲደረስ ይሆናል፡፡

፯/ የባለቤትነት ስም ዝውውር የሚመዘግብ ማናቸውም አካል ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበትን ዕቃ ሲመዘግብ ይህንኑ በባለቤትነት የምስክር ወረቀት ላይ መግለጽ ያለበት ሲሆን ዕቃው ለሦስተኛ ወገን በሚተላለፍበት ጊዜ ቀረጥና ታክሱ መከፈሉን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ከጉምሩክ ሥራ ጋር የተያያዙ ግዴታዎች

### ፩፻፴፩. የአጓጓዥ ግዴታዎች

፩/ የዚህ አዋጅ ክፍል ሦስት ምዕራፍ ስድስት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም አጓጓዥ፡-

ሀ) ወደ አገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ማጓጓዣን በባለሥልጣኑ ከተፈቀደው የጉዞ መስመር ውጭ ማንቀሳቀስ፣ ማቆም፣ መንገደኛ ማሳፈር፣ ዕቃ ማውረድ ወይም ማራገፍ የለበትም፤

ለ) ባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጠውና ጉምሩክ ሹም በስፍራው ሳይገኝ መንገደኛ ማሳፈር ወይም ማውረድ ወይም ዕቃ መጫን ወይም ማራገፍ አይችልም፤

ሐ) ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንኛውም ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲገባ መፍቀድ የለበትም፤

መ) በባህሪያቸው ምክንያት ተቀጣጣይ ወይም አደገኛ የሆኑ ዕቃዎች ከማጓጓዣው ከመራገፋቸው በፊት ማስታወቅ አለበት፤

ሠ) ማጓጓዣው ጉምሩክ ወደብ ከመድረሱ በፊት ስለጫነው ዕቃ፣ ስለ መንገደኞች እና በማጓጓዣው ውስጥ ስለሚቀረው ዕቃ ዝርዝር መግለጫ ለጉምሩክ ሹም ማቅረብ አለበት፤

ረ) ማጓጓዣው በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል ውስጥ የጉምሩክ ሥነሥርዓት የተፈጸመበትን ዕቃ ጭኖ እንዲንቀሳቀስ ከተፈቀደለት በኋላ በማናቸውም ምክንያት የሚያዘገይ ከሆነ ይህንኑ ለጉምሩክ ሹም ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ The concerned licensing or registry office shall have the obligation to ascertain the fulfilment of the conditions stated under sub-article (4) of this Article and to inform the Authority in case of conditions that require follow up.

6/ Duty and tax exempted goods can be given as security if an agreement is reached with the Authority as to the payment of duties and taxes.

7/ Government bodies that are registering title to property shall indicate in the title deed that the goods are duty and tax exempt and ensure that the duty and taxes are paid before registering transfer of title.

## PART FIVE

## OBLIGATIONS RELATED TO CUSTOMS OPERATIONS

### 131. Obligations of Carrier

1/ Without prejudice to the provisions of Chapter Six of Part Three of this Proclamation, any carrier shall:

a) use authorized customs routes for arrival and departure of the means of transport, for loading and unloading of goods, and for embarkation and disembarkation of travellers;

b) refrain from embarking or disembarking travellers or loading or unloading cargos in the absence of customs officer unless authorized by the Authority;

c) not allow any unauthorized person to approach to the means of transport;

d) provide information regarding inflammable or dangerous goods, before they are discharged;

e) provide detailed information regarding the goods loaded, passengers, and goods to be retained on board to the customs officer before the arrival of the carrier;

f) if the carrier is to be delayed after permit is granted to depart shall report the same immediately to the customs officer.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም አጓጓዡ ማጓጓዣውን ከጉምሩክ ወደብ ውጪ ሊያሳርፍ ወይም ሊያቆም ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ አጓጓዡ ሁኔታውን በአቅራቢያው ላለው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ወይም በአካባቢው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ከሌለ ለአካባቢው አስተዳደር ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፩፻፴፪. የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ ግዴታዎች

የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

፩/ ለጉምሩክ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎችን፣ መሣሪያዎችን፣ ቴክኖሎጂዎችንና ሠራተኞችን የማሟላት፤

፪/ ወደ መጋዘኑ የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችን ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መመዝገብና በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ፤

፫/ በመጋዘኑ የሚቀመጡትን ዕቃዎች እንደዓይነታቸውና እንደባህሪያቸው በመለየት ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለቁጥጥር በሚያመች ሁኔታ የማስቀመጥ፤

፬/ የጉምሩክ ሹም ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠትና ለቁጥጥርና ለምርመራ ሥራው የመተባበር፤

፭/ በባለሥልጣኑ ያልተፈቀደ ዕቃ ወደ መጋዘን እንዳይገባ ወይም ከመጋዘን እንዳይወጣ የመቆጣጠር፤

፮/ የተሰጠውን የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ በወቅቱ የማሳደስ፤

፯/ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ወደ መጋዘን እንዳይገቡ የመቆጣጠር፤

፰/ የጤና ምርመራ ሊደረግበት የሚገባ ዕቃ ከማጓጓዣው እንደተራገፈ አስፈላጊው የጤና ምርመራ እስከሚፈጸም ድረስ ከሌሎች ዕቃዎች ተለይቶ በኳራንቲን ክልል የማቆየት፤

፱/ በአያያዝ ጉድለት የጠፋ ወይም የተበላሸ ዕቃዎችን በሚመለከት የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ የመክፈል፤

፲/ ወደ መጋዘኑ መግባት ያለባቸው ዕቃዎች ያልገቡ እንደሆነ ያለመግባታቸውን ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ፤

፲፩/ መጋዘኑ ጊዜያዊ የጉምሩክ ማከማቻ ሲሆን፡-

ሀ) የጉምሩክ ፎርማሊቲ የተከናወነበት ዕቃ ወዲያውኑ እንዲወጣ የማድረግ፤

ለ) በዚህ አዋጅ የተፈቀደው የጊዜ ገደብ ያለፈባቸውን በመጋዘኑ የተከማቹ ዕቃዎችን ለባለሥልጣኑ ማሳወቅና ዕቃዎቹን ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የማስተላለፍ፤



2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) (a) of this Article, the carrier may, in case of force majeure, land or stop the means of transport at any place other than a customs port; provided, however, that he shall immediately report the incident to the nearest branch of the Authority or, in the absence of branch of the Authority, to the local administration office.

## 132. Obligations of Customs Warehouse Permit Holder

Any customs warehouse permit holder shall:

1/ maintain offices, equipments, technological devices and staff necessary for customs operation;

2/ keep registration book in accordance with directive issued by the Authority for the goods deposited in and removed from the warehouse, and report to the Authority from time to time;

3/ segregate goods on the basis of their type and nature for the purpose of their safe storage and convenience for control;

4/ provide proper reply to queries made by customs officer and cooperate for inspection and investigation;

5/ ensure that no goods are deposited in or removed from the warehouse without the permission of the Authority;

6/ secure renewal of his customs warehouse license within the specified time;

7/ prohibit unauthorized persons from entering the customs warehouse;

8/ store goods requiring quarantine examinations, as soon as they are discharged from the means of transport, in a separate zone until completion of the quarantine examination;

9/ pay duties and taxes with respect to goods lost or damaged due to improper handling;

10/ where delivery of goods intended to be deposited in the warehouse has not been effected, report immediately to the Authority the non-receipt of the goods into the warehouse;

11/ in case of temporary customs storage:

a) release goods from the storage upon the completion of customs formalities;

b) report to the Authority the list of those goods deposited for more than the time specified under this Proclamation and transfer them to government customs warehouse;

፲፪/ መጋዘኑ በንድድ የጉምሩክ መጋዘን ከሆነ ዕቃዎቹ ለተፈቀደላቸው ዓላማ ሳይውሉ ሲቀሩ ቀረጥና ታክሱን ለመክፈል የሚያስችል ዋስትና የማቅረብ፡፡

## ፻፴፫. መረጃ የመስጠት ግዴታ

፩/ የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት ወይም በአነስተኛ ምጣኔ ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ወይም የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃ መኖሩን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ወይም የህግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪ አካል የሚሰጠው መረጃና ማንነቱ በሚስጥር ይጠበቃል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለጸው መሠረት ለባለሥልጣኑ ወይም ለህግ አስከባሪው አካል በተሰጠ መረጃ መሠረት የተገኙትን ዕቃዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ለማድረግ ከተቻለ መረጃና ድጋፍ ለሰጡ ሰዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ወሮታ ይከፈላል፡፡

## ፻፴፬. መረጃዎችን ይዞ ስለማቆየት

፩/ ለጉምሩክ ፎርማሊቲ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ወይም መረጃዎችን የያዘና ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው መረጃዎቹን ለአምስት ዓመት ይዞ ማቆየት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሰነዶችና መረጃዎች የሚቆዩበት ጊዜ የሚታሰበው፡-

ሀ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸው ከተለቀቁበት ቀን፤

ለ) የወጪ ዕቃዎች ዲክላራሲዮኑ ተቀባይነት ካገኘበት ቀን፤

ሐ) ከቀረጥ ነፃ ሆነው በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከተከናወነበት ቀን፤

ጀምሮ ይሆናል፡፡

## ፻፴፭. የመተባበር ግዴታ

፩/ ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ በሥራ ላይ ያሠማራቸው ሠራተኞች ሃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እንዲችሉ ትብብር ማድረግ አለበት፡፡



12/ in case of bonded customs warehouse, furnish security to cover the duties and taxes in a situation where the goods are not used for the authorized purpose.

## 133. Obligation to Provide Information

1/ Any person who has information about untaxed or less taxed goods in contravention of customs law or about prohibited, restricted or contraband goods shall immediately inform the nearest branch of the Authority or law enforcement body.

2/ The information supplied and the identity of the informant may not be disclosed.

3/ Where the information supplied to the Authority or other law enforcement body pursuant to sub-article (1) of this Article leads to seizure of the goods, all persons that have provided information and support shall be rewarded in accordance with directive issued by the Ministry.

## 134. Retaining Information

1/ Any person who is responsible to pay duties and taxes and thus possesses any documents or information necessary for customs formalities shall retain them for a period of five years.

2/ The period referred to in sub-article (1) of this Article shall count down from the day on which:

a) goods imported for home use are released for free circulation upon the completion of customs formalities;

b) a goods declaration is accepted for export goods;

c) customs formalities are completed in case of goods imported temporarily on duty free basis.

## 135. Duty to Cooperate

1/ Any person shall have the duty to cooperate with employees assigned by the Authority in discharging their official duties efficiently.

፪/ የፌደራልና የክልል የመንግሥት አካላት ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር በሚከናወን ስራ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ሃላፊነት አለባቸው፡፡

፫/ ኮንትሮባንድንና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የሚደረግ ጥረት ባለሥልጣኑ ከአቅሙ በላይ ሲሆን ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት የፀጥታ አስከባሪ አካላት ጋር በመሆን በጣምራ ሥራውን ሊያከናውን ይችላል፡፡

፬/ የጉምሩክ ሹም ተግባሩን ለማከናወን ዕርዳታ ሲጠይቅ ማናቸውም ህግ አስከባሪ አካል ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱት አካላት ተገቢና ተመጣጣኝ ሃይል ተጠቅመው ህገወጥ ሥራን ማስቆም ይችላሉ፡፡

## ክፍል ስድስት
## ስለጉምሩክ ቁጥጥርና ህግን ስለማስከበር

### ምዕራፍ አንድ
### የጉምሩክ ቁጥጥር

**፻፴፮. የጉምሩክ ቁጥጥር ዓላማ**

የጉምሩክ ቁጥጥር ዓላማ፡-

፩/ ቀረጥና ታክስ በአግባቡ መሰብሰቡን የማረጋገጥ፤ እና

፪/ የጉምሩክ ህጎችን በመተላለፍ የሚፈፀሙ ጥፋቶችን የመከላከል፣ የመመርመርና በጥፋተኞች ላይ አግባብ ያለው እርምጃ የመውሰድ ወይም የማስወሰድ፤

ይሆናል፡፡

**፻፴፯. የጉምሩክ ቁጥጥር አፈፃፀም**

ማንኛውም የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ቁጥጥር እርምጃዎች ሲወስድ የጉምሩክ ህጎችን ለማስከበር በሚያስፈልጉ እርምጃዎች ዓይነትና መጠን መወሰን አለበት፡፡

**፻፴፰. በገቢ፣ በወጪና ተላላፊ ዕቃዎች ላይ ስለሚደረግ የጉምሩክ ቁጥጥር**

፩/ የሚከተሉት ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ይሆናሉ፡-

ሀ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ጉምሩክ ወደብ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸው እስከሚለቀቁ፤

ለ) ወደ ቦንድድ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች

2/ Federal and regional state organs shall cooperate with the Authority in the fight against contraband.

3/ Where the Authority, in the fight against contraband, encounters circumstances which are beyond its control, it may discharge its duties in collaboration with the federal and regional state law enforcement organs.

4/ Any law enforcement body shall, upon request, assist a customs officer in discharging his duty properly.

5/ The bodies referred to in this Article may use appropriate and proportional force to stop an illegal activity.

## PART SIX
## CUSTOMS CONTROL AND LAW ENFORCEMENT

### CHAPTER ONE
### CUSTOMS CONTROL

**136. Purpose of Customs Control**

The purpose of customs control shall be:

1/ to ensure that duties and taxes are properly collected; and

2/ to prevent, investigate and take,or cause the taking of, appropriate action against breaches of customs law.

**137. Application of Customs Control**

In taking customs control measures, any customs officer shall confine himself to the forms and extent of measures sufficient for ensuring the observance of customs law.

**138. Customs Control on Import, Export and Transit Goods**

1/ The following goods shall be placed under customs control:

a) goods imported for home consumption, from the time of their arrival at customs port until the completion of customs formalities and they are released;

b) goods deposited in bonded customs warehouse, from the time they are deposited until they are

ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ለተፈቀደላቸው ዓላማ እስከሚለቀቁ፤

ሐ) ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች ወደጉምሩክ ወደብ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖባቸው እስከሚላኩ፤

መ) ተላላፊ ዕቃዎች እንዲንቀሳቀሱ ከተፈቀደበት ጊዜ ጀምሮ ወደተፈቀደው መድረሻ ቦታ እስከሚደርሱ ድረስ፤

ሠ) ባለቤት የሌላቸው፣ የተተው፣ የተወረሱ ወይም በኮንትሮባንድ የተያዙ ዕቃዎች እስከሚወገዱ ድረስ፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለፀው መሠረት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች ወደተከማቹበት ሥፍራ መግባት፣ ዕቃዎችን መክፈት ወይም ማናቸውንም ተግባር በዕቃዎቹ ላይ መፈፀም አይችልም፡፡

**፻፴፱. <u>የጉምሩክ የጠረፍ ቁጥጥር</u>**

፩/ የጉምሩክ ጠረፍ መስመርና የጉምሩክ ማቋረጫ በህግ ወይም በዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ድንበር ለማቋረጥ ወይም ዕቃን ለማጓጓዝ መብት ለተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ያገለግላል፡፡

፪/ በጉምሩክ የጠረፍ መስመር ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በጉምሩክ ማቋረጫዎች በኩል ለኑሯቸው አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችንና በዓለም አቀፍ ስምምነት ድንጋጌዎች መሠረት የተፈቀዱ ሌሎች ዕቃዎችን የማጓጓዝ መብት ይኖራቸዋል፡፡

፫/ በጉምሩክ የጠረፍ መስመር አካባቢ የሚኖሩ ሐኪሞች፣ የእንስሳት ሐኪሞች፣ ሌሎች የሕክምና ሠራተኞች እና የሕዝብን ሕይወትና ንብረት በማዳን ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ለሥራቸው የሚያስፈልጓቸውን መድሃኒቶችና መሣሪያዎች አግባብ ያለው የመንግሥት አካል በሚሰጣቸው ፈቃድ መሠረት በጉምሩክ ማቋረጫዎች በኩል ማጓጓዝ ይችላሉ፡፡

**፻፵. <u>የጉምሩክ ወደቦችና የመተላለፊያ መስመሮች</u>**

፩/ ገቢ፣ ወጪና ተላላፊ ዕቃዎች በተወሰነ የጉምሩክ ወደብ ወይም ማቋረጫ በኩል መግባት ወይም መውጣት እና በተፈቀዱ የመተላለፊያ መንገዶች ብቻ መጓጓዝ አለባቸው፡፡

፪/ የጉምሩክ ወደቦች፣ ማቋረጫዎችና የመተላለፊያ መንገዶች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የህዝብ ማስታወቂያ ይወሰናሉ፡፡

released for their authorized purpose;

c) export goods, from the time they entered customs port until the completion of customs formalities and be exported;

d) goods in transit, from the time their movement is allowed until they reach their destination;

e) goods found without owner, abandoned, forfeited or contraband goods until their disposal.

2/ No person may, without prior authorization of the Authority, enter a place in which goods, put under customs control in accordance with sub-article (1) of this Article, are deposited, or open or do any acts on such goods.

**139. <u>Customs Border Control</u>**

1/ Customs frontier strip and customs crossing shall be used for border crossing or transport of goods only by persons entitled to such activities on the basis of laws or international agreements.

2/ Residents within customs frontier strip shall be entitled to transport goods necessary for their living and work on their property as well as other things stipulated by international agreements.

3/ Doctors, veterinarians, other medical staff and rescue workers residing within customs frontier strip may carry instruments and medications needed for their activities through frontier crossings when approved by the pertinent government body.

**140. <u>Customs Ports and Transit Routes</u>**

1/ Import, export and transit goods shall enter or exit through prescribed customs ports or customs crossings and be transported through prescribed routes.

2/ Customs ports, customs crossings and transit routes shall be determined by public notice to be issued by the Authority.

**፻፵፩. <u>በጉምሩክ የቁጥጥር ሂደት የሚወሰዱ እርምጃዎች</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ፎርማሊቲ መከናወኑን ለማረጋገጥ በሥራ ላይ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት አግባብነት ያላቸውን ማናቸውንም ዓይነት እርምጃዎች መውሰድ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ባለስልጣኑ ዕቃዎች ከጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ጀምሮ የጉምሩክ ፎርማሊቲ እስከሚከናወን ድረስ በአይነት፣ በቅርፅ፣ በይዘትና በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ያልተለወጡ ሆነው መቆየታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ በጉምሩክ የቁጥጥር ሥርዓት መሠረት የሚወሰዱት እርምጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

ሀ) ዕቃዎችን በጉምሩክ ወደብ፣ በጉምሩክ ጣቢያ፣ በጉምሩክ መጋዘን፣ በመተላለፊያ መንገድ ወይም ባለሥልጣኑ በሚወስነው ማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ የመመርመር፣ የመከታተልና ጥበቃ የማድረግ፤

ለ) በመረጃና በስጋት ሥራ አመራር ላይ ተመስርቶ ምርመራ የተከናወነበትን ወጪ ወይም ገቢ ዕቃ በድጋሚ እንዲመረመር የማድረግ፤

ሐ) ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ ከአገር ወጥቷል ብሎ ማረጋገጫ የመስጠት፤

መ) የጉምሩክ ማህተሞችን ማድረግ፣ የጉምሩክ ሰነዶችን የመስጠትና የማረጋገጥ፤

ሠ) የዕቃዎች ዓይነትና ሁኔታ አለመለወጡን ለማረጋገጥ ናሙናዎችን፣ መግለጫዎችን፣ ፎቶዎችንና ሌሎች መረጃዎችን የመውሰድ፤

ረ) የመንገደኞችን ሻንጣዎችና ሌሎች ዕቃዎች የመመርመር፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ሐ) መሠረት ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ ከአገር ወጥቷል ተብሎ በባለሥልጣኑ ማረጋገጫ የሚሰጠው ከኢትዮጵያ መውጫ በሆነው የመጨረሻ ጣቢያ ከሚገኘው የጉምሩክ ሹም ዕቃው ከአገር መውጣቱን የሚገልጽ ማረጋገጫ ወደ ባለሥልጣኑ አውቶሜሽን ሲስተም ሲገባ ወይም በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በጽሁፍ ሲደርስ ብቻ ነው፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>ህግ ስለማስከበር</u>

**፻፵፪. <u>የመፈተሽ ሥልጣን</u>**

፩/ የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ጥፋት የተፈጸመባቸው ዕቃዎች ለመኖራቸው በቂ መረጃ ወይም ጥርጣሬ

**141. <u>Measures Taken Under Customs Control</u>**

1/ The Authority may, in accordance with conditions laid down by the provisions in force, take any measure it deems necessary to ensure the completion of customs formalities.

2/ Unless otherwise provided by this Proclamation, the Authority shall ensure that goods remain the same in kind, form, quality and in any other respect from their introduction into the customs territory until the completion of customs formalities.

3/ Measures to be taken under customs control shall include:

a) examining, surveillance and safeguarding of goods at customs port, customs station, customs warehouse, transit route or any other place determined by the Authority;

b) re-examination of import or export goods based on information and risk management;

c) certification of exit of export goods;

d) affixing of customs seals, issuance and verifying of customs documents;

e) taking samples, prospectus, photos and other data for the purpose of ascertaining non-alteration in the kind and state of goods;

f) examining luggage and other goods carried b travelers.

4/ Exit certificate of export goods shall be issue pursuant to sub-article (3) (c) of this Article only whe the information from the customs officer at the end c the customs checkpoint reach the Authority through i automated information network or delivered in writin through other communication media.

## <u>CHAPTER TWO</u>

## <u>LAW ENFORCEMENT</u>

**142. <u>Power to Search</u>**

1/ Where a customs officer has sufficient information reasonable suspicion to believe the existence of goo in respect of which a customs offence has be

ሲኖረው ዕቃዎቹን የጫነውን ማጓጓዣ በማስቆም ወይም ዕቃዎቹ ወደተከማቹበት ማናቸውም ሥፍራ በመግባት የመፈተሽና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፵፫ (፩)(ሀ) መሠረት ዕቃዎቹንና ማጓጓዣውን የመያዝ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፪/ የጉምሩክ ሹም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የፍተሻ ሥራ ሲያከናውን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታሸገ ካልሆነ በስተቀር የዕቃዎችን እሽግ የማንሳትና በቁልፍ የተዘጉ ዕቃዎችን የመክፈት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፫/ የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ጥፋት የተፈጸመበትን ዕቃ ደብቋል ብሎ ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው ማንኛውንም ሰው ማስቆምና መፈተሽ ይችላል፡፡

፬/ አካላዊ ፍተሻ ተመሳሳይ ጾታ ባለው ሰው ይከናወናል፡፡

፭/ የአካላዊ ፍተሻው አፈፃፀም በትህትና እና የሚፈተሸውን ሰው ስብዕና በማይነካ፣ ጤናውን ወይም ንብረቱን በማይጎዳ መልኩ እና ተደብቋል ተብሎ የተጠረጠረውን ህገወጥ ዕቃ ለማግኘት በሚያስችል ደረጃ መፈፀም አለበት፡፡

፮/ የጉምሩክ ሹሙ ውስጣዊ የአካል ፍተሻ ለማድረግ በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን ይኸው ፍተሻ ብቃት ባለው የህክምና ባለሙያ አማካኝነት እና በሚፈተሸው ሰው ላይ ጉዳት በማያስከትል መልኩ ይከናወናል፡፡

፯/ የጉምሩክ ሹሙ በማንኛውም ሰው ላይ ውስጣዊ አካላዊ ፍተሻ ለማድረግ በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ ሊያገኝ ይገባል፡፡ ሆኖም በፍርድ ቤት የተፈቀደን ፍተሻ እንዳይፈፀምበት የተቃወመ ሰው ያለመፈተሽ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ደብቋል ተብሎ የተጠረጠረውን ዕቃ ደብቆ እንደያዘ ይቆጠራል፡

፰/ የጉምሩክ ሹም በዚህ አንቀጽ መሠረት ፍተሻ ሲያደርግ ዩኒፎርም ማድረግና በቅድሚያ ማንነቱን የሚያስረዳ መታወቂያ ለሚመለከተው ሰው ማሳየት አለበት፡፡

፱/ የጉምሩክ ሹም በዚህ አንቀጽ መሠረት ፍተሻ ለማድረግ የሚመለከተውን ሰው ጠይቆ ፈቃድ ካላገኘ የፖሊስ ሀይል ሊጠቀም ይችላል፡፡

፲/ በቂ ምክንያት ሲኖረው የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ሥነሥርዓት አጠናቀው የተለቀቁ ዕቃዎችን በድጋሚ ለመፈተሽ ይችላል፡፡

committed, he shall have the power to undertake search by stopping any means of transport carrying such goods or by entering into any place where the goods are stored and to seize the goods and the means of transport pursuant to Article 143(1) (a) of this Proclamation.

2/ A customs officer shall, while conducting search pursuant to sub-article (1) of this Article, have the power to remove packages or to open locked goods, except where such goods are sealed by the order of a court.

3/ A customs officer may stop and search any person when he has reasonable grounds to suspect that he has concealed goods in respect of which a customs offence has been committed.

4/ A physical search of a person shall be conducted by a person of the same sex.

5/ A physical search of a person shall be conducted in a polite manner without humiliating the searched person, endangering his health or causing damage to his property and within the limits required for detecting the goods concealed.

6/ When a customs officer has reasonable grounds to believe that internal search is necessary, the search shall be conducted by a qualified medical professional and without any risk to the person being searched.

7/ The customs officer shall obtain court authorization prior to conducting internal search on any person; provided, however, that if the person refuses to submit for internal search authorized by court, it shall be presumed that he has concealed the suspected goods.

8/ Any customs officer shall wear uniform while conducting search and show his identity card to the person concerned prior to commencement of the search.

9/ A customs officer may use the police force where, upon requesting the concerned person, he is denied to conduct search pursuant to the provisions of this Article.

10/ A customs officer may for good reason re-examine goods released after completing customs procedures.

**፻፵፫. ዕቃዎችንና መጓጓዣዎችን የመያዝ ሥልጣን**

፩/ ባለሥልጣኑ እቃዎች እና ማጓጓዣዎች፦

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፵፯ መሠረት ሊወረሱ የሚችሉ ከሆነ፣ ወይም

ለ) በቀጣይ ሂደት በማስረጃነት የሚፈለጉ ከሆነ፣

ሊይዛቸው ይችላል፡፡

፪/ ከጭነቱ ውስጥ ከፊሉ ዕቃ የጉምሩክ ህጎችን የመተላለፍ ድርጊት የተፈፀመበት በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ዲክላራሲዮን የቀረበባቸውን ዕቃዎች በመልቀቅ ጥፋቱ የተፈፀመባቸው ዕቃዎች እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የመያዝ እርምጃ ሲወስድ፦

ሀ) የተያዘውን ዕቃ ወይም ማጓጓዣ ዓይነትና ብዛት የሚያመለክት፣ እና

ለ) የመያዝ እርምጃው የተወሰደበትን ምክንያትና ተፈፀመ የተባለውን የጉምሩክ ህግን የመተላለፍ ድርጊት ዓይነት የሚገልጽ፣

ሰነድ ለሚመለከተው ሰው መስጠት አለበት፡፡

፬/ የተያዘው ዕቃ ወይም ማጓጓዣ ባለቤት ወይም ሃላፊ የሆነ ሰው ያልታወቀ ሲሆን ባለሥልጣኑ የዕቃው ባለቤት ወይም ሃላፊነቱን የሚወስድ ሰው እንዲቀርብ የጋዜጣ ማስታወቂያ በማውጣት ወይም ማስታወቂያውን ዕቃው ወይም ማጓጓዣው በተያዘበት አካባቢ በሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ ለህዝብ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ በመለጠፍ ይጠራል፡፡

**፻፵፬. የፖስታ ዕቃን የመክፈትና የመመርመር ሥልጣን**

፩/ የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ህጎችን ለማስፈጸም ሲባል የፖስታ እቃዎችን ባለቤቱ ወይም ወኪሉ ወይም የፖስታ ድርጅቱ ተወካይ ባለበት መክፈትና መመርመር ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ምርመራ የጉምሩክ ህግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመባቸው ዕቃዎች የተገኙ እንደሆነ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፵፫ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም "ባለቤት" ማለት ለገቢ ዕቃ ተቀባዩ ወይም ለወጪ ዕቃ ላኪው ነው፡፡

**፻፵፭. የተያዙ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን በዋስትና ስለመልቀቅ**

ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፵፫ መሠረት የተያዙ ዕቃዎችን ወይም መጓጓዣዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች

**143. Power to Seize Goods and Means of Transport**

1/ The Authority may seize goods and means of transport where:

a) they are liable to forfeiture pursuant to Article 147 of this Proclamation; or

b) they are needed as evidence in later procedure.

2/ Where an act of contravention of customs law relates to part of a consignment, the Authority shall release the goods for which customs declaration has been submitted and seize that part the consignment which relates to the contravention.

3/ When the Authority takes a measure of seizure pursuant to this Article, it shall furnish the person concerned with a document showing:

a) the description and quantity of the goods or means of transport seized; and

b) the reason for the seizure and the nature of the act of contravention of the customs law.

4/ Where the owner or person responsible for the seized goods or means of transport is unknown, the Authority shall summon such person through a newspaper notice or by a notice posted at a conspicuous place in the vicinity of the customs station where the goods or the means of transport are seized.

**144. Powers to Open and Examine Postal Goods**

1/ A customs officer may, for the purpose of enforcing the customs law, open and examine postal goods in the presence of the owner of the goods or his agent or a representative of the post office.

2/ When the examination under sub-article (1) of this Article reveals goods in respect of which contravention of the customs law has been committed, the provisions of Article 143 of this Proclamation shall be applicable.

3/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, the term "owner" means the consignee for import goods or sender for export goods.

**145. Release of Seized Goods and Means of Transport Against Security**

The Authority may release goods or means of transport seized pursuant to Article 143 of this Proclamation

በቂ ዋስትና በመያዝ ሊለቃቸው ይችላል፡-

፩/ ዕቃዎች ያልተከለከሉ፣ ገደብ ያልተደረገባቸው ወይም በቀጣይ ሂደት በማስረጃነት የማያስፈልጉ ከሆኑ፣

፪/ መጓጓዣዎቹ ዕቃዎችን ለመደበቅ እንዲያስችሉ ሆነው የተሠሩ፣ የተለወጡ ወይም መደበቂያ አካል የተገጠመላቸው ካልሆኑ ወይም በቀጣይ ሂደት ለፍርድ ቤት በማስረጃነት የማያስፈልጉ ከሆኑ፣ ወይም

፫/ የውርስ ውሣኔ የሚተላለፍባቸው ካልሆነ።

## ፻፵፮. ሰነዶችን የመመርመርና የመያዝ ሥልጣን

፩/ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) የጉምሩክ ህጎችን ከማስፈጸም ጋር በተያያዘ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኝ ሰነድ አስቀርቦ ለመመርመርና የሰነዶቹን ቅጂ የመውሰድ፣

ለ) ወደ አገር ከሚገባ ወይም ከአገር ከሚወጣ ዕቃ ጋር በተያያዘ የጉምሩክ ጥፋት ተፈጽሟል ብሎ ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖር ዕቃውን የሚመለከት ማናቸውንም ሰነድ የመመርመር፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የተመረመሩ ሰነዶች ለቀጣይ ሂደት በማስረጃነት የሚፈለጉ ሲሆን ሰነዶቹን የመያዝ፣

ሥልጣን ይኖረዋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) የተመለከቱት ሰነዶች በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ የተያዙ ሲሆንና የሰነዶቹ ባለይዞታ በሚፈለገው መንገድ አጠናቅሮ ለማቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ባለሥልጣኑ ሰነዶቹ የሚገኙበትን የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ መያዝ ይችላል።

## ፻፵፯. ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ስለመውረስ

፩/ የሚከተሉት ዕቃዎች ውርስ ሆነው ለመንግሥት ገቢ ይደረጋሉ፡-

ሀ) በኮንትሮባንድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች፣ ወይም ቀረጥና ታክስ ሊከፈልባቸው የሚገባ ሆኖ በማናቸውም አኳኋን የተደበቁ ዕቃዎች፣

ለ) ተደብቆ የተገኘው ዕቃ ዋጋ በዲክላራሲዮን ከተመዘገበው አጠቃላይ ዋጋ ከ፶ በመቶ በላይ ሆኖ ሲገኝ ተደብቀው የተገኙት ዕቃዎች፣

ሐ) ወደ አገር ውስጥ የገቡ ወይም ወደ ውጭ ሊላኩ በማጓጓዣ ላይ የተጫኑ ወይም ወደ ጉምሩክ ጣቢያ የገቡ የተከለከሉ ዕቃዎች፣

against adequate security where:

1/ the goods are not subject to any prohibitions or restrictions or needed as evidence at later stage in the procedure;

2/ the means of transport have not been constructed, altered or fitted with a compartment for the purpose of concealing goods or not needed as evidence in the court of law at later stage in the procedure; or

3/ the goods are not subject to forfeiture.

## 146. Power to Examine and Seize Documents

1/ The Authority shall have the power to:

a) examine and take copies of documents under the possession of any person in connection with the enforcement of the customs law;

b) examine any document related to import or export goods where it has sufficient grounds to suspect that customs offence has been committed with respect to such goods;

c) seize documents examined pursuant to this sub-article where they are needed as evidence in later procedure.

2/ Where the documents referred to in sub-article (1) (c) of this Article are stored in an electronic device and the person possessing them is unwilling to process and produce them in the required form, the Authority may seize the electronic device containing the documents.

## 147. Forfeiture of Goods and Means of Transport

1/ The following goods shall be forfeited to the government:

a) contraband imports or exports or dutiable goods found concealed in any manner;

b) if the value of goods that are concealed is more than 50% of the total declared value of goods imported or exported, goods concealed;

c) prohibited imports or prohibited exports put any means of transport or brought in customs station for the purpose of export;

መ) ገደብ የተደረገባቸው ሆኖ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር ወደ አገር ውስጥ የገቡና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፶፮ (፫) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደመጡበት አገር እንዲመለሱ ያልተደረጉ ዕቃዎች፤

ሠ) በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እያሉ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ውጪ በባለቤቱ እሽጋቸው ተከፍቶና ተለያይተው፣ ወደ ሌላ ሥፍራ ተዛውረው፣ ተለውጠው ወይም ተነካክተው የተገኙ ዕቃዎች፤

ረ) የዕቃው ባለቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፵፫ (፬) መሰረት በማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎለት ማስታወቂያ በወጣ በአንድ ወር ውስጥ ያልቀረበ ወይም አቤቱታ ያላቀረበ እንደሆነ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የዕቃ ውርስ የዕቃውን መያዣ ወይም መጠቅለያ ይጨምራል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወረሱ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የዋለ ማንኛውም ማጓጓዣ፡-

ሀ) ዕቃዎቹን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ የተሠራ፣ የተለወጠ ወይም መደበቂያ አካል የተገጠመለት ከሆነ፤

ለ) የማጓጓዣው ባለቤት እያወቀ የድርጊቱን መፈጸም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ፤ ወይም

ሐ) የማጓጓዣው ባለቤት ወይም ሃላፊ በአንቀጽ ፻፵፫(፬) መሠረት በማስታወቂያ ተጠርቶ ያልቀረበ እንደሆነ፤

ከዕቃዎቹ ጋር ውርስ ሆኖ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ውርሱ የሚመለከተው ዕቃ ወይም ማጓጓዣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፵፭ መሠረት በዋስትና የተለቀቀ ከሆነ የተያዘው ዋስትና ውርስ ሆኖ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚፈጸም የዕቃዎች ወይም ማጓጓዣዎች ውርስ በቅን ልቦና የዕቃዎቹ ወይም የማጓጓዣዎቹ ባለቤትነት የተላለፉላቸውን ሦስተኛ ወገኖች መብት የሚነካ አይሆንም፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ ማንኛውም ዕቃ ወይም ማጓጓዣ በዚህ አንቀጽ መሠረት ውርስ ሆኖ ለመንግሥት ገቢ ከመደረጉ በፊት የዕቃው ወይም የማጓጓዣው ባለቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፵፫ (፫) ወይም (፬) መሠረት የመያዝ እርምጃውን እንዲያውቀው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ተቃውሞውን እንዲያቀርብ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

d) restricted goods imported without obtaining authorization from the concerned organ and not re-exported within the period specified under Article 156 (3) of this Proclamation;

e) goods in respect of which bulk is broken, moved, altered or interfered by the owner while they are under customs control and without authorization by the Authority;

f) if the owner of the goods does not appear or lodge petition within one month after having been served with summon in accordance with Article 143 (4) of this Proclamation.

2/ The forfeiture of goods under sub-article (1) of this Article shall extend to the package or wrapper of the goods.

3/ Any means of transport used to carry goods liable to forfeiture under sub-article (1) of this Article shall be forfeited to the government if:

a) the means of transport is constructed, adopted or fitted with a compartment to conceal goods;

b) the owner of the means of transport, being aware of the fact, fails to take appropriate measure to prevent or stop the commission of the act; or

c) if the owner of the means of transport fail to appear after being summoned pursuant to Article 143(4) of this Proclamation.

4/ If the goods or the means of transport subject to forfeiture under this Article was released against security pursuant to the provisions of Article 145 of this Proclamation, the security furnished shall be forfeited to the government.

5/ The forfeiture of goods or means of transport under this Article may not affect the rights of third parties who have in good faith acquired ownership of the goods or means of transport.

6/ The Authority shall, prior to the forfeiture of any goods or means of transport pursuant to this Article, give the owner of the goods or the means of transport the opportunity to present his objection within one month from the date he has been notified of the measure of seizure in accordance with Article 143(3)or (4) of this Proclamation.

፯/ የዕቃው ወይም የማጓጓዣው ባለቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቃወሚያውን ካላቀረበ ወይም ያቀረበው መቃወሚያ በባለሥልጣኑ ተመርምሮ ተቀባይነት ካላገኘ የዕቃው፣ የመጓጓዣው ወይም የቀረበው ዋስትና ውርስ መሆንና ለመንግሥት ገቢ መደረግ ተፈጻሚ ይሆናል።

፰/ የዕቃው ወይም የማጓጓዣው ባለቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ያቀረበው ተቃውሞ ተቀባይነት ካገኘ ባለሥልጣኑ ዕቃውን፣ ማጓጓዣውን ወይም የተያዘውን ዋስትና ወዲያውኑ መልቀቅ አለበት።

፱/ የዕቃው፣ የመጓጓዣው ወይም የዋስትናው በዚህ አንቀጽ መሠረት ውርስ መሆንና ለመንግሥት ገቢ መደረግ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፵፱ መሠረት በተካሄደው የወንጀል ምርመራ ውጤት ላይ ተመሥርቶ በአጥፊው ላይ ሊቀርብበት የሚችለውን የወንጀል ክስ አያስቀርም።

## ፻፵፰. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት የመጣልና የማስፈጸም ሥልጣን</u>

፩/ ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ጥፋቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ በዚህ አዋጅ ክፍል ሰባት ምዕራፍ አንድ ድንጋጌዎች መሠረት የገንዘብ መቀጮ የመጣልና የማስፈጸም ሥልጣን ይኖረዋል።

፪/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ባለሥልጣኑ የሚጥለው መቀጫ ተፈፃሚ የሚሆነው መቀጫው እስከሚከፈል ድረስ ጥፋት የተፈጸመበትን ዕቃ በመያዝ ይሆናል። ሆኖም የተያዘው ዕቃ መቀጫውን ለማስፈፀም በቂ ካልሆነ ባለሥልጣኑ በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የአስመጪውን ንብረት በመያዝ ቅጣቱን ሊያስፈፅም ይችላል።

## ፻፵፱. <u>የጉምሩክ ወንጀልን የመመርመርና ክስ የመመሥረት ሥልጣን</u>

፩/ ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ህጎችን በመተላለፍ የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶችን የመመርመርና ክስ የመመሥረት ሥልጣን ይኖረዋል።

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የጉምሩክ ወንጀል ምርመራ ሲያካሂደውንና ክስ ሲመሠርት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ለፖሊስና ለዐቃቤ ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

፫/ ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ወንጀልን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊሰወሩ ወይም ሊጠፉ ይችላሉ የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲኖር በማናቸውም ቦታ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፍተሻ እንዲካሄድ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል።

7/ If the owner of the goods or means of transport fails to lodge his objection within the time limit specified under sub-article (6) of this Article or his objection, upon examination by the Authority, is rejected, the forfeiture of the goods, means of transport or the security furnished shall become effective.

8/ If the objection lodged by the owner of the goods or means of transport pursuant to sub-article (6) of this Article is accepted, the Authority shall forthwith release the goods, means of transport or the security furnished.

9/ The forfeiture of the goods, means of transport or the security furnished under this Article may not preclude the institution of criminal proceedings, based on the findings of the investigation conducted pursuant to Article 149 of this Proclamation.

## 148. <u>Power to Impose and Execute Administrative Penalties</u>

1/ The Authority shall have the power to impose and execute fines on persons committed customs offences in accordance with the provisions of Chapter One of Part Seven of this Proclamation.

2/ The penalty imposed by the Authority pursuant to sub-article (1) of this Article shall be executed by holding the release of the goods which are related to the offence until the fine is paid; provided, however, that in case the value of the goods is not sufficient to settle the fine, the Authority may seize the property of the importer in accordance with the Income Tax Proclamation to execute the penalty.

## 149. <u>Power to Investigate and Prosecute Customs Offences</u>

1/ The Authority shall have the power to investigate and prosecute offences committed in violation of the customs law.

2/ The Authority shall, in investigating and prosecuting customs offence pursuant to sub-article (1) of this Article, have the powers and duties of the police and the public prosecutor provided for under the Criminal Procedure Code.

3/ The Authority may, without court warrant, conduct a search at any place where there is sufficient ground to suspect an evidence relating to a customs offence may be concealed or lost within a short period of time.

## ምዕራፍ ሦስት
## ስለአቤቱታና ስለይግባኝ

### ፻፶፪. የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ስለማቋቋም

ባለሥልጣኑ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እና በዋናው መሥሪያ ቤት ደረጃ የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍሎች ያቋቁማል፡፡

### ፻፶፫. የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ሥልጣንና ተግባር

፩/ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍሎች፡-

ሀ) በዕቃዎች የስሪት አገር አወሳሰን፣ ዋጋ አተማመን፣ አሰያየም፣ አመዳደብና በታሪፍ ልክ፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተካሄደ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲትን ተከትሎ በተሰጡ ውሳኔዎች፤ እና

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ለ) እና (ሐ) ከተመለከቱት ውጪ በሆኑ ከጉምሩክ ፎርማሊቲ ጋር በተያያዘ በሚሰጡ ሌሎች አስተዳደራዊ ውሳኔዎች፤

ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የመመርመርና የመወሰን ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል፡፡

፪/ በባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት የሚቋቋም የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን የመመርመርና የመወሰን፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፵፯ (፮) መሠረት የሚቀርቡ የዕቃ ወይም የማጓጓዣ ውርስ መቃወሚያዎች ተቀባይነት ማጣት ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የመመርመርና ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ለወከለው ሃላፊ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ፤ እና

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፵፰ መሠረት በሚሰጡ አስተዳደራዊ የቅጣት ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የመመርመርና ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ለወከለው ሃላፊ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ፡፡

### ፻፶፬. የአቤቱታ አቀራረብና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፶፫ መሠረት ለማንኛውም የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ይግባኝ ቅሬታውን ያስከተለው ውሳኔ በፅሑፍ በተሰጠ በ፲፭ የስራ ቀናት ውስጥ በፅሑፍ መቅረብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ የአቤቱታ ወይም የይግባኝ ማመልከቻ አቤቱታው

## CHAPTER THREE
## COMPLAINTS AND APPEALS

### 152. Establishment of Complaint Review Sections

The Authority shall establish complaint review sections at the levels of its branch offices and at its head office.

### 153. Powers and Duties of Complaint Review Sections

1/ The Authority's branch offices complaint review sections shall have the powers and duties to review and decide on complaints lodged against:

a) decisions on the origin, valuation, description and tariff classification of goods;

b) decisions given following post clearance audit under this Proclamation;

c) other administrative decisions given in respect of customs formalities excluding decisions referred to in paragraph (b) and (c) of sub-article (2) of this Article.

2/ The complaint review section of the Authority established at the head office shall have the powers and duties to:

a) review and decide on appeals against decisions given under sub-article (1) of this Article;

b) review rejection of objections to the forfeiture of goods or means of transport lodged pursuant to Article 147(6) of this Proclamation and submit recommendations to the Director General of the Authority or any other officer delegated by him; and

c) review administrative penalties imposed pursuant to Article 148 of this Proclamation and submit recommendations to the Director General of the Authority or any other officer delegated by him.

### 154. Complaint Handling Procedures

1/ A complaint or an appeal to be lodged to any complaint review sections pursuant to Article 153 of this Proclamation shall be submitted in writing within 15 days from the date of the written decision causing the grievance.

2/ A complaint or an appeal to be lodged under sub-article (1) of this Article may be signed and

በሚመለከተው ሰው ወይም በወኪሉ ተፈርሞ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል የቀረበለትን አቤቱታ ባለሥልጣኑ በመመሪያ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መርምሮ ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል የቀረበለትን አቤቱታ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ካደረገው አቤቱታ አቅራቢው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይግባኝ ማቅረብ የሚችል መሆኑን በውሳኔው ውስጥ መግለጽ አለበት፡፡

**፻፶፭. ስለይግባኝ ሥነ ሥርዓት**

፩/ የባለሥልጣኑ አቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም የተወከለው ሃላፊ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በተሰጠ በአንድ ወር ውስጥ ይግባኙን በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የግብር ይግባኝ ጉባዔ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ የቀረጥና ታክስ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የግብር ይግባኝ ጉባዔው ክርክር ያስነሳው የቀረጥና ታክስ ክፍያ መፈጸሙን ሳያረጋግጥ ይግባኙን አይቀበልም፡፡

፫/ የግብር ይግባኝ ጉባዔው የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት አለበት በማለት የሚቃወም ተከራካሪ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በአንድ ወር ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ ይችላል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በገቢ ግብር አዋጁ የይግባኝ ሥነ ሥርዓትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚቀርቡ ይግባኞችም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት
## የጉምሩክ ጥፋቶችና ቅጣቶች

## ምዕራፍ አንድ
## የጉምሩክ ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች

**፻፶፮. በወጪና ገቢ ዕቃዎች ላይ የተጣለ ገደብን አለማክበር**

፩/ ማንኛውም ሰው ገደብ የተደረገበትን ዕቃ ፈቃድ ሳይኖረው ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ከአገር ያስወጣ ወይም ለማስወጣት የሞከረ እንደሆነ እና ከሚመለከተው አካል በአንድ ወር ውስጥ ፈቃድ ማቅረብ ካልቻለ ከብር ፲ሺ በማያንስና ከብር ፶ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

submitted by the aggrieved person or his agent.

3/ Any complaint review section shall review and decide on a complaint submitted to it and communicate its decision in writing to the complainant, within a period specified by directives of the Authority.

4/ Any complaint review section shall, if totally or partly rejects a complaint submitted to it, state in its decision the complainant's right to lodge an appeal pursuant to the provisions of this Proclamation.

**155. Appeal Procedures**

1/ Any person who is aggrieved by the decision of the Authority's complaint review section or the Director General of the Authority or the officer delegated by him may lodge an appeal to the Tax Appeal Commission established under the Income Tax Proclamation within one month from the date of such decision.

2/ If the appeal is with respect to payment of duties and taxes, the Tax Appeal Commission may not admit lodging of the appeal unless the disputed duties and taxes are paid.

3/ Any party dissatisfied with the decision of the Tax Appeal Commission on the ground of error of law may appeal to the Federal High Court within one month from the date of such decision.

4/ Without prejudice to sub-article (2) and (3) of this Article, the provisions of the Income Tax Proclamation relating to appeal procedures shall also be applicable to appeals lodged pursuant to this Article.

## PART SEVEN
## CUSTOMS OFFENCES AND PENALTIES

## CHAPTER ONE
## CUSTOMS OFFENCES AND ADMINISTRATIVE PENALTIES

**156. Failure to Comply with Restrictions on Import and Export of Goods**

1/ Any person who, without having authorization, imports, exports or tries to export restricted goods and fails to obtain such authorization from the concerned organ within one month shall be punishable with fine not less than Birr 10,000 and not exceeding Birr 50,000.

፪/ ማንኛውም መንገደኛ ይዞት የተገኘ ዕቃ በብዛት ወይም በዋጋ በህግ ወይም በሚኒስቴሩ መመሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ የሆነ እንደሆነ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቃውን ቀረጥና ታክስ እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መቀጮ ያስከተለው ዕቃ የገቢ ዕቃ ከሆነ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ለማቅረብ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ካበቃ በኋላ በአንድ ወር ውስጥ በአስመጪው አማካይነት ተመልሶ እንዲወጣ፣ የወጪ ዕቃ ከሆነም ከአገር እንዳይወጣ ይደረጋል፡፡

**፻፶፯. ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል ወይም አንሶ እንዲከፈል ስለማድረግ**

፩/ ማንኛውም ሰው ለጉምሩክ ፎርማሊቲ በቀረበ የዕቃ ዲክላራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ወይም ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወይም አነስተኛ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት ወደ አገር እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ካደረገ ወይም ከአገር እንዲወጣ ለማድረግ የሞከረ እንደሆነ ያልተከፈለው የዕቃው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚሁ ቀረጥና ታክስ እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በጠቅላላ ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ በብልጫ የሚፈለገው ከ፲ በመቶ የማይበልጥ ከሆነ አስመጪው በልዩነት የተገኘውን ቀረጥና ታክስ ያለ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

**፻፶፰. እሽጎችን ስለመፍታትና ምልክቶችን ስለማንሳት**

ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የጉምሩክ ሹም ፈቃድ ሳያገኝ በመተላለፍ ላይ ያለ ወይም የጉምሩክ ወደብ የደረሰ፡-

፩/ ማጓጓዣ ወይም ኮንቴይነር ላይ የተደረገውን የጉምሩክ ማሸጊያ የፈታ ወይም ያላቀቀ እንደሆነ፤

፪/ ዕቃ ወይም የዕቃው መያዣ ላይ የተደረገውን ምልክት ያነሳ፣ የፋቀ፣ የሰረዘ ወይም የለወጠ እንደሆነ፤ ወይም

፫/ የዕቃን መያዣ የከፈተ ወይም ጥቅሎችን የበተነ እንደሆነ፤

ከብር ፲ሺ በማያንስና ከብር ፶ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**፻፶፱. ናሙናዎችን አለመመለስ**

ማንኛውም ሰው ለናሙና የወሰደውን ዕቃ ያልመለሰ ወይም በዕቃው የተገለገለ ወይም ዕቃው እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ የዕቃውን ዋጋ፣ ቀረጡንና ታክሱን መክፈሉ እንደተጠበቀ

2/ Any traveller who is found in possession of goods which exceed, in quantity or value, the limits specified by law or directives of the Ministry shall, without prejudice to settlement of the duty and tax payable, be punishable with fine equivalent to twice the amount of such duty and tax.

3/ Where the imposition of penalty under sub-article (1) of this Article relates to import, the goods shall be re-exported by the importer within one month from the expiry of the period allowed for obtaining authorization from the concerned organ, and in the case of goods destined for export, they shall be prevented from being exported.

**157. Causing Evasion or Understatement of Duties and Taxes**

1/ Any person who causes the importation or exportation of goods or attempts to export such goods, without payment of duty and tax or with the payment of understated duty and tax, by not entering or correctly stating them in a declaration submitted for completing customs formalities shall, without prejudice to settlement of the duty and tax payable, be punishable with fine equivalent to twice the amount of such duty and tax.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, if the remaining duties and taxes payable are not more than 10% of the total duty and tax payable, the importer shall pay the remaining duties and taxes without the penalty.

**158. Opening of Parcels and Removal of Marks**

Any person, who, without being authorized by the appropriate customs officer:

1/ removes or disconnects the customs seals affixed on a means of transport or container of goods;

2/ removes, defaces, cancel or alter labels affixed on goods or their package; or

3/ opens packages or breaks bundles of goods;

during transit or arrival at customs port shall, be punishable with fine not less than Birr 10,000 and not exceeding Birr 50,000.

**159. Failure to Return Samples**

Any person who fails to return samples of goods or who uses or damages them shall, without prejudice to the

ሆኖ የቀረጥና ታክሱን እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፩፻፷. <u>የአጓጓዥ ግዴታዎችን ያለማክበር</u>

፩/ ማንኛውም አጓጓዥ፦

ሀ) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመንገደኞች ወይም የጭነት መግለጫ ካላቀረበ፤

ለ) ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲገባ ካደረገ፤ ወይም

ሐ) ማጓጓዣው ከጉምሩክ ወደብ እንዲወጣ ከተወሰነ በኋላ ምክንያቱን ለጉምሩክ ሹም ሳያስረዳና ፈቃድ ሳያገኝ እንዲቆይ ካደረገ፤

ከብር ፪ሺ በማያንስ እና ከብር ፭ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም አጓጓዥ ጉምሩክ ወደብ በደረሰ ማጓጓዣ ላይ የጉምሩክ ሹም በሌለበት ዕቃ የጫነ፣ ያራገፈ ወይም ለመጫን ወይም ለማራገፍ ሙከራ ያደረገ እንደሆነ ከብር ፯ሺ በማያንስና ከብር ፲ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፩፻፷፩. <u>የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ግዴታዎችን ስለማክበር</u>

በማንኛውም የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ግዴታዎቹን ያላከበረ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፸፮(፫) መሠረት በሚወጣ መመሪያ ላይ ተመሥርቶ ሊወሰድ የሚችል ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር ፶ሺ በማያንስና ከብር ፩፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፩፻፷፪. <u>የጉምሩክ የትራንዚት ሥነ ሥርዓትን አለማክበር</u>

ማንኛውም ሰው የጉምሩክ የትራንዚት ሥነሥርዓትን በሚመለከት ተፈጻሚነት የሚኖረውን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያላከበረ እንደሆነ ከብር ፭ሺ በማያንስና ከብር ፳ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፩፻፷፫. <u>ከቀረጥ ነፃ በገባ ዕቃ ያለአግባብ ስለመገልገል</u>

፩/ ማንኛውም ሰው ከቀረጥ ነፃ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባን ዕቃ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሚቃረን ሁኔታ፦

ሀ) የቀረጥ ነፃ መብቱ ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ በሌላ አገልግሎት ላይ ያዋለ ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፈ እንደሆነ፤

ለ) ዕቃው ለግል አገልግሎት እንዲውል የገባ ሲሆን በማናቸውም መልኩ ከቤተሰብ ውጪ በሌሎች ሰዎች አገልግሎት ወይም ይዞታ ሥር እንዲውል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

payment of the value of the goods and duty and tax payable on the goods, be punishable with fine equivalent to twice the amount of such duty and tax.

## 160. <u>Failure to Comply with Obligations of Carrier</u>

1/ Any carrier who:

a) fails to submit travelers or cargo manifest within the specified time;

b) gives access to any unauthorized person to the means of transport; or

c) delays the departure of the means of transport from the customs port without notifying and getting permission from the customs officer;

shall be punishable with fine not less than Birr 2,000 and not exceeding Birr 5,000.

2/ Any carrier who loads, unloads or attempts to load or unload goods in the absence of customs officer shall be punishable with fine not less than Birr 7,000 and not exceeding Birr 10,000.

## 161. <u>Failure to Comply with Warehouse Permit Conditions</u>

Any warehouse permit holder who fails to comply with permit conditions under this Proclamation shall, without prejudice to any additional administrative measure that may taken in accordance with directives issued pursuant to Article 176(3) of this Proclamation, be punishable with fine not less than Birr 50,000 and not exceeding Birr 100,000.

## 162. <u>Failure to Observe Customs Transit Procedures</u>

Any person who engages in the transit of goods and fails to observe the customs procedure applicable to the transit of goods shall be punishable with fine not less than Birr 5,000 and not exceeding Birr 20,000.

## 163. <u>Misuse of Duty Free Goods</u>

1/ Any person who, contrary to the provisions of this Proclamation:

a) uses duty free goods or goods imported on the basis of reduced rate of duty and tax for purposes other than which the duty relief is granted or transfers them to another person;

b) places duty free goods or goods imported on the basis of reduced rate of duty and tax for personal use under the service or possession of other persons outside of his family; or

ሐ) ዕቃው ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የገዛ፣ የተቀበለ፣ የተገለገለ፣ ያስተላለፈ፣ ወይም ለሌሎች ሰዎች አገልግሎት እንዲውል ያደረገ እንደሆነ፣

ዕቃው በተያዘበት ጊዜ ወደ አገር እንደገባ ተቆጥሮ ለዕቃው ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱን ፶በመቶ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) አፈፃፀም "ቤተሰብ" ማለት የባለመብቱን የትዳር ጓደኛ፣ ልጆችና የባለመብቱንና የትዳር ጓደኛውን ወላጆችን ብቻ ያጠቃልላል፡፡

## ፻፷፬. በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባን ዕቃ ያለአግባብ ስለመገልገል

ማንኛውም ሰው በጊዜያዊነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ አገር የገባን ዕቃ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሚቃረን ሁኔታ ሲጠቀምበት የተገኘ እንደሆነ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቀረጥና ታክስ ፶በመቶ በመቀጫ መልክ ከፍሎ ዕቃው ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## ፻፷፭. ሌሎች ጥፋቶች

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ክልከላዎችን ወይም ግዴታዎችን ባለማክበር በዚህ ምዕራፍና በዚህ ክፍል ምዕራፍ ሁለት ከተመለከቱት ውጪ ሌላ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ከብር ፲ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የጉምሩክ ወንጀሎችና ቅጣቶች

## ፻፷፮. የጉምሩክ ቁጥጥርን ስለማሰናከል

፩/ ማንኛውም ሰው የጉምሩክ ሹም ሰነዶችን እንዳይመረምር ወይም ማጓጓዣዎችን ወይም ዕቃዎችን እንዳይፈትሽ ወይም ወደ መጋዘን፣ የንግድ መደብር ወይም መኖሪያ ቤት እንዳይገባ ያደረገ ወይም ሁከት የፈጠረ ወይም ለሚጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ያልሰጠ ወይም ለምርመራ ያልተባበረ ወይም በማናቸውም መንገድ ሥራውን ለማደናቀፍ ጣልቃ የገባ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር ፭ሺ በማያንስና ከብር ፲ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ሃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የእስራት ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ከፍ ይደረጋል፡፡

c) knowingly or ought to have been aware of the fact that the goods are imported duty free or on the basis of reduced rate of duty and tax, buys, receives, uses, transfers or places such goods under the services of others;

shall, without prejudice to settlement of the duty and tax payable assuming that the goods are imported at the time of seizure, be punishable with fine equivalent to 50% of the amount of such duty and tax.

2/ For the purpose of sub-article (1)(b) of this Article, the term "family" includes only the spouse, children and parents of the beneficiary and the spouse.

## 164. Misuse of Temporarily Imported Goods

Any Person who, contrary to the provisions of this Proclamation, uses goods temporarily imported without payment of duties and taxes, shall be punishable with fine equivalent to 50% of the duties and taxes payable without affecting the forfeiture of the guarantee, and the goods shall be re-exported.

## 165. Other Offences

Any person who, through failure to comply with prohibitions or obligations prescribed under this Proclamation, commits any offence other than those specified under this Chapter and Chapter Two of this Part shall be punishable with fine not exceeding Birr 10,000.

## CHAPTER TWO
## CUSTOMS CRIMINAL OFFENCES AND PENALTIES

## 166. Obstruction of Customs Control

1/ Any person who obstructs or hinders the duties of a customs officer in the investigation of documents or the inspection of a means of transport or goods, prohibits him from entering a warehouse, a business premise or a dwelling house, refuses to reply to the inquiries of the customs officer, resists to co-operate for investigation or interferes by any means so as to obstruct the duties of the customs officer shall be punishable with simple imprisonment not less than six months and not exceeding one year and with fine not less than Birr 5,000 and not exceeding Birr 10,000.

2/ Where the offence referred to in sub-article (1) of this Article is committed by the use of force or by an organized group the imprisonment shall extend from one to five years rigorous imprisonment.

**፻፷፯ ሰነዶችንና መለያዎችን ወደ ሀሰተኛነት ስለ መለወጥና አስመስሎ ስለመሥራት**

ማንኛውም ሰው፡-

፩/በባለሥልጣኑ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፣ ባለሥልጣኑ የሚጠቀምበትን ቅፅ፣ ማህተም፣ መታወቂያ፣ ዓርማ፣ የጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ማንኛውንም ሰነድ ወይም ምልክት ወደ ሀሰተኛነት የለወጠ ወይም አስመስሎ የሠራ ወይም ይህንኑ ያከፋፈለ፣ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከረ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ክብር ፭ሺ በማያንስና ክብር ፲ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤

፪/ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፣ ባለሥልጣኑ የሚጠቀምበትን የደንብ ልብስ አስመስሎ የሠራ ወይም ይህንኑ ያከፋፈለ፣ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከር እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ክብር ፭ሺ በማያንስና ክብር ፲ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

**፻፷፰. የኮንትሮባንድ ወንጀል**

፩/ ማንኛውም ሰው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የጉምሩክ ህጎችን በመተላለፍ የተከለከሉ፣ ገደብ የተደረገባቸው ወይም የንግድ መጠን ያላቸውና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመባቸው ዕቃዎችን በድብቅ ወይም ከህጋዊ መተላለፊያ መስመሩ ውጪ ወደ አገር ካስገባ፣ ከሀገር ካስወጣ ወይም ከአገር ለማስወጣት ወይም ለማስገባት ከሞከረ ወይም በህጋዊ መንገድ የወጡ ዕቃዎችን በህገወጥ መንገድ መልሶ ካስገባ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ክብር ፶ሺ በማያንስና ክብር ፪፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ሕገወጥ መንገድ የተገኙ ዕቃዎች መሆናቸውን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ዕቃዎቹን ያጓጓዘ፣ ያከማቸ፣ የያዘ፣ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ማንኛውም ሰው ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት እና ክብር ፶ሺበማያንስና ክብር ፩፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ሃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የፅኑ እስራት ቅጣቱ ከ፲ ዓመት እስከ ፲፭ ዓመት ከፍ ይደረጋል።

**167. Falsifying and Counterfeiting Documents and Symbols**

Any person who:

1/ with intent to cause damage to the Authority or to procure undue advantage for himself or for any other person, falsifies or counterfeit forms, seal, identity cards, emblem, customs seals or any other document or symbol or distributes, uses or attempts to use same shall be punishable with rigorous imprisonment not less than five years and not exceeding ten years and with fine not less than Birr 5,000 and not exceeding Birr 10,000;

2/ with intent to procure undue advantage for himself or for any other person or to cause damage to another person, counterfeits uniforms used by the Authority or distributes, uses or attempts to use same shall be punishable with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding five years and with fine not less than Birr 5,000 and not exceeding Birr 10,000.

**168. Contraband**

1/ Any person who, knowingly or ought to have been aware of the fact, imports, exports or attempts to export prohibited or restricted goods or goods subject to customs clearance by smuggling or out of their legal route or illegally imports duly exported goods, in contravention of customs law shall be punishable with rigorous imprisonment not less than five years and not exceeding ten years and with fine not less than Birr 50,000 and not exceeding Birr 200,000.

2/ Any person who transports, stores, possesses, offers for sale or buys goods referred to in sub-article (1) of this Article while being or ought to have been aware of the fact shall be punishable with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding five years and with fine not less than Birr 50,000 and not exceeding Birr 100,000.

3/ Where the criminal offence referred to in sub-article (1) of this Article is committed by the use of force or by an organized group, the rigorous imprisonment shall extend from ten years to fifteen years.

፬/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም በህገወጥ መንገድ ከአገር ለመውጣት በጉምሩክ የጠረፍ መስመር ውስጥ የተያዘ ወጪ ዕቃ የኮንትሮባንድ ዕቃ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል።

4/ For the purpose of this Article goods seized within the customs frontiers strip to be illegally exported shall be considered as contraband goods.

## ፻፷፱ የማጭበርበር ወንጀል

፩/ ማንኛውም ሰው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው በህጋዊ ዕቃ ከለላነት፣ ክልክላ የተደረገበትን ዕቃ ወደ አገር ካስገባ፣ ከአገር ካስወጣ ወይም ከአገር ለማስወጣት ወይም ወደ አገር ለማስገባት የሞከረ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር ፶ሺ በማያንስና ከብር ፪፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ ተደብቆ የተገኘው ዕቃ ዋጋ በዲክላራሲዮን ላይ ከተገለጸው ጠቅላላ ዋጋ ፶በመቶ በላይ ሆኖ ከተገኘ ዕቃዎችን በመደበቅ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ወደ አገር ለማስገባት ወይም ከአገር ለማስወጣት የሞከረ ማናቸውም ሰው ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ፶ሺ በማያንስና ከብር ፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

## 169. Crime of Fraudulent Acts

1/ Any person who, knowingly or ought to have been aware of the fact, imports or exports or attempts to import or export prohibited goods under the cover of legally declared goods shall be punishable with rigorous imprisonment not less than five years and not exceeding ten years and with fine not less than Birr 50,000 and not exceeding Birr 200,000.

2/ Any person who attempts to illegally import or export goods shall be punishable with rigorous imprisonment of not less than five years and not exceeding ten years, and fine not less than Birr 50,000 and not exceeding Birr 100,000 where the value of the goods concealed is more than 50% of the total declared value of the goods.

## ፻፸. እሽጎችን በመፍታትና ምልክቶችን በማንሳት ስለሚፈጸም ወንጀል

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፶፰ የተመለከተው ጥፋት የተፈጸመው ዕቃውን ለማጉደል፣ አንዱን ዕቃ ከሌላው ለመደባለቅ፣ ለማበላሸት፣ ለመስረቅ ወይም በማናቸውም አኳኋን እራሱን ወይም ሌላውን ሰው ለመጥቀም ወይም ማንኛውንም ሰው ለመጉዳት በማሰብ ከሆነ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከብር ፶ሺ በማያንስና ከብር ፪፻ሺ በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ሃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የፅኑ እስራት ቅጣቱ ከአሥር እስከ አስራ አምስት ዓመት ከፍ ይደረጋል።

## 170. Crime Committed by Opening of Parcels and Removal of Marks

1/ Where the offence referred to in Article 158 of this Proclamation is committed with the intent to remove, mix up, damage or steal the goods or in any manner to procure undue advantage to himself or another person or to cause damage to any person, the punishment shall be rigorous imprisonment not less than five years and not exceeding ten years and fine not less than Birr 50,000 and not exceeding Birr 200,000.

2/ Where the offence referred to in sub-article (1) of this Article is committed by the use of force or by an organized group the rigorous imprisonment shall extend from ten to fifteen years.

## ፻፸፩. የአጓጓዥ ግዴታዎችን በመጣስ ስለሚፈጸም ወንጀል

ማንኛውም አጓጓዥ ወደ አገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎችን ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖር ከጉምሩክ ወደብ ውጪ ካራገፈ ወይም ከጫነ ወይም ለማራገፍ ወይም ለመጫን ከሞከረ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር ፯ሺ በማያንስና ከብር ፲፭ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

## 171. Criminal Offence by Carrier

Any carrier who, in the absence of force majeure, unloads, loads or attempts to unload or load import or export goods at a place other than a customs port shall be punishable with rigorous imprisonment not less than five years and not exceeding ten years and with fine not less than Birr 7,000 and not exceeding Birr 15,000.

**፻፸፪. <u>የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ያለአግባብ መጠቀም</u>**

ማንኛውም ሰው ያለባለሥልጣኑ ፈቃድ የባለሥልጣኑን የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት የተጠቀመ ወይም ያልተፈቀደለት ሌላ ሰው እንዲጠቀም ያደረገ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ፭ሺ በማያንስና ከብር ፳ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**፻፸፫. <u>በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ ስለሚፈጸም ቅጣት</u>**

በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በወንጀል ህግ አንቀጽ ፴፬ በተደነገገው መሠረት በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱ የጉምሩክ ወንጀሎች ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ በወንጀል ህጉ አንቀጽ ፺ መሠረት ይቀጣል፡፡

**፻፸፬. <u>የማስረጃ ተቀባይነት</u>**

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ተቀባይነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ማስረጃዎች በፍርድ ቤት በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡-

፩/ ዲጂታል ወይም ኤሌክትሮኒክስ ማስረጃዎች፤

፪/ በውጭ አገር የህግ አስከባሪ አካላት የተገኙ ማስረጃዎች፤

፫/ በጉምሩክ ቁጥጥርና ህግን በማስከበር ሂደት በባለሥልጣኑ የተሰባሰቡ ማስረጃዎች፤

፬/ ከዕቃዎች ምደባ ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ጉምሩኮች ድርጅት የተዘጋጁ ሰነዶች፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፻፸፭. <u>የጉምሩክ መጋዘኖች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ</u>**

፩/ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ እና ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን የኪራይ ወይም የግል አገልግሎት የሚሰጡ ሆነው ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡

፪/ የወል ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም የወል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን፡-

ሀ) ዕቃ የማጓጓዝ ሥራ በሚያካሂድ የንግድ ድርጅት፤

ለ) የመጋዘን አገልግሎት ሥራ ለመሥራት በተቋቋመ የንግድ ድርጅት፤

**172. <u>Unauthorized Use of Electronic Information Exchange System</u>**

Any person who uses or allows another person to use the Authority's electronic information exchange system without authorization of the Authority shall be punishable with rigorous imprisonment not less than three years and not exceeding five years and with fine not less than Birr 5,000 and not exceeding Birr 20,000.

**173. <u>Punishment Applicable to Legal Persons</u>**

A legal person which participates in the commission of customs criminal offence in this Chapter as provided in Article 34 of the Criminal Code shall be punishable in accordance with Article 90 of the Code.

**174. <u>Admissibility of Evidence</u>**

Without prejudice to admissibility of evidences presented in accordance with the Criminal Procedure Code and other relevant legislations, the following shall be admissible evidences:

1/ digital or electronic evidences;

2/ evidence gathered by foreign law enforcement bodies;

3/ evidence gathered by the Authority through the process of customs control and law enforcement;

4/ documents prepared by the World Customs Organizations in relation to classification of goods.

## <u>PART EIGHT</u>

## <u>MISCELLANIOUS PROVISIONS</u>

**175. <u>Establishment and Types of Customs Warehouses</u>**

1/ Temporary customs storages and bonded customs warehouses may be established for rental or private use upon obtaining permits granted by the Authority.

2/ Public temporary customs storage or public bonded customs warehouse may be established, for rental use, by:

a) an enterprise engaged in freight transport;

b) an enterprise established to operate warehouse service;

ሐ) የኢንዱስትሪ ዞን አገልግሎት ለመስጠት በተቋቋመ ድርጅት፣

መ) ዕቃ የማስተላለፍ ሥራ በሚያካሂድ የንግድ ድርጅት፣ ወይም

ሠ) በባለሥልጣኑ መመሪያ በሚወሰን ማንኛውም ሌላ ሰው፣

ለኪራይ አገልግሎት ሊቋቋም ይችላል፡፡

፫/ የግል ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ፡-

ሀ) በመንግሥት ፕሮጀክት ላይ በተሠማራ የሥራ ተቋራጭ፣ ወይም

ለ) ባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ በሚፈቅድለት ሌላ ሰው፣

ለግል አገልግሎት ሊቋቋም ይችላል፡፡

፬/ የግል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን፡-

ሀ) ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ለመሸጥ በተቋቋመ ድርጅት፣

ለ) ለእርዳታ ወይም ለንግድ ዓላማ ባልተቋቋመ ድርጅት፣

ሐ) ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎችንና ግብዓቶችን በመጠቀም ዕቃዎችን በሚያመርት ድርጅት፣ ወይም

መ) በባለሥልጣኑ መመሪያ በሚወሰን ማንኛውም ሌላ ሰው፣

ለግል አገልግሎት ሊቋቋም ይችላል፡፡

፭/ የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የሚቋቋመውና የሚተዳደረው በባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

፮/ የጉምሩክ መጋዘኖች ደረጃ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፻፸፮. የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ**

፩/ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ለኪራይ አገልግሎት ለማቋቋም ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የሚጠይቅ ሰው፡-

ሀ) የሚያከናውነውን የሥራ ዓይነት የሚገልጽ ማስረጃ፣

ለ) ሥራውን ለማከናወን የተሰጠውን ፈቃድ፣

ሐ) አመልካቹ ድርጅት ከሆነ የሕግ ሰውነት የተሰጠው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣

መ) የመጋዘኑን የህንፃ ፕላን ፤

c) an enterprise established to provide industrial zone services;

d) an enterprise established to operate customs clearing services; or

e) any other person specified by directive of the Authority.

3/ Private temporary customs storage may be established, for private use, by:

a) a contractor engaged in a government project; or

b) any other person exceptionally authorized by the Authority.

4/ Private bonded customs warehouse may be established, for private use, by:

a) an enterprise engaged in the sale of duty free goods;

b) a charity or other non-profit making organization;

c) an enterprise engaged in the manufacturing of goods using raw materials and accessories acquired without payment of duty and tax; or

d) any other person specified by directives of the Authority.

5/ Government customs warehouse shall be established and operated by the Authority.

6/ The standards of customs warehouses shall be determined by directives to be issued by the Authority.

**176. Customs Warehouse Permit**

1/ Any person applying for a permit to establish temporary customs storage or bonded customs warehouse, for rental use, shall submit his application to the Authority together with:

a) documents showing the specific activities of his business;

b) the license issued to operate the business;

c) certificate of registration where the applicant is an enterprise;

d) the building plan of the warehouse;

በባለሥልጣኑ ወጪ የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኝ ወይም የባለሥልጣኑ ነገረፈጅ እንዲከራከርለት ይደረጋል፤

፪/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በቅን ልቦና በፈፀመው ተግባር ለሚደርስ ጉዳት ካሳ እንዲከፍል አይጠየቅም፡፡

**፻፹. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፻፹፩. ስለተሻሩ ሕጎችና ስለሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት**

፩/ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፪/፪ሺ፩ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ነባር ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ አዲስ ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

**፻፹፪. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በነበረው ህግ መሰረት ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡

**፻፹፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

Authority's attorney in legal proceedings instituted against him in connection with any act committed in the course of properly discharging his official duties;

2/ may not be held liable to pay compensation for any damage arising from any bona fide action taken under the provisions of this Proclamation.

**180. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Authority may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

**181. Repeal and the Applicability of other Laws**

1/ The Customs Proclamation No. 622/2009 is hereby repealed.

2/ No law or customary practice may, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have force or effect with respect to matters provided for by this Proclamation.

3/ Without prejudice to the provision of sub-article (2) of this Article, existing regulations and directives shall continue in force until replaced by new regulations and directives issued hereunder.

**182. Transitory Provisions**

Without prejudice to the provisions of other laws cases pending before the effective date of this Proclamation shall be disposed in accordance with the previous laws.

**183. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 9th day of December, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**